# ጥያቄ እና መልስ

# በዕብራውያን ክፍል I

ያለ እግዚአብሔር እንዴት ማድረግ ትችላለች? ያ እውነተኛ መሆን አለበት፡ አይደል? ያለ እግዚአብሔር ማድረግ አይቻልም።

ከነሱ ሁሉ አልሰብክም። ብቻ ግን ጥያቄዎቹ በጣም ከባድ ይሆናሉ ብዬ አስቤ ነበር፡ ታውቃላችሁ፡ ስለዚህ ብዘጋጅ ይሻለኛል ብዬ አሰብኩ። ነገር ግን፡ ኦህ፡ በጣም፡ በጣም ቀላል ነበር። ስለዚህ ምናልባት በሕዝቡ መካከል ብዙ ከባድ ጥያቄዎች የሉም፡ በጣም ቀላልና የማይከብዱ ጥያቄዎች ብቻ ናቸው ያሉት። እንግዲህ፡ በጌታ እርዳታ፡ የምችለውን ሁሉ ለመመለስ በመሞከሬ ደስተኛ ነኝ።

2 እህት አርጋንብራይት ዛሬ ማታ እዚህ ነች… እኅት ሩት። እዚህ ነሽ፡ እኅት ሩት? እዚያ ጋር። ኦ… ኦህ፡ አዎ፡ እዚህ አድራሻ አገኘሁት፡ አ… አይ፡ አይደለም። ደህና፡ ከዚህ ላገኘው እችላለሁ። በኪስ ቦርሳዬ ውስጥ ይዤው ነበርና፡ የኪስ ቦርሳዬን ቤት ትቼ መጣሁ። አሁን፡ ወደ ቤት ስሄድ ፖሊስ ከያዘኝ፡ ወንድም ፍሊማን፡ አንተ ትመጣልኛለህ። ቢሊን ንገረው… የኪስ ቦርሳዬን በቤት ውስጥ ትቼአለሁ፡ ዛሬ ማታ የምነዳው ያለ መንጃ ፍቃድ ነው። ኪሴ ውስጥ ያለ መሰሎኝ ነበር፡ ከዚያ ልብስ ቀየርኩ። ዛሬ ከሰአት፡ በችኮላ ሳር እያጨድኩ ነበረና አቋሪጬ፡ ቸኩዬ ወደ ቤት ገባሁና፡ ልብሴን ቀይሬ ወደዚህ መጣሁ። መዝገበ ቃላት አ—አምጥቻለሁ፡ ነገር ግን ከዚህ ከፕሮግራሙ በኋላ መጠቀም ትችላላችሁ።

3 **በዚያ** በማስታወሻው ጉዳይ ቅር አይበላችሁ። ከዚህ የሚከፋ ካላገኘሁ፡ ከእስካሁኖቹ ይህ በጣም ጥሩ ማስታወሻ ነው። ጥሩ ነበር። እጅግ፡ በጣም ጥሩ ነው። እንዳላነበብኩት ነግሪያችሁ ነበር፡ ነገር ግን በጨረፍታ አይቸዋለሁ፡ ታውቃላችሁ፡ ከዛ በላይ ላየው አልቻልኩም። በጥያቄው ምን እንዳላችሁ ብቻ ነው ያየሁት። እጅግ፡ በጣም ጥሩ ነበር፡ ልክ የትምህርት ቤት አስተማሪ መጻፍ እንዳለበት ነው የተጻፈው። ያም ድንቅ ነበር፡ አድንቄአለሁ። እና—ይህ የሚሰጣችሁ…

4 አያችሁ፡ ከ—ከእናንተ ትንሽ የሚለይ ሰው ጥያቄ እወዳለሁ። አያችሁ፡ ሁል ግዜ ተመሳሳይ ከሆነ፡ ማንም የሚቃረናችሁ ሰው ከሌለ፡ ሳትለወጡ ባላችሁበት ቦታ ትቀጥላላችሁ። ለመረዳትና ነገሮችን በጥልቀት ለማየት ትንሽ ልዩነት ሊኖራችሁ ይገባል። ዙሪያችሁን የ—የማትመለከቱት ከሆነ ለውጥ ወደሌለው ነገር ውስጥ ትገባላችሁ፡ ከ—ከዚያም ያንን ስታደርጉ በችግር ውስጥ ትገባላችሁ። ጉዟችሁን መቀጠል አለባችሁና ከእናንተ ጋር የሚቃረን ሰው ማግኘት አለባችሁ ከዚያም በዚያ ነገር ተነቃቁ።

5 በአፍሪካ ሁለት ትናንሽ አንበሶችን አገኘሁ፡ ትናንሽ አንበሶች ነበሩ፡ ልክ **እንደዚያ** ያሉት። የሚያምር ቀለም ያለው፡ አነስተኛ፡ ትንሹ አንበሳ፡ ትንሽ አንበሳ፡ ትንሿ ሴት አንበሳ ነበሩ። እናም፡ ድመቶች ይመስላሉ፡ ያን ያህል

በጣም ትንሽ ነበሩ፡ በ... በጣም ቆንጆ ትናንሽ ነገር ነበሩ፡ እንዲሁ ይጫወታሉ። ወደ አሜሪካም ላመጣቸው ነበር፡ በወፍ መያዣ ውስጥ አስቀመጥኳቸው። ወደዚህ ላመጣቸው ሄድኩ፡ ነገር ግን ሊከትባቸው የሚችል፡ ም—ምንም አይነት ክትባት ማግኘት አልቻልኩም። ክትባት ሳይደረግላቸው ወደ አሜሪካ እንዳስገባቸው አልፈቀዱልኝምና፡ ክትባቱን በመላው አፍሪካ ውስጥ ማግኘት አልቻልኩም። ነገር ግን አንበሳ መሆኑን ለማወቅ ከፈለጋችሁ፡ ትንሽ ወደ ኋላ ገፋ አድርጉት። ከእናንተ ጋር ለመፋለም እንደሚዘጋጅ ይቆምና አንበሳ መሆኑን ያሳውቃችኋል፡ ሰ—ሰለዚህ ያ አቋሙ እንዴት እንዴት እንደሆነ ያሳውቃችኋል።

6 አንዳንዴ ማድረግ ያለባችሁ እንደዛ ነው፡ ታውቃላችሁ፡ ለመፈተሽ ያክል፡ ክንፎቻችሁን ወደኋላ መዘርጋት አለባችሁ። ነገር ግን፡ አሁን፡ እንደ አንበሳ አንቆጣ፡ ሰ—ሰዎች ጥያቄ ሲጠይቁን፡ ያ... ያንን እንወዳለን። እህት ሩት፡ እንደዛ አይነት ጥያቄ፡ ለእኔ እጅግ፡ በጣም ጥሩ ነው። እ... ያ—ያንን እወዳለሁ፡ እያችሁ። እጅግ አስጸያፊ የሆኑትን ጥያቄዎችን ነው የሚጠላቸው። ነገር ግን እጅግ... ጥሩ ጥያቄዎች ናቸው።

7 አሁንም አንዳንድ ጥሩ፡ የሚያነቃቁ፡ የቤት ጥያቄዎች ብቻ ደርሰውናል። አንድ ሰባኪ አሁን ወደ ኋላ አካባቢ አለ፡ ጠየቀኝ፡ እንዲህ ሲል፡ "በራእይ 11 ላይ የተጠቀሱት ሁለቱ ነቢያት፡ ከንጥቀት በፊት ይመጣሉን? ወይስ እስራኤል ከመወሰዷ በፊት? እና... " አሁን፡ የ—የ—ሚያቀራርባችሁ እንዲህ ዓይነት ጥያቄዎች ናቸው። ነገር ግን እንደነዚህ ያሉት ቀላል ጥያቄዎች ጥሩ ናቸው።

አሁን ግን፡ ከመጀመራችን በፊት፡ ራሳችንን ለጸሎት ዝቅ እናድርግ።

8 አባቴ ሆይ፡ የአስራ ሁለት ዓመት ልጅ ሳለህ፡ በቤተ መቅደስ ውስጥ ካሉት ሊቃውንትና ጠቢባን ጋር፡ ቅዱሳን መጻሕፍትን እየተወያየህ እንደነበር ተጽፏል። በ—በቅዱሳን መጻሕፍት በ... በደንብ የተማሩ፡ የጥንት ሰዎች፡ ምንም እንኳ ታዳጊ ልጅ ቢሆንም ቅዱሳን መጻሕፍትን በ—በማብራራት ሲያስደንቃቸው፡ ሲመለከቱ በጣም ተደነቁ። በአባትህ ጉዳይ ነበርክ። እናትህን እንዲህ አልካት፡ "የአባቴ ሥራ መሰራት እንዳለብኝ አታውቁምን? " ይህም መጽሐፍ ቅዱስን በመንፈሳዊ ትርጉም ለማስረዳት ነው።

9 አሁንም፡ ጌታ ሆይ፡ ም—ምን ያህል ደካሞችና አቅመ ቢሶች እንደሆንን፡ እንዲሁም ለስህተት ምን ያህል የተጋለጥን እንደሆንን በማወቅ፡ ዛሬ ማታ በመንፈስ ቅዱስ መልክ ወደ እኛ እንድትመጣና፡ ቅዱሳት መጻሕፍትን እንድታብራራልን እንጸልያለን። እጠብቅሃለሁ በአንተ ላይም እደገፋለሁ። እኔም በየትኛውም ጊዜ፡ የምገልፀው መንገድ ትክክል እንዲመስል ለማድረግ፡ የራሴን ሀሳብ ወይም፡ ትርጓሜ ወይም የራስ ወዳድ የሆነ ነገር ለማስቀመጥ ከሞከርኩ፡ ዳንኤል ላይ በመጡ ጊዜ፡ በ... በአንበሶቹ ላይ እንዳደረግከው፡ አፌን ዝጋው፡ ጌታ ሆይ። አንተ ያው የሆንክ አምላክ ነህ።

10 ሙሉ በሙሉ ይሁን... በመንፈስ ቅዱስ ላይ የምንመካ እንደመሆናችን መጠን፡ እነዚህን ነገሮች ግለጥልን። እኔም በምናገርበት ጊዜ፡ ጥያቄውን የጠየቀው ሰው መልሱን መቀበል እንዲችል ግልጽ አድርጋቸው። መልሱ ከዚህ በፊት በማምነው መንገድ ተቃራኒ ሆኖ ባገኝም፡ ጌታ ሆይ፡ አዲስ ነገር እንዳገኘሁ በማወቅ፡ የጌታ መልካም መንገድ እንዳገኘው በማወቅ፡ ልቤን ደስ ይበለው። እንዲህ ብለሃልና፡ "በመጻሕፍት የዘላለም ህይወት እንዳላችሁ

ይመስላችኋልና፡ እነርሱን ትመረምራላችሁ፡ እነርሱም ስለእኔ የሚመሰክሩ ናቸው።"

11 አሁን፡ ከዚህ የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት በኋላ፡ ብዙ ሃሳቦች እንደሚነሱ ጥርጥር የለውም። እግዚአብሔር ሆይ፡ እፀልያለሁ፡ አሁን እነዚህ ሁሉ ጥያቄዎች በጣም በገርነትና በእርጋታ የተጠየቁ ይመስላሉ፡ መንፈስ ቅዱስም በገርነትና በእርጋታ ይመልሳቸው። ይህን የምንጠይቀው በኢየሱስ ስም፡ ለእግዚአብሔር ክብርና፡ ለቤተክርስቲያኑ መገንባት ነው። አሜን።

12 ብዙ ጊዜ በማንኛውም ነገር ላይ፡ የራስ ወዳድነት ፍላጎት የነገሮች ጣዕም ያበላሻል። አሁንም፡ ከቅዱሳን ጽሑፎች ጥያቄዎች ቀርበውልናል።

13 አሁን፡ በንግግሬ መሀል የፉጨት መሳይ ድምጽ ከተሰማችሁ፡ ጥርሴ የወለቀበት ቦታ ስላለ ነው። እሱን አስገብቼው፡ መሰበክ አልቻልኩም፡ ስሰብክ አዘገያለሁ፣ ሳወጣውም፡ የፉጨትን ያህል ነው።

14 ወይዘሮ ቢሊ ግራሃም ስለ እሱ አንድ ታሪክ ተናገረች፡ ከፊት በኩል ጥርሱ ተነቅሎ ስታይ፡ ያ፡ በሱ ላይ ካየችው ሁሉ በጣም ያስደነቃት ነገር ነበር። ጥርሱ ወጣና፡ ወድያው የቴሌቪዥን ፕሮግራም ነበረው፡ እ—እና… ሰው ሰራሽ ጥርስ መግጠሚያው ላይ ብዙ የኋላ ጥርሶች ነበሩት። ለመናገር ሲሞክር፡ አፏጩ "ዊኺው፡ ዊኺው" በተነቀለው ጥርስ በኩል ያፏጫል። እሷም እንዲህ አለች ከቴሌቪዥን ሰርጭቱ አሥር ደቂቃ ቀደም ብሎ፡ ተንበርክኮ፡ እየጸለየና እያላበው እንደነበርና፡ በመጨረሻም ከሱሪዎቹ ወድቆ በጫማው ጫፍ ላይ ወደቆ እንዳገኙት ተናገረች። ያንን የውሸት ጥርስ፡ አንድ እንግዳ ተቀባይ አገኘው። ወይዘሮ ቢሊ ግራሃም፡ ስለሱ ይህን ተናግራለች። እና ትንሽ ወረቀት ይዣለው፡ እዚህ መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ያደረኩት ይመስለኛል።

15 ት… ትንሽ በዕድሜ ስንገፋና እቅማችን ሲቀንስ፡ ታውቃላችሁ፡ እነዚህን ማጣት፡ ያ መጥፎ ያደርገዋል። እዚያ ከ… ከወንድም ሮበርሰን ጋር ሳለሁ፡ ከእነርሱም ጋር ሳለሁ፡ አንድ ቀን ጠዋት እየቦረሽኩ ሳለሁ አንድ ቁራጭ ተሰብሮ ወደቀ፡ ወደ ሐኪም ወስጄ፡ እንዲጠገኑት ማድረግ ነበረብኝ። ስለዚህ ጌታ በረከቱን ይጨምር።

16 አሁን እንቀጥላለን፡ አሁን፡ ከቻልኩኝ፡ እያንዳንዳቸውን ጥያቄዎችን ለማየት እሞክራለሁ። እና፡ ወንድም ቶኒ፡ በእግዚአብሔር ጸጋ፡ የሕልምህን ትርጉም ተቀብያለሁ፡ ደግሞም እጅግ ግሩም ነው። ይህን በማየቴ በጣም ደስ ብሎኛል። ጥሩ ትርጓሜ ነው፡ እዚህ በአደባባይ መናገር የለብኝም ብዬ አስባለሁ፡ ስለዚህ በዚህ መንገድ የሚትፈልግ ከ—ከሆነ በ… በግልህ እነግርሃለሁ። ባለፈው ምሽት፡ አንድ ሕልም አይቶ ስለነበር ጠየቀኝ፡ እኔም በጌታ ፊት ቀርቤ ስለ ሕልሙ እስክጸልይ ድረስ ሕልሙ ምን እንደሆነ መናገር አልቻልኩም ነበር። ከዚያም ጌታ መልሶ አሳየኝ ትርጉሙንም ነገረኝ። ወንድም ቶኒ፡ ይህ ለአንተ አስደናቂና፡ መልካም ዜና ነው።

17 አሁን፡ በመጀመሪያው ጥያቄ። አሁን፡ መጀመሪያ ከዬት መጀመር እንዳለብኝ አላውቅም፡ ምክንያቱም ሁሉም ደስ የሚሉ ናቸው። ነገር ግን፡ አሁን፡ በጥያቄዎቹ ብዙ የማንቆይ ከሆነ፡ ብዙ ጊዜ ላለመውሰድ እንሞክራለን፡ ምናልባትም እስከ ቀጣይ እሑድ ልንጨርሳቸው እንችላለን።

**51. በማቴዎስ 25:46 ያለው "የዛላለም ቅጣት፡" ምን ማለት እንደሆነ አብራራው። "ነገር ግን... "** ጥያቄው ይህ ነው።

**52.** በመቀጠል፡ ቀጣዩ ጥያቄው፡ **"ነገር ግን የመንግስት ልጆች ወደ ጨለማው ይጣላሉ፡" ይህ ከእግዚአብሔር ልብ አውጥቶ ከመጣል ጋር ተመሳሳይ ነውን?**

18 ደህና፡ አሁን፡ በቅዱስ ማቴዎስ፡ ምዕራፍ 25፡ የ-... የሚገኘውን የመጀመሪያውን፡ ጥያቄአችሁን እናያለን። አ... አሁን ይህን አጥንቼው፡ አላውቅም፡ ኋላ ተመልክቻቸዋለሁ፡ ከሁሉ አሰበለጨ በ—በድንብ ላያቸው ሞክርያለሁ። መ... መጽሐፍ ቅዱስን ሰናጠና፡ መጽሐፍ ቅዱሳችሁን ከእኔ ጋር አብራችሁ እንብቡ። አሁን፡ ይህን ከግሪክ መዝገበ ቃላት ለማየት ፈልግያለሁ፡ እናንት ኦ—ኦርጅናሉን ከዛ ታገኛላችሁ። ያ—ያንን እወደዋለሁ። ሰለዚህ እኛ በ—በግሪኩም በ—በሌላዉም ይኖረናል። አሁንም ይህ ቀሰ ያ—ያለና፡ በጥናት መልኩ ይሆናል፡ ምክንያቱም ጥቅሶችን በየቦታቸው ለማድረግ ማግኘት ከምችልበት ሁሉ፡ መድረሰና መያዝ አለብኝ። መልካም።

19 አሁን፡ መጽሐፍ ቅዱስን ማጥናት የሚፈልግ አለ? የሚፈልግ ካለ፡ እጁን ያንሳ። እኛም... ሶሰት ወይም አራት መጽሐፍ ቅዱሶች እዚህ አሉ። በጥቅሱ ማጥናት ከፈለጋችሁ፡ እሺ። ወንድም ኮክስ፡ እዚህ መጥተህ እዚህን መጽሐፍ ቅዱሶችን ልታቀብለኝ ትችላለህ? ከ—ከቻልክ፡ ላንተም ጥሩ ነው፡ ለ... (አንድ አለ፡ መውሰድ ከ—ከፈለግክ፡ ሁሉንም ወደዚያ ውሰዳችው)። ሌላ የሚፈልግ ካለ፡ እጁን ያንሳ፡ ልጁ ቀጥታ ወደናንተ ያመጣቸዋል፡ አያችሁ። ይህን አብረን ማጥናት እንፈልጋለን፡ እና...

20 አሁን፡ በዚህ ምንባብና በመጨረሻዎቹ ምዕራፎች... ከዕብራዊያን መጽሐፍ የመጀምሪያዎቹ ሰባት ምዕራፎች። ትምህርቶቹን፡ ካሰትማርኳቸው በኋላ፡ እነዚህን ትምህርቶች፡ እነዚህን ያወረዳቸው ወጣት፡ ወንድም መርሰየርና ወንድም ጎድ፡ ትምህርቶችን በመጽሀፍ መልክ ለማሳተም እያሰተካከሉ ናቸው። ጨርሰውታል። አሁን... በገሚሰ እንደተበጠረ አይነት ሳይሆን፡ ላዩን ብቻ ነካክተነዋል። ከዕብራዊያን ትምህርርት ትንሽ ወርቃማ የ... የሆኑትን ብቻ አ—አውጥተው... እነዛን እያሰተካከሉ ነው፡ ብዬ አሰባለው። ወንድም መርሲየር ለሚፈልጋቸው፡ ለማንኛውም ሰው፡ በህትመት በቅርብ ያዘጋጅላችኋል።

21 አሁን በዚህ ውሰጥ፡ የሚያመጣው... ዝም ብላችሁ ማለፍ አትችሉም... በወንጌላዊት ቤተ ክርሰቲያን፡ ይህችም የወንጌል ቤተ ክርሰቲያን ነች። ጥሪጣሬዎችንና የ—የብዙዎችን ጥያቄ ሳታነሱ በማሰተማር ውሰጥ መግባት አትችሉም። ይህን ማድረግ አለባችሁ። አሁን፡ እኔ ከአሰተማሪነት የራቅኹ ነኝ፡ የመጽሐፍ ቅዱሰ ተንታኝ አይደለሁም። ለዛ ነገር የ—የምችለውን ነገር ሳልጠይቅ፡ ወይም ሳልፈልግ፡ ምንም ነገር ለ—ለመናገር ወይም ለማድረግ ሞክሬ አላውቅም።

22 ትናንት ማታ፡ በአንድ የተወደደ ወንድም ተጠይቄ ነበር፡ እንዲህ አለኝ፡ "ወንድም ብራንሃም፡ ወንድም ሰዋርድ በአንድ ወቅት ሰለ አንተ—መቼም ቢሆን አንተን ማጥመድ እንደማይቻል ተናግሮ ነበር። አየህ፡ ይህም ከነገር ለማምለጥ ወይም ለመሸሽ የሆነ መንገድ እንደማታጣ ነው።"

23 እኔም፡ “መልካም፡ ይሄ የሆነበት ምክንያት፡ ሁልጊዜ ማንኛውንም ነገር ከማድረጌ በፊት ለማሰብ እሞክራለሁ። አየህ? ከዚያም ሰዎች ቢጠይቁኝ፡ ምን አስቤ እንደነበር እነግራቸዋለሁ። አየህ?” ይህ ግን በትክክል ካሰብክ ነው። ማንኛውንም ነገር ከማድረጋችሁ በፊት፡ እግዚአብሔር እንድትመርጡት የሚፈልጋችሁን ምረጡ፡ ያኔ በእርግጥ እናንተን በነገር ማጥመድ የማይቻል ይሆናል።

24 አክዓብ ኤልያስን ለማጥመድ የ—የሞከረበትን ጊዜ መገመት አያዳግታችሁም። ፈሪሳውያን ኢየሱስን ለማጥመድ የሞከሩበትን ጊዜ ትዝ ይላችኋል? አያችሁ፡ መልሱን በ—በፍጥነት ያገኝ ነበር፡ ምክንያቱም የሚያደርጋቸው ነገሮች ሁሉ፡ በእግዚአብሔር ፈቃድ ያደርግ ነበር፡ መ… መልሱንም የሚያገኝበት—መንገድ ያ ነበር። አሁን ደግሞ፡ በዚህ መንገድ ነው የምንፈልገው።

አሁን የተጠየቀው ጥያቄ ይህ ነው፡ ጥያቄውን እንቀጥላለን፡-

**በማቴዎስ 25:46 ላይ “የዘላለም ቅጣት፡” የሚለው ቃል ምን ትርጉም እንዳለው አብራራ።**

25 አሁን በጥሞና አዳምጡ። ሁሉም ሰው አሁን፡ ማቴዎስ 25፡46፡-

**ወደ ዘላለም ቅጣት ይሄዳሉ፡…**

26 አሁን፡ ጥያቄው፡ “ምን… አብራራ…” አሁን everlasting ዘመናት የሚለው ቃል “ዘመን እና ዘመናት፡” ከሚለው ቃል የመጣ ነው፡ ይህ forever ዘመናት ማለትም “የጊዜ ገደብ” ያለው ማለት ነው። ይህ ማለት “በጣም ብዙ ወቅት፡” ልክ እንደ forever ማለት ነው። አሁን ብታነቡት… ጥያቄዎቹን ማን እንደፃፋቸው አላውቅም፡ ምክንያቱም ሰሙን አልጻፈባቸውም፣ መሆንም የለበትም፡ አልፈልጋቸውም፡ አያችሁ።

ነገር ግን **ወደ ዘላለም ቅጣት ይሄዳሉ፡…** (አሁን ይህም፡ ስለ ክፉዎቹ ነው።)

27 አሁን፡ ጥያቄውን የ—የጠየቅከው ውድ ሰው፡ ቀሪውን አንብብ፣

… **ጻድቃን ግን** ወደ **ዘላለም ሕይወት ይሄዳሉ።**

28 “እነዚህም ወደ ብዙ ዘመናት ቅጣት ይሄዳሉ (በተወሰነ የጊዜ ገደብ)፡ ጻድቃን ግን ወደ ዘላለም ሕይወት ይሄዳሉ።” የዘላለም ቅጣት ፈጽሞ አያገኛችሁም፡ ሊሆን አይችልም። አያችሁ፡ ዘላለማዊ ቅጣት ካገኙ፡ ዘላለማዊ ሕይወት አላቸው ማለት ነው፡ ዘላለማዊ ሕይወት ካላቸው ደግሞ፡ ይድናሉ። አያችሁ፡ ይህ ሊሆን አይችልም። አሁን የምትመለከቱት ከሆነ፡ ጥ—ጥያቄው… ራሱ መልስ ይሰጣል። አያችሁ?

**እና እነዚህ…**

አሁን ተመልከቱ፡ አመጣቸዋለሁ፡

… **እነርሱም**…

29 በ20ኛው ውስጥ… 44ተኛው ቁጥር፡

… **ጻድቃንም** መልሰው፡ ይሉታል፡ **ጌታ ሆይ፡ ተርበህ አይተን** መቼ አበላንህስ፡ ወይስ **ተጠምተህ** አይተን መቼ አጠጣንህ፡

**እንግዳ ሆነህስ፡** ወይስ **ታርዘህ፡... ወይስ ታሰረህ አይተን መቼ አላገለግልንህም?**

**እርሱም—እንዲህ ይመልስላቸዋል፡ ይላቸዋልም፡ እውነት እላችኋለሁ፡ ከሁሉ ከሚያንሱ... ከእነዚህ** ለአንዱ እንኳ ስላደረጋችሁት... ለእኔ፡ **አደረጋችሁት ይላቸዋል።**

**እነዚያም ወደ** (ዘመናት) **ቅጣት ይሄዳሉ፡** (እነዛ ክፉዎቹ ናቸው)... **ጻድቃን ግን ወደ** ዘላለም ሕይወት ይሄዳሉ።

30 ልዩነቱን አያችሁ? ክፉዎች የብዙ ዘመን ቅጣት አላቸው፡ ነገር ግን **ዘመናት** ማለት "የጊዜ ገደብ ነው።" አሁን፡ ተመሳሳይ ቢሆን ኖሮ፡ ይጻፍ ነበር፡ "እነዚህም ወደ ዘመናት ቅጣት ይሄዳሉ፡ ሌሎቹም ወደ ዘላለም ሕይወት ይሄዳሉ።" አያችሁ? ወይም፡ "እነርሱ ወደ ዘለአለማዊ ቅጣት፡ ሌሎቹ ደግሞ ወደ ዘለአለማዊ ሕይወት ይሄዳሉ።" አያችሁ፡ የዘላለም ቅጣት ካለ፡ ለዘለአለም እና ለዘለአለም የሚቀጣ ከሆነ፡ ይህ ማለት የ... የዘላለም ሕይወት አለው ማለት ነው፥ የዘላለም ሕይወት ግን አንድ አለ፡ ያም የሚመጣው ከእግዚአብሔር ነው። መጀመሪያ የሌለው ነገር ሁሉ መጨረሻ የለውም፡ መጀመሪያ ያለው ነገር ሁሉ መጨረሻ አለው። ምን ማለቴ እንደሆነ አያችሁ?

31 አሁን፡ ቅዱሳት መጻሕፍት ራሳቸው—የተወደደው ሰው ሲመልስ... አሁን በመዝገበ ቃላት ላይ ካያችሁ፡ **"እነዚህ ተቆርጠው፡ ወደ ዘመነ ዘመናት ቅጣት ይሄዳሉ፡ ወደ ዘመናት-... እሳት፡ ወደ እሳት ባሕር።"** አሁን፡ a-i-n-i-o-n የሚለው ቃል "የቅጣት ወቅት" ማለት ነው። በግሪክ መዝገበ ቃላት ውስጥ፡ እዚህ ላይ፡ "የቅጣት ወቅት፡" ወይም፡ "የቅጣት ጊዜ" ይላል። አያችሁ፡ "ወደ ቅጣት ጊዜ ይሄዳሉ" ማለት ነው። a-i-n-i-o-n የሚለውን ቃል፡ ተጠቅሟል። **አንዮን**፡ ትርጉሙም "ጊዜያት፡ ጊዜ፡ የተወሰነ ጊዜ" ማለት ነው። እንግዲያውስ የ—የእንግሊዘኛ፡ ትርጓሜውን እንውሰድ፡ everlasting ማለት "የተወሰነ ጊዜ" ማለት ነው። አያችሁ፡ ከግሪክኛ የመጣው፡ "የጊዜ ገደብ" የሚል ነው። **አኒዮን**፡ ወይም a-i-n-i-o-n፡ **አኒዮን** የሚለው ቃል "ለተወሰነ ጊዜ የሚሰጥ ቅጣት" ማለት ነው።

32 ነገር ግን ሌሎቹንም አንብቡ፡ "እነዚህ ግን ወደ ዘለዓለም ህይወት ይገባሉ።" ይህ ነው ልዩነቱ። አያችሁ፡ የዘላለም ሕይወት። Eternal ማለት ዘላለማዊ የሚለው ቃል የመጣው "ከዘላለማዊነት" ሲሆን፡ ዘላለማዊነት መጀመሪያም መጨረሻም የለውም። ለዘመናት **እና** ለዘመናት ነው። አሁን ይህ ያንን ይመልሰዋል፡ አያችሁ፡ መጽሐፍ ቅዱስ በትኩረት ካነበባችሁ፡ ታዩታላችሁ።

33 **"እነዚህም ወደ ዘመናት ቅጣት ይሄዳሉ፡ ጻድቃን ግን... "** ኃጢአተኞች ወደ ዘመናት ቅጣት ይሄዳሉ፡ ለተወሰነ ጊዜ ይቀጣሉ፡ ምናልባትም ቢሊዮን ዓመታት፡ አላውቅም፡ ግን በእርግጠኝነት ለኃጢአታችሁ ትቀጣላችሁ። የኃጢአት መጀመሪያ እንዳለው፡ መጨረሻ አለው። ቅጣት ደግሞ መጀመሪያ አለው፡ መጨረሻም አለው። ሲኦልም የተፈጠረው ለዲያብሎስና ለመላእክቶቹ ነው። አያችሁ? መልካም። አሁን፡ እዚህ መልስ መስጠት ያለብኝ ሌላ ጥያቄ አለኝ፡ በጥቂት ደቂቃዎች ውስጥ እመልሳለሁ፡ ይህም እጅግ ቆንጆ ጥያቄ ነው፡ አዳምጡት።

**አሁን፡ ይሄ ግን እዚህ፡ “የመንግሥቱ ልጆች ግን ወደ ጨለማ ይጣላሉ፡” ታዲያ ይህ ማለት አምላክ እነሱን ከልቡ አውጥቷቸዋል ማለት ጋር የሚመሳሰል ነውን?**

34 አይደለም፡ ተመሳሳይ አይሆንም። አሁን፡ ስለ ሠርጉ እራት እየጠቀሳችሁ ነው። አሁን፡ “የመንግሥቱ ልጆች፡” እዚህ ላይ እንደተጠየቀው። የመንግሥት ልጆች የሆኑት አይሁዳውያን ናቸው፡ እነሱ ግን ወደ ውጭ ወደ ጨለማ ተጥለው ቆይቷል። እና እነዚህ—ወደ ውጭው ጨለማ ተጥለው ነበር፡ በልቅሶና በዋይታና ጥርስ በማፋጨት ጊዜ አልፈዋል። አንተም ሆንክ እኔ ንስሐ ለመግባት የሚያስችል አጋጣሚ እንድናገኝ ሲባል ወደ ውጭ ጨለማ ተጥለዋል፡ ከእግዚአብሔር ልብ ግን በጭራሽ አልተጣሉም። እርሱ እስራኤልን መቼም ብሆን አይረሳም። እስራኤል ደግሞ፡ ማንኛውም የመጽሐፍ ቅዱስ አንባቢ እንደሚያውቀው፡ “የመንግሥቱ ልጆች” ተብለው ተጠቅሰዋል። አያችሁ፡ መንግሥቱ ነው፡ የተሰፋው ቃል ነው። በሌላ አነጋገር፡ እግዚአብሔር ከእስራኤል ጋር ሲነጋገር፡ ከሕዝቡ ጋር ይነጋገራል፡ የመንግስቱ ልጆች ከሆኑት ጋር።

35 አሁን፡ አስታውሱ፡ እዚያ እንዲህ ብሏል፡ “አብርሃምና ይስሐቅና ያዕቆብ፡” በአንድ ቦታ፡ “በመጨረሻው ዘመን መጥተው በመንግሥቱ ይቀመጣሉ።” አያችሁ፡ አብርሃም፡ ይስሐቅ እና ያዕቆብ በመንግሥቱ ውስጥ ይሆናሉ፡ እነሱ የመንግሥቱ፡ በረከት ሰዎች ነበሩ። የመንግሥቱ ልጆች ግን ወደ ውጭ ወደ ጨለማ ይጣላሉ።

36 አሁን፡ ሃሳቡ የሚመጣው ከ—ከሙሽራው ነው። ሙሽራው ሲመጣ፡ እነርሱ... አምስቱ ደናግል ጌታን ለመቀበል ወጡ፡ በ—በመብራታቸው ግን ዘይት አልያዙም። ሌሎቹም አምስቱ በ—በመብራታቸው ዘይት ይዘዋል። አሁን፡ ልብ ካላችሁ፡ ይህ አይሁድም አሕዛብም ሁለቱ፡ የተጣሉበት፡ ውብ ተምሣሌት ነው። ሁልጊዜ ሦስት ዓይነት ሕዝብ እንዳሉ፡ አስታውሱ፥ አይሁድ፡ አሕዛብ (መደበኞቹ)፡... ፣ አይሁድ፡ አሕዛብና፡ ቤተ ክርስቲያን። እነዚህን ከቀላቀላችሁ፡ ራዕይ ስትደርሱ ችግር ውስጥ ትወድቃላችሁ። ስለዚህ...

37 ሚስተር ቦሃኖን አንድ ጊዜ እንዲህ እንዳለኝ፡ እንዲህ አለኝ፡ “ቢሊ፡ ራዕይን ለማንበብ የሚሞክር ማንኛውም ሰው ያቃዠዋል። ለምን፡” እንዲህ አለኝ፡ “እነሆ ሙሽራዋ እዚህ ምድር ላይ ናት፡ ዘንዶውም ከ—ከእሷ ጋር ለመዋጋት ከአፉ ውኃ ያፈሳል።” አለኝም፡ “ከዚያም በተመሳሳይ ጊዜ ሙሽራዋ እንደ መቶ አርባ-አራት ሺህ ሆና ትቆማለች” (የጀሆቫ ዊትነሶች ትምህርት) “በሲና ተራራ ቆማለች። በተመሳሳይ ጊዜ መሽሪቷ በሰማይ ናት” አለ። አይ፡ አይ፡ ተሳስተሃል።

38 ሦስት ዓይነት ህዝብ አለ። አያችሁ፡ ይህም፡ የተቆረጡት አይሁድ፡ በተጨማሪ ደግሞ ሰነፏ ደናግል ይህ ማለት ውኖች... የሴትቱ ዘር አይደሉም፡ ዘንዶው ከአፉ ውኃ ያፈሰሰባት የሴቲቱ ዘር ሳይሆኑ የሴቲቱ ዘር ቅሪቶች ናቸው... ራዕይ 11። እንዲሁም፡ በእርግጥ፡ መቶ አርባ-አራት ሺህዎቹ አይሁዳውያንም ሙሽራይቱ አይደሉም፡ እነርሱ የአይሁድ ቤተ ክርስቲያን ቅሪቶች ናቸው። በጂሆቫ ዊትነሶች ትምህርት ሙሽራ አድርገው ያስቀምጧታል፡ ይህን ማድረግ የሚችሉት እንዴት እንደሆነ አልገባኝም፡ ምክንያቱም፡ ሙሽሪት አይደሉም።

39 በራእይ ላይ እንደተገለጸው ካስተዋላችሁ፡ “ድንግሎችም ናቸው፡” ይላቸዋል። ጃንደረቦች ናቸው። ጃንደረቦች ምንድናቸው? ምን ነበሩ... ጃንደረቦች የመቅደስ ጠባቂዎች ንግሥቲቱን የሚጠብቁ ናቸው፡ ምክንያቱም... እ-... እነዚህ ሰዎች መካን እንዲሆኑ የተደረጉ ናቸው። ያልረከሱ... ይህን አስተውላችኋል፡ እንዲህ ብሏል፡ “ከሴቶች ጋር ራሳቸውን አላረከሱም”? ቤተ መቅደሱ ውስጥ የነበሩ ጃንደረቦች ናቸው። እነዚህም እግዚአብሔር ከአይሁዳውያን መካከል የመረጣቸው የተመረጡ ሰዎች ነበሩ። አሁን፡ ካስተዋላችሁ... በትንሽ ጊዜ ውስጥ ካየነው፡ ስለዚህ አዕምሯችሁ ውስጥ ይቀመጣል፡ በእርግጠኝነት...

40 የዮሐንስ ራዕይ፡ ምዕራፍ 7ን እንይ፡ ምን እንደተባለ፡ እዚህ... እናያለን። በጣም የሚያምር ነገር ነው።

> **ከዚህም** በ... **በኋላ በአራቱ በምድር ማዕዘን ቆመው አራት መላእክት አየሁ...** (አሁን ይህ በሕዝቅኤል 9 ላይ፡ አይሁዳውያን ሲጠፉ ያየበትን ክፍል ያመሳሰለዋል። እዚህ ላይ ደግሞ የአሕዛብን ጥፋት ይመለከታል፡ ራእይ፡ ምዕራፍ 7) ... ከዚህም **በኋላ በአራቱ በምድር ማዕዘን ቆመው አራት መላእክት አየሁ፡ አራቱን የምድር ነፋሳትን ያዙ** (**ንፋሳት** ማለት “ጦርነት እና ግጭት ማለት ነው”) ... **ይህም** ንፋሱ **በምድር** ላይ፡ **ወይም በባህር፡... ላይ** ወይም በማንም ዛፍ ላይ **እንዳይነፍስ አራቱን የምድር ነፋሳት ያዙ።** (ያ ጦርነት ነው፡ “መያዝ”)

41 ኦህ፡ በዚህ ጉዳይ ላይ በዝርዝር ለመወያየት ጊዜ ቢኖረን ደስ ይለኛል። ይህ ሲሆን... ሩሰል የቀላቀለበት ቦታ ይኸው ነው። ሩሰል ይህን አስቀድሞ በመገመት፡ ትንቢት ተናግሯል። “ጌታ ኢየሱስ እንደሚመጣ” ትንቢት ተናግሯል፡ ቤተ ክርስቲያኒቷ መ—መታተሟን ሳያውቅ ነበር። አያችሁ?

42 እና አንደኛው የዓለም ጦርነት... እንዴት እንደቆመ ጥያቄ ይፈጥርባቸዋል። ይኸውላችሁ፡ ሐምሌ አስራ አንድ፡ በአስራ አንድ ሰአት ነው የቆመው፣ አሥራ አንደኛው ወር፡ ዐሥራ አንደኛው ቀን፡ ዐሥራ አንደኛው ሰዓት። ከዚያም በኋላ ወዲያውኑ፡ በኢየሱስ ስም የውኃ ጥምቀት እና የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት ለቤተክርስቲያን ተገለጠ። በትክክል፡ ከዚያ በኋላ ወዲያውኑ ተገለጠ።

43 በራዕይ ላይ ከተመለከታችሁት፡ በፊላዴልፊያ ዘመንና፡ በሎዶቅያ ዘመን መካከል እንዴት እንዳስተሳሰርነው ከተመለከታችሁ ታገኙታላችሁ። የፊላደልፊያ ዘመን የሜቶዲስቶች ዘመን ነው፡ የወንድማማችነት መዋደድ የተባለው። የመጨረሻው ዘመን፡ የቤተክርስቲያን ዘመን፡ የሎዶቅያ ዘመን ነው፡ ይህም ለብ ያለ ዘመን ነው። እዚያ ላይ፡ “እነሆ የተከፈተ ደጅ (የተከፈተ በር) በፊትህ አድርግያለው” ብሏል። የተከፈተ በር! በትክክል እናንተን ለማሳየት፡ እነዚህን ጥቅሶች ወደ ኋላ ብትመለከቷቸው፡ መላውን መልዕክት በትክክል ወደ አንድ ቦታ ያገናኘዋል።

44 ተመልከቱ! እዚህ ጋር በጥምቀት ላይ፡ ሁሉም ነገር በአባት፡ በልጅ፡ በመንፈስ ቅዱስ ስም ሆኖ ቆየ፡ (በቀጥታ ወደ እዛ ውስጥ እንገባለን) ይህም በፍፁም የካቶሊክ እምነት እንጂ የክርስትና ትምህርት አልነበረም። አይደለም፡ ወዳጄ። እንግዲህ... ዛሬ ማታ፡ እዚህ እናወራዋለን፡ ዘልቀን እናያለን፣ መዝገበ

ቃላትን በመጠቀም ጭምር፡ እናየዋለን። አያችሁ? አዎን፡ ወዳጄ፡ በታሪክም ጭምር። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ወይም ከመጽሐፍ ቅዱስ በኋላ በነበሩት፡ የመጀመሪያዎቹ ስድስት መቶ ዓመታት ውስጥ ማንም ሰው እንደዚህ ተጠምቆ አያውቅም። በካቶሊክ በራሷ አስተምህሮ ላረጋግጥላችሁ እችላለሁ፡ ይህን የጀመሩት እነርሱ ናቸው፡ መርጨትና ማፍሰስ።

45 ከዚያ ወደ ዌስሊያን ቤተ ክርስቲያን፡ ወደ ሜቶዲስት ቤተ ክርስቲያን፡ ከሜቶዲስት ወደ ባፕቲስት፡ ባፕቲስት ወደ ሌላ ቤተ ክርስቲያን ይዘውት መጡ፡ አሁንም ቢሆን የሐሰት ትምህርት ነው! በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ አሳይቺ መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ እንዳለ ላረጋግጥላችሁ እችላለሁ "ሕያው እንደ መሆንህ ስም አለህ፡ ሞተህማል።" ይህ ትክክል ነው። እነርሱም...

46 በቤተክርስቲያን ዘመን ማለትም በጴርጋሞስ የቤተክርስቲያን ዘመን አራተኛው ዘመን እስከሚመጣበት የጨለማው ዘመን ድረስ፡ ሰሙን ለ—ለጥምቀት እንደሚጠቀሙ... መጽሐፍ ቅዱስ እ—እንደሚያስተምር፡ ላረጋግጥላችሁ እችላለሁ። እርሱም እንዲህ አለ፡ በዚያ፡ የጨለማ ዘመን በአስራ አምስት መቶ ዓመታት ውስጥ፡ በሁሉም፡ እንዲህ ብሏል፡ "ጥቂት ብርሃን አለህ፡ ምክንያቱም ሰሜን አልካድህምና።"

47 ወደዚያ ሌላ ዘመን ሲመጣ፡ ወደ ካቶሊክ ዘመን፡ እንዲህ አለ፡ "'ሕያው' እንደ መሆንህ ስም አለህ፡ ሞተህማል! ስሜንም ክደሃል።" ይሄው። አያችሁ? ይህ ሁሉ አንድ ትልቅ ውብ ምስል አንድ ላይ ያገናኛል፡ መላው መጽሐፍ ቅዱስን።

48 አሁን ይህንን አስተውሉ፡

> **... አራቱን ነፍሶች መያዝ...**
>
> **የሕያው እግዚአብሔር ማኅተም ያለው፡ ሌላም መልአክ** ከሰማይ **ሲወጣ አየሁ...** (ማህተም)

49 አሁን፡ የሕያው እግዚአብሔር ማኅተም ምንድን ነው? አሁን፡ እናንተ የአድቬንት ወንድሞች፡ "ሰንበትን መጠበቅ ነው" ትላላችሁ። ከመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ጥቅሱን እንድታሳዩኝ እፈልጋለሁ። በዚያ የለም። አንድም ቦታ የ... የ— የለም...

50 ኤፌሶን 4:30ን፡ በፍጥነት፡ ብታነቡ የህያው የእግዚአብሔር ማህተም ምን እንደሆነ ታውቁታላችሁ። ኤፌሶን 4:30 እንዲህ ይላል፡ "እስከ ቤዛችሁ ቀን ድረስ የታተማችሁበትን የእግዚአብሔርን ቅዱስ መንፈስ አታሳዝኑ።" እስከሚቀጥለው ሪቫይቫል ድረስ ሳይሆን ዘላለማዊ ደህንነት እስክታገኙ ድረስ (ኡህ-ሁህ)። "እስከ ቤዛችሁ ቀን ድረስ የታተማችሁበትን የእግዚአብሔርን ቅዱስ መንፈስ አታሳዝኑ።" ኤፌሶን 4:30 እንደዛ የማይል ከሆነ ተመልከቱ፡ የቀረውን ለማወቅ በራሳችሁ ንባብ ቀጥሉና ፍለጋችሁን በመጽሃፍ ቅዱስ በኩል አድርጉና፡ አግኙ። አሁን፡ "እስከ ቤዛችሁ ቀን ድረስ ታትማችኋል። የህያው የእግዚአብሔር ማህተም ተቀበላችሁ።

51 አሁን፡ አስታውሱ፡ እስከ 1ኛ የዓለም ጦርነት ድረስ መንፈስ ቅዱስ እንደ መንፈስ ቅዱስ ጥምቀት አልታሰበም ነበር። ወርቃማው ኢዮቤልዩ

በ—በዓላችንን፡ አርባ አመት፡ ወይም የአርበኛ አመት ኢዮቤልዩን እንዲሁ እናከብራለን።

> ... **ምድርን** ወይም **ባሕርን ሊጐዱ ለተሰጣቸው ለአራቱ መላእክት፡ በታላቅ ድምፅ እየጮኸ፡**
>
> **የአምላካችንን ባሪያዎች፡ ግምባራቸውን እስክናትማቸው** ድረስ **ምድርን ቢሆን፡ ወይም ባሕርን፡** ወይም ዛፎችን፡ **አትጉዱ አላቸው...** (አሁን ወደ ጥያቄያችሁ እየሄዳችሁ ነው፡ "**ልጆችን፡**" አያችሁ)... **የአምላካችን እግዚአብሔር ባሪያዎች** ግምባራቸውን። (አትጉዱ፡ ምድርን አታጥፉ፡ የአቶሚክ ቦምብ አታፈንዱ፡ የአምላካችን **ባርያዎች** እስኪታተሙ ድረስ የተሟላ ነገር አይኖረንም)

52 አሁን፡ ወደዚያ ወደ ኋላ ተመልሰን ብንመለከት፡ **ሁለተኛ የአለም ጦርነት** እ—እንዴት **እንደቆመ፡** በሁለተኛው ዕትም እንኳ ብናይ፡ ጄኔራል አሌንቢ በኢየሩሳሌም ዳርቻዎች ላይ እስኪደርስ ድረስ በተዋጋ ጊዜ፡ ወደ እንግሊዝ ንጉስ መልእክት ሰደደ፡ እና እንዲህ አለ፡ "በከተማይቱ ቅድስና ምክንያት፡ በከተማይቱ ላይ መተኮስ አልፈልግም።" እርሱም፡ "ምን ማድረግ አለብኝ?" አለ

53 እሱም፡ "ጸልይ" አለው።

54 እንደገና ከላይዋ በረረ፡ በበረሩ ጊዜም፡ "አሌንቢ እየመጣ ነው፡" አሉ። በዚያም ሞሃመዳዊያን ሰለ ነበሩ፡ "አላህ እየመጣ ነው፡" ብለው አሰቡ። ነጩን ባንዲራ ከፍ አድረጉና ተማረኩ አሌንቢም ወደ ኢየሩሳሌም ሄደና እንደተነገረው ትንቢት፡ አንድም ጥይት ሳይተኩስ ገባ፡ እውነት ነው፡ ወደ አይሁዶችም መለሰላቸው።

55 ከዚያም በመላው ዓለም፡ አይሁዶችን ለማሳደድ ሂትለርን አስነሱና፡ ወደዚያ እንዲመለሱ አደረጋቸው።

56 መጽሐፍ ቅዱሰም "በንስር ክንፍ ይመልሳቸዋል" ይላል። ተመልሰው መምጣት ሲጀምሩ... **ላይፍ** መጽሔት እና ሌሎች የዜና ማሰራጫዎች በቅርቡ ከጥቂት ሳምንታት በፊት ታሪኩን ዘግበው ነበር፡ በሺዎች የሚቆጠሩ ሰዎችን፡ ወደ ኢየሩሳሌም ሰመልሱ፡ አረጋውያንን በጀርባዎቻቸው ላይ አዝለው ነው የተመለሱት። ቃለ መጠይቅ ተደረገላቸው። ሁሉንም ነገር በተንቀሳቃሽ እና በፎቶግራፍ ይዣለሁ። እርሱም... በዚያም ባለ-አራት ኮከብ፡ የዳዊት ባንዲራ ተንጠልጥሎ ነበር፣ በዓለም ላይ እጅግ ጥንታዊ የሆነው፡ ባንዲራ ከሁለት ሺህ ዓመታት ወዲህ ለመጀመሪያ ጊዜ ተውለበለበ።

57 ኢየሱስ ሲናገር፡ "የበለስ ዛፍ ቡቃያውን እስኪያወጣ ድረስ፡ ይህ ትውልድ አያልፍም" ብሏል።

58 እነሆም ሸማግሌዎችን ሲያሰገቧቸው፡ እንዲህ ይሏቸው ነበር፡ "ምነው? የምትመለሱት በሃገር ቤት ለመሞት ነው?"

59 እነርሱም፡ "አይደለም፡ እኛ የመጣነው መሲሁን ለማየት ነው።"

60 ሰለዚህ፡ ወንድሜ ሆይ፡ እነግርሃለሁ፡ እነሆ በደጅ ነን! ባርያዎች ማለት እነዚህ ናቸው፡ በዚያ ማዶ እየጠበቁ ይገኛሉ። ቢችሉ ሰው ሰራሽ ጥርሶቻችሁን

ሊሰርቋችሁ ስለሚችሉ ስለእነዚህ የአይሁድ መንጎች አላለም፡ ስለነዚያ አይሁድ አይደለም እየተናገረ ያለው። ነገር ግን እነዚህ ህጎችን እና ነገሮችን የ—የሚጠብቁና፡ መሲሕ መምጣቱን እንኳ ላልተገነዘቡት ነው።

61 እና ወንድም... ወንድም ፔትሩስ፡ ከሰቶክሆልም፡ አንድ ሚሊዮን አዲስ ኪዳን መጽሐፍቶችን ላከላቸው፡ እነሱም ተቀብለው እያነበቡት ነበር። እነርሱም "እንግዲህ፡ ይህ መሲሁ ከሆነ፡ የነቢይን ምልክት ሲያደርግ እንየውና፡ እናምነዋለን፡" አሉ።

62 ለአገልግሎቴ የሚሆን ድንቅ ቅንጅት ነው! ወደ ኢየሩሳሌም ለመግባት፡ ከሁለት ሰዓት ባነሰ ጊዜ ውስጥ ነበርኩ፡ በግብፅ፡ ካይሮ ውስጥ ነበርኩ። በዚያም እየሄድኩ ነበርና፡ መንፈስ ቅዱስ፡ "አሁን አትሂድ አለኝ።"

63 እንዲህ አሰብኩ፡ "በምናቤ እያሰብኩ ነበር። ቲኬቴ ቆርጪያለው፡ ጉዞ ላይ ነኝ። ሰውዬው፡ መላውን ቡድን፡ ትምህርት ቤቶችን እና የመሳሰሉት ሊያገኙኝ ተሰብሰበዋል።"

64 ትንሽ እንደተራመድኩ፡ መንፈስ ቅዱስ እንዲህ አለኝ፡ "እንዳትሄድ! አትሄድም።"

65 ወደ ቲኬቱ ወኪል ተመለስኩና፡ እንዲህ አልኩት፡ "ይህን ቲኬት ሰርዤዋለሁ። ወደ አቴንስ፡ ግሪክ፡ ወደ ማርስ ሂል መሄድ እፈልጋለሁ።

66 እርሱም "እንግዲህ፡ ትኬቱ ወደ እየሩሳሌም ይላል፡ ጌታዬ፡" አለኝ።

67 እኔም፡ "እየሩሳሌም በመሄድ ፈንታ ወደ አቴንስ መሄድ እፈልጋለሁ" አልኩት። መንፈስ ቅዱስ ገና እየጠበቀ ነው፡ ሰዓቱ አልደረሰም። ትክክል አይደለም።

68 ተመልከቱ፡

> ... **የአምላካችንን ባሪያዎች** ግምባራቸውን **እስክናትማቸው ድረስ፡**
>
> **የአምላካችንን ባሪያዎች፡** ግምባራቸውን... **እስክናትማቸው... ድረስ ምድርን አትጉዱ አላቸው።** (ያ የመንፈስ ቅዱስ ማህተም እንደሆነ ማንም ሰው ያውቃል፣ ተመልከቱ)
>
> **የታተሙትንም ቍጥር ሰማሁ፡...** (አሁን፡ አይሁድ ካልሆኑ፡ ተመልከቱ) ... **ከእስራኤል ልጆች ነገድ** ሁሉ **የታተሙት መቶ** አርባ-አራት **ሺህ ነበሩ።** (በእነርሱ ውስጥ አህዛብ የለም። ያ በመጨረሻው ዘመን ነው)

69 ተመልከቱ! ከይሁዳ ነገድ፡ አሥራ ሁለት ሺህ፡ ከሮቤል ነገድ፡ አሥራ ሁለት ሺህ፡ ሲቀጥል፡ ከጋድ ነገድ፡ አሥራ ሁለት ሺህ፣ ከአሴር ነገድ አሥራ ሁለት ሺህ፡ ከ—ከ—ከንፍታሌም ነገድ አሥራ ሁለት ሺህ፡ እ—እና ዛብሎን፡ ከአስራ ሁለቱም እስራኤል ነገዶች። አስራ ሁለት ጊዜ አስራ ሁለት ስንት ነው? መቶ አርባ-አራት ሺህ። መቶ አርባ-አራት ሺህ፡ አይሁዶች እነዚህ ናቸው! አህዛብ አይደሉም፡ አይሁድ ናቸው! ከሙሽሪት ጋር የሚያገናኛው ነገር የለም። ስለዚህ ጂሆቫ ዊትነሶች በአስተምሮታቸው ስህተት ናቸው። መጽሐፍ ቅዱስ በግልጽ "አይሁድ፡" ናቸው ይላል እንጂ አህዛብ ናቸው አይልም። እነርሱ የእግዚአብሔር

ባሪያዎች ናቸው፡ አህዛብ በፍጹም እንደ ባሪያ ተቆጥሮ አያውቅም። እኛ ወንድ ልጆቹ እኛ ሴት ልጆች እንጂ፡ ባሪያዎቹ አይደለምም።

70 አሁን ቀሪዎቹን እንብቡ። ሃባብ እየበላ፡ "ጨምረን እንብላ እንጂ፡ ጥሩ ነው፡" እናዳለው ሰውዬ ነው። መልካም፡ እዚህ ጋር እግዚአብሔር በቂ አለው። አሁን፡ አስተውሉ። አሁን፡ አሁን 8ኛው ቁጥር ላይ ነን፡

> **ከዛብሎን ነገድ... አሥራ ሁለት ሺህ** ታተሙ። **ከዮሴፍ ነገድ** ሁሉ **አሥራ ሁለት ሺህ ታተሙ። ከብንያም ነገድ አሥራ ሁለት ሺህ ታተሙ።**

71 አያችሁ፡ ዮሐንስ፡ አይሁዳዊ ስለሆነ፡ እያንዳንዳቸውን አውቋቸዋል፡ አስራ ሁለቱ የእስራኤል ነገዶችን አይቷቸዋል፥ አስራ ሁለቱንም የእስራኤል ነገሮችን፡ አስራ ሁለት ጊዜ አስራ ሁለት መቶ አርባ-አራት ሺህ ነው። እነርሱ ናቸው፡ ቤተክርስቲያን አይደሉችም፡ አይሁዶች ናቸው። መጽሐፍ ቅዱስ እዚህ፡ ሁሉም "የእስራኤል ልጆች" ናቸው ይላል፡ እያንዳንዱ ነገድ ተሰይሟል።

72 አሁን፡ 9ኛ ቁጥር ተመልከቱ፡

> **ከዚህ በኋላ** (አሁን እዚህጋ ሙሽሪት ትመጣለች)...
>
> **ከዚህ በኋላ አየሁ፡... እነሆም፡ አንድ እንኳ ሊቆጥራቸው የማይችል፡ ብዙ ህዝብ፡...**

73 የቤተ መቅደሱ ጃንደረቦች፡ አንድ መቶ አርባ-አራት ሺህ ብቻ ናቸው፡ ትንሽ ብቻ ናቸው፡ ጥቂት የቤተ መቅደስ ጠባቂዎች፡ ከሙሽራይቱ ጋር የሚሆኑ የእርሷ፣ አ—አጃቢዎች ብቻ ናቸው። አንድ መቶ አርባ-አራት ሺህዎች፡ የሙሽሪት አጃቢዎች ናቸው፡ የቤተመቅደስ ጃንደረቦች ናቸው።

74 ተመልከቱ! እርግጥ ነው፡ ወደ 14ኛው ቁጥር እንደምትመለሱ አውቃለሁ፡ እንዲሁም "ለምን፡ ከሙሽሪት ጋር ናቸው... " ትላላችሁ፡ በፍጹም! ጃንደረቦች ከንግስቲቱ ጋር በሄደችበት ሁሉ ይጓዛሉ። በትክክል! ግን ምን ነበሩ? ምንም አይደሉም አጃቢዎች ናቸው፡ በትክክል መጽሐፍ ቅዱስ እዚህ የሚናገረው ይህን ነው።

75 አስተውሉ፡

> **ከዚህ በኋላ አየሁ... እነሆም፡ አንድ እንኳ፡ ሊቆጥራቸው፡ የማይችል፡ ከሕዝብና፡... ከነገድ፡... ከወገንም ከቋንቋም፡...** ብዙ ሰዎች ነበሩ (እኖኋት የአህዛብ ሙሽሪታችሁ ሰትመጣ፡ መልካም) ... በዙፋኑና **በበጉ... ፊት ቆሙ፡** (ይሄው አዳኛቸው፡ በጉ፡ ህግ አይደለም፣ በጉ ነው፡ ጸጋ) ... **ነጭ ልብሰም ለብሰው፡...** (ተመልከቱ፡ በትንሽ ደቂቃ ውሰጥ፡ ነጭ ልብሰ የቅዱሳን ልብሰ ካልሆነ ተመልከቱ)... **የዘንባባንም ዝንጣፊዎች በእጆቻቸው ይዘው፥**
>
> **በታላቅም ድምፅ እየጮሁ፡**... (ይህ የጴንጤቆሰጤ ሪቫይቫል ካልሆነ፡ ምንም አልሰማሁም ማለት ነው)... **እንዲህ አሉ፡ በዙፋኑ ላይ** ለተቀመጠው **ለአምላካችንና፡ ለበጉ ማዳን ነው አሉ።**

**መላእክቱም ሁሉ በዙፋኑና፡ በሽማግሌዎቹ በአራቱም እንስሶቹ** ዙሪያ **ቆመው፡... ነበር... በዙፋኑም ፊት በግምባራቸው ተደፉ፡ ለእግዚአብሔርም እየሰገዱ፡**

**እንዲህ አሉ፡ አሜን፡ በረከትና፡... ክብር፡... ጥበብም፡... ምስጋናም ውዳሴም፡...** ኃይልም፡... **ብርታትም፡** ከዘላለም፡ **እስከ ዘላለም ድረስ ለአምላካችን ይሁን። አሜን አሉ።**

76 የካምፕ ስብሰባ ጊዜ ይመስላል፡ አይደል? እንዲህ ይሆናል! እነዚህ ማን ነበሩ? መቶ አርባ-አራት ሺህዎቹ ናቸውን? ፈጽሞ አይደሉም! እነሆም አንድ እንኳ ሊቆጥራቸው የማይችል... ከሕዝብና፡ ከነገድ፡ ከወገንም ከቋንቋም ነበሩ። አይታያችሁም፡ የተወደዳችሁ ወዳጆቼ?

77 አሁን ተመልከቱ፡ አንብቡት። አሁን፡

**ከሽማግሌዎቹም አንዱ ተመልሶ፡ እንዲህ አለኝ፡ እነዚህ ነጩን ልብስ የለበሱ... እነማን ናቸው? ከወዴትስ** መጡ?

78 አይሁዳዊ የሆነው መቶ አርባ-አራት ሺህ ያወቀው ሽማግሌውም፡ ዮሐንስን፡ "አሁን፡ ታውቃለህ፡ እነዚህ ሁሉ አይሁድ ናቸው። ነገር ግን እነዚህ እነማን ናቸው? ከወዴትስ መጡ፡" አለው? ሽማግለው ምን እንዳለ አያችሁ? "ከሽማግሌዎቹም አንዱ መልሶ፡" (ከዙፋን ፊት የነበረ ሽማግሌ ነው) "ተመልሶ፡ እንዲህ አለ፡ 'እነዚህ ነጩን ልብስ የለበሱ እነማን ናቸው? ከወዴትስ መጡ? አሁን፡ አይሁዶችንና ቃልክዳናቸውንና ሌሎችንም እናውቃለን፡ ነገር ግን እነዚህ መቼ መጡ? '" አሁን ተመልከቱ፡

**ጌታ ሆይ፡ አንተ ታውቃለህ፡ አልሁት።** ("እ—እ—አላውቅም፡" ዮሐንስ፡ "ከአቅሜ በላይ ነው። አላውቅም" አለ።) **አለኝም፡ እነዚህ** ከ**ታላቁ** መከራ **የመጡ ናቸው፡** ("በፈተናዎችና፡ በብዙ አደጋዎች፡ በድካምና በወጥመድ አልፌያለሁ።" አያችሁ?) **ከታላቁ** መከራ የመጡ ናቸው፡ **ልብሳቸውንም አጥበው፡...** (በቤተክርሰቲያን? ልክ አይደለም?) ... **ልብሳቸውንም አጥበው፡ በበጉ ደም አነጹ።**

... ስለዚህ **በእግዚአብሔር ዙፋን ፊት ሆነው፥ ሌሊትና ቀንም በመቅደሱ ያመልኩታል...** (በቤቴ የምታገለግለኝ ማን ናት? ሚሰቴ። ትክክል ነው?)... **በመቅደሱ፡...** (በቤቴ እና በኢኮኖሚዬ፡ ከእኔ ጋር የምትቆየው ሚሰቴ ነች። እሷ ከእኔ ጋር የምትቀመጥ፡ ልብሶቼን የምታጥብ፡ ነገሮችን ለእኔ የምታዘጋጅልኝ እሷ ነች) ... በዙፋኑም ላይ **የተቀመጠው በእነርሱ ላይ ያድርባቸዋል።** (ኦህ፡ ማይ፡ አዳምጡ!)

**ከእንግዲህ ወዲህ አይራቡም፡...** (ሲመጡ ትንሽ ምግብ አጥተው የነበሩ ይመስላሉ) ... **ከእንግዲህም** ወዲህ አይጠሙም፣ **ፀሐይም ትኩሳትም ሁሉ፡** ከቶ **አይወርድባቸውም።**

**በዙፋኑ መካከል ያለው በጉ እረኛቸው ይሆናልና፡ ወደ ሕይወትም** ውኃ **ምንጭ ይመራቸዋልና፡ እግዚአብሔርም እንባዎችን... ሁሉ ከዓይናቸው** ያብሳል። (ይቹት፡ ሙሽሪታችሁ)

79 መቶ አርባ-አራት ሺዎቻችሁ፡ አገልጋዮቻችሁ ናቸው። ስለዚህ “የመንግስቱ ልጆች” ናቸው እነዚህ፡ ጥያቄውን የጠየቅከው ውድ ሰው፡ ይህን እ... አስፈላጊ ጥያቄ የጠየቀው ማነው። እዚህ የሆነ ቦታ የረሳሁት ሊ... ሊኖር ይችላል ብዬ አስባለሁ፡ ግን “ወደ ውጪ ሲጣሉ፡” ከእግዚአብሔር ልብ ይጣላሉ ማለት አይደለም። ለተወሰነ ጊዜ ከመንፈሳዊ ጥቅሞች ይጣላሉ። አያችሁ፡ ለትንሽ ወቅት ብቻ።

80 ምክንያቱም፡ ነቢዩ ስለ እስራኤል በዚህ ዘመን ስትመጣ ባየ ጊዜ፡ እንዲህ አለ፡ “መልካም፡ የሰንበት ቀን ሲወገድ፡ በ—በሰንበት እንደሌሎች ቀኖች መሸጥ ሲጀምሩና፡ ሌሎች ነገሮችን ሲያደርጉ እስራኤል ምን ትሆናለች? ” እርሱም አለ፡ “መልካም፡ እ—እ... እስራኤላውያን ሙሉ በሙሉ ይረሳሉ? ”

81 እንዲህ አለ፡ “ሰማይ ምን ያህል ከፍ ያለ ነው? ምድር ምን ያህል ጥልቀት አላት? በፊትህ በተዘረጋው በትር ለካው።”

እርሱም “አልችልም!” አለ፡

82 እንዲህም አለ፡ “እስራኤልንም መቼም አልረሳትም።” በእርግጠኝነት አይረሳትም! እስራኤል መቼም አትረሳም።

83 ስለዚህ፡ አያችሁ፡ **ዘመናት** እና **ዘለአለም** ሁለት የተለያዩ ነገሮች ናቸው። እስራኤል ውጪ ተጥሏል፡ ነገር ግን ከእግዚአብሔር ልብ አይደለም። ጳውሎስ ስለዚህ ተናግሯል፡ ለ... ለጥናት ጊዜ ካገኘሁ፡ ስለዚህ በአእምሮዬ የሚመጣውን ለእናንተ ልጠቅስላችሁ እችል ዘንድ፡ በ... በፍጥነት ወደ መጽሐፍ ቅዱስ እልፋለሁ፡ አያችሁ።

84 ጳውሎስ በዚያ ሲናገር፡ እኛ አሕዛቦች በምንሄድበትና በምንሠራበት መንገድ፡ መጠንቀቅ እንዳለብን ተናግሯል። አያችሁ? ምክንያቱም እግዚአብሔር ለመጀመሪያው ቅርንጫፍ ካልራራ፡ አያችሁ፡ እኛ ደግሞ በቅርንጫፉ ላይ የተተከልን ነን፡ አያችሁ፡... እስራኤልም፡ ለጊዜው ታውራለች፡ ብሏል። ለጥቂት ጊዜ ብቻ፡ እስራኤል ታውራለች። በትክክል፡ ነገር ግን መጋረጃው ከዓይናቸው ላይ ይነሳል። የመጨረሻዎቹ አሕዛብ ወደ እግዚአብሔር መንግሥት ሲወለዱ፡ መጋረጃው ከእስራኤል ዓይኖች ላይ ይነሳል። እነርሱም፡ “ይህ እኛ ለማየት ተሰፋ ያደረግነው መሲሕ ነው” ይላሉ። ትክክል ነው፡ ነገር ግን በአሕዛብ ላይ በር ተዘግቷል (መርከቡ—ተዘግቷል)፡ በዚያን ጊዜ ለ—ለአሕዛብ የሚቀር ጸጋ አይኖርም።

85 አሁን፡ በአንድ ጥያቄ ላይ ብዙ ጊዜ ወሰድኩ። አንድ ሰው “አሁንስ ወደ ጥያቄዬ አትደርሰምን፡” ሊል ይችላል። ደህና፡ በፍጥነት እንሄዳለንና መድረስ ካልቻልን እናያለን።

86 መልካም፡ ይ—ይሄው ረጅሙ ጥያቄው። የጠየቀችው ሴት ወይም የጠየቀው ወንድ፡ ወይም ማንኛዉም ሰው፡ ጥያቄው ትክክል ነው።

**53. ጌታ ኢየሱስ የሞተው ለዓለም ሁሉ ማለትም በዓለም ላሉት ሁሉ ሳይሆን፡ ነገር ግን...** (አሁን፡ ያንን አብራራለሁ፡ ነገር ግን እሱ፡ ወይም እሷ፡ ማንም ይሁን፡ የሴት ጽሁፍ ይመስላል።) **... ነገር ግን እብ ለ—ለሰጠው፡ ለዓለም ክፍል ላሉ ሰዎች የሞተ አይደለምን? ዓለም**

**ከመመሰረቱ በፊት፡ እግዚአብሔር የዘላለም ሕይወት እንዲኖራቸው ለሾማቸው፡ እንደ ፈቃዱም ለመረጣቸው አይደለምን?**

87 በፍጹም፡ ትክክል ነው! ትክክል ነው። ኢየሱስ የ... የሞተው... ዝምብሎ አይደለም ለዓላማ ነው።

88 እስቲ እንመልከት፡ ጥያቄው... የ—የሚመጣው በ... በዚህ ላይ ነው ብዬ አምናለሁ፡

**54. መጽሐፍ ቅዱስ እነዚህ ሰዎች እንደማይድኑ በ—በግልጽ ይናገራል። ስለዚህ...**

89 በትክክል። መጽሀፍ ቅዱስ እንደሚነግረን በእግዚአብሔር ለፍርድ አስቀድመው የተወሰኑ ሰዎች አሉ።

90 ሁልጊዜ በአእምሯችሁ ውስጥ ግልጽ እንዲሆን፡ ይህን ማንበብ ትፈልጋላችሁ? መልካም፡ እስቲ አሁን ወደ ይ—ይሁዳ መጽሐፍ እንለፍ፡ ይሁዳ እዚህ እየተናገረ ያለው፡

**የኢየሱስ ክርስቶስ ባሪያ፡ የያዕቆብም ወንድም የሆነ፡ ይሁዳ፡ በእግዚአብሔር አብ ተወደው፡ ለኢየሱስ ክርስቶስም ተጠብቀው፡ ለተጠሩ፡**

91 ለማን እንደሚናገር ተመልከቱ? ለኃጢአተኞች ሳይሆን፡ ለወንጌል አገልጋዮች ብቻ ሳይሆን፡ ነገር ግን ለተቀደሱና ለተጠሩት ነው። እያችሁ፡ አስቀድመው በመንግሥቱ ውስጥ ላሉትን ነው።

**ምሕረትና፡ ሰላም፡ ፍቅርም፡ ይብዛላችሁ።**

**ወዳጆች ሆይ፡... ስለምንካፈለው ስለ መዳናችን ልጽፍላችሁ፡ እጅግ** ተግቼ **ሳለሁ፡ ለቅዱሳን አንድ... ጊዜ ፈጽሞ ስለ ተሰጠ ሃይማኖት እንድትጋደሉ እየመከርኋችሁ እጽፍላ**ችሁ **ዘንድ ግድ ሆነብኝ።**

**ከብዙ ጊዜ በፊት ለዚህ** ፍርድ፡ **የተጻፉ አንዳንዶች ሰዎች ሾልከው ገብተዋልና፡...** (እንዴት? ) ... **የአምላካችንን ጸጋ በሴሰኝነት ይለውጣሉ፡...**

92 ከጥንት ጀምሮ የተደነገገ! እግዚአብሔር በዙፋኑ ላይ ተቀምጦ፡ "**ይህን** ሰው አድናለሁ፡ **ያን** ሰው አላድንም፡" አላለም። እንደዛ አልነበረም! አምላክ ሞቷል፡ ኢየሱስ በሞተበት ጊዜ፡ የኃጢአት ዋጋው መላዋን ምድርን ለእያንዳንዱ ሰው ሸፍኗል። እግዚአብሔር ግን፡ አስቀድሞ በማወቁ... እርሱ... ማንም እንዲጠፋ ፈቃደኛ አይደለም። ሁሉም ሰው እንዲድን ይፈልጋል። ይህ የዘላለም ዓላማው ያ—ነበር። ይሁን እንጂ አምላክ ከሆነ፡ ማን እንደሚድንና ማን እንደማይድን ያውቃል። የማያውቅ ከሆነ፡ ወሰን አልባ አምላክ አይደለም። ስለዚህ መጽሐፍ ቅዱስ ይህን ያስተምራል። ይህም እኛ...

93 ጊዜ ቢኖረን በሮሜ፡ ምዕራፍ 8 ላይ፡ የሚገኘውን ይህን መጽሐፍ ማንበብ ትችላላችሁ። ሮሜ፡ ምዕራፍ 9፡ ሌሎች ብዙ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች ላይ አለ። ኤፌሶን፡ ምዕራፍ 1። የእግዚአብሔርም መመረጥ እንዲጸና፡ እግዚአብሔር ቃል ኪዳኑን ያለምንም ቅድመ ሁኔታ እንደሰጠ፡ ማየት

ትችላላችሁ። ኢየሱስን የላከው አስቀድሞ ለሚያውቃቸው ሰዎች እንዲሞት ነው። አያችሁ?

94 ለማለት ብቻ አይደለም፡ “መልካም፡ እግዚአብሔር እንደምትድን እና እንደማትድን አያውቅም ትላላችሁን?” ዓለም ከመፈጠሩ በፊት፡ እግዚአብሔር እንደምትድን፡ ወይም ትድናለህ አትድንም ያውቃል፡ አለበለዚያ እሱ አምላክ አልነበረም።

95 **ወሰን አልባ** ማለት ምን ማለት እንደሆነ ታውቃላችሁ? መ... መዝገበ ቃላቱን ተመልከቱና **ወሰን አልባ** ማለት ምን ማለት እንደሆነ ለማወቅ ሞክሩ። ምክንያቱም፡ በምድር ላይ የሚኖሩትን ነፍሳት ሁሉ፡ ዝንቦችንም፡ ትንኞችንም፡ ጀርሞችንም ሁሉ ያውቃል። እነዚህ ነገሮች ከመፈጠራቸው በፊት ያውቃቸዋል፡ አለበለዚያ አምላክ አይደለም ማለት ነው። በእርግጥም፡ እርሱ ያውቃል። መልካም።

96 ከዚያም፡ በዚያ፡ እግዚአብሔር እ—እንዲህ ሊል አይችልም፡ “**አንተን** ወሰጄ፡ ወደ ገሃነም እልክሃለሁ፣ **አንተን** ወሰጄ፡ ወደ ሰማይ እልክሃለሁ።” እግዚአብሔር ሁላችሁም ወደ ሰማይ እንድትሄዱ ይፈልጋል። ይሁን እንጂ አንድ ሰው አጭበርባሪ እንደሚሆንና፡ ሌላኛው ደግሞ ጨዋ ሰውና ክርስቲያን እንደሚሆን አስቀድሞ ያውቅ ነበር። አያችሁ? ስለዚህ እንዲሞት ኢየሱስን መላክ ነበረበት፡ ያ ሰው እንዲድን አስቀድሞ ያውቅ ስለነበር። ተረድታችኋል?

አሁን እዚህጋ ተመልከቱ፡

**ቅዱሳን መጻሕፍት እነዚህ ሰዎች እንደማይድኑ በድንግዝግዝ ይነግሩናል።**

55. **ስለዚህ ቤዛው የአዳምን ዘር በሙሉ የሚሸፍን ከ... ከሆነና፡ አንዳንዶቹ የተሰፋውን ቃል፡ ወይም የተዘጋጀላቸውን ባለመቀበላቸው የጠፉ ከሆነ፡ ከ... ኃይል-... ነጻ... ከ... ከዘላለማዊው ሁሉን ቻይ አምላክ እቅዶችና ዓላማዎች የሚበልጥ ኃይል ይኖራልን? እንደዛ ይሆንን...** (አሁን ይህ የጠየቀው ሰው፡ ሁለተኛ ጥያቄ፡ እየጠየቀ ነው።) **የሰው ልጅ ነጻ ፈቃድ መኖር ሁሉን ቻይ ከሆነው አምላክ ዘላለማዊ እቅድና ዓላማ የላቀ ኃይል አይኖረውምን?**

97 አይ፡ ወንድሜ ወይም እህቴ። ፈጽሞ አይደለም! ከዚህ የበለጠ ኃይል ያለው ነገር የለም... የሰው ፈቃድ ከእግዚአብሔር ፍርድ—ከዘላለማዊ ዓላማ ጋር ሊወዳደር አይችልም። ይህ ሊሆን አይችልም፡ አያችሁ።

98 አሁን፡ የመጀመሪያው ጥያቄህ ትክክል ነበር። ሁለተኛው ጥያቄህ ሊሆን አይችልም፡ ወዳጄ። ምክንያቱም እዚህ ላይ፡ የተጻፈበትን መንገድ ተመልከቱ፡ አያችሁ፥ “የሰው ልጅ ነጻ ፈቃድ ሁሉን ቻይ ከሆነው አምላክ ዘላለማዊ እቅድና ዓላማ የላቀ ኃይል አይኖረውም?” ለምን፡ በፍጹም አይደለም። የሰው ፈቃድ ሁሉን ቻይ ከሆነው ከእግዚአብሔር ዓላማ እንዴት ሊበልጥ ይችላል? ሰው በሥጋዊ ሁኔታው የፈለገውን ማድረግ ይችላል፡ ይህ ደግሞ ዘላለማዊና ፍጹም ከሆነው አምላክ፡ የበለጠ ኃይል ይኖረዋል ማለት ነውን? ፈጽሞ አይደለም! ይህ ሊሆን አይችልም፡ አያችሁ። ዓላማው ፍጹም የሆነ፡ ዘላለማዊ አምላክ፡ እዚህ ምድር ላይ ያ—ያለ ሥጋዊ ሰው፡ ምንም ያህል ጻድቅ (እንዲሁም

ሊሆን ቢችልም)፡ የዘላለምና ሁሉን ቻይ ከሆነው ከ—ከአምላክ ዓላማ ጋር፡ ሊወዳደር የሚችልበት ጥበብ የለውም።

99 [አንዲት እህት ለወንድም ብራንሃምን ተናገረች—አርታዒ።] አዎን። ["ይቅርታ አድርግልኝ። አንድ ጥያቄ መጠየቅ ፈልጌ ነበር፡ ምን ማለቴ እንደሆነ—ም በተሳሳተ መንገድ ተረድተሃል።"] እሺ፡ መልካም፡ እህቴ። ["እኔ ያንን በፍፁም አላምንም፡ ለማለት የፈልኩት 'የእግዚአብሔር ዘላለማዊ ዓላማ ከሰው ልጅ ነጻ ፈቃድ በላይ ነው' ማለቴ ነው።"]

100 ትክክል ነው። ኦህ፡ ደህና፡ በ—በተሳሳተ መንገድ አንብቤዋለሁ ማለት ነው፡ አያችሁ። መልካም። አዎን፡ ትክክል ነሽ፡ እህቴ። ያ—ያንቺ ጥያቄ እንደሆነ አላውቅም ነበር። መልካም። ነገር ግን፡ ከየት እንዳመጣሁት፡ ተመልከቱ፡ አያችሁ፡... አሁን ልየው፡ "ስለዚህ ቤዛው የአዳምን ዘር በሙሉ የሚሸፍን ከሆነና፡ አንዳንዶቹ የተሰፋውን ቃል ወይም የ—የተዘጋጀላቸውን ባለመቀበላቸው የጠፉ ከሆነ፡ ታዲያ የሰው ልጅ ነፃ ፈቃድ ሁሉን ቻይ የሆነው አምላክ ዘላለማዊ ዕቅድና ዓላማ ካለው የበለጠ ኃይል አይኖረውም?" አያችሁ፡ ሃ—ሃሳብሽን በተሳሳተ መንገድ ተረድቼው ነበር። አዎን፡ ሁሉን ቻይ የሆነው አምላክ ዘላለማዊ ዓላማ። ደህና፡ ያ ያሰማማል።

101 ሁሉም ሰው ያንን ይረዳል ብዬ እገምታለሁ። ከተረዳችሁ፡ እጃችሁን አንሱ። የ—የእግዚአብሔር ዘላለማዊ አላማ፡ በእርግጥ ሰው ከሚያደርገው እጅግ በጣም—እጅግ በጣም የላቀ ነው።

አሁን፡

**በማቴዎስ ምዕራፍ 28 ቁጥር 19 ላይ የ... የሚገኘውን፡ ስለ ውኃ ጥምቀት፡ የሚናገረውን ሃሳብ አልገባኝም። ይህ ምን ማለት ነው?**

102 መልካም፡ አሁን፡ ብዙ አይወስደኝም ጥቂት ደቂቃ ብቻ። እስኪ ከእኔ ጋር ፍቃደኛ ከሆናችሁ፡ ማቴዎስ ወንጌል ምዕራፍ 28፡ እና ቁጥር 19፡ እንክፈት። አካሉ ምን እንደሆነ፡ እናገኘዋለን... ሃያ-አምስት... አሁን፡ በደምብ ካዳመጣችሁት ይህ ያጠናክራቸዋል። ይህ—ጥሩ ነው፡ አያችሁ። የወንጌል አገልግሎት አይደለም፡ ነገር ግን...

103 አሁን እዚህ ላይ... ሰዎች፡ "በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ግጭት አለ" ይላሉ። አሁን፡ አንድ ሰው ማ... ማቴዎስ 28:19 እንዲከፈትልኝ እፈልጋለሁ። ወይም፡ አይ፡ የሆነ ሰው... ማቴዎስ 28:19 ይክፈትልኝ። ደግሞ ሌላ ሰው ሐዋርያት ስራ 2፡38 እንዲከፈልኝ እፈልጋለሁ። ወንድም ኔቪል፡ መጽሐፍህን ከፍተሃል?

104 አሁን ለራሳችሁ እንዲታነቡ እፈልጋለሁ። "በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የሚገኘውን ጥብቅ ተቃርኖ አሳያችኋለሁ። እና ምን—መጽሐፍ ቅዱስ... ይላሉ ሰዎቹ 'መጽሐፍ ቅዱስ ከራሱ ጋር አይቃረንም፡' ይህንን ግምት ውስጥ እንድታስገቡ እፈልጋለሁ።"

105 ይህ ደግሞ ፕሮፌሰሮቹን ያሸብታቸዋል። ግን ቀ—ቀላል ነው። አሁን ማቴዎስ 28:19ን አነባለሁ፡ እናንተም ተከተሉኝ። የሐዋርያት ሥራ 2፡38ን የከፈታችሁ፡ ተዘጋጁ። ከ18ኛው ቁጥር እጀምራለሁ፡ ይህ የማቴዎስ ወንጌል የመጨረሻ ምዕራፍ ነው፥

**ኢየሱስም መጥቶ ለ-...** ለደቀ **መዛሙርቱ ተናገረ፡ እንዲህም አላቸው፡ ሥልጣን ሁሉ በሰማይና በምድር ተሰጠኝ።** (የአብ ስልጣን የት አለ? )

106 በሰማይና በምድር ያለው ስልጣን ሁሉ ለኢየሱስ ከተሰጠ፡ እግዚአብሔር ስልጣን አልባ ሆኗል፡ ማለት ነውን? ወይስ ታሪክ ብቻ እየተናገረ ነውን? ወይስ እየቀለደ ነውን? የእውነቱን ነውና! የእውነቱን እንደተናገረ አታምኑምን? መልካም፡ ሥልጣን ሁሉ የተሰጠው ለእርሱ ከሆነ፡ ታዲያ የእግዚአብሔር ሥልጣን የት አለ? እርሱ ራሱ እግዚአብሔር ነው! በትክክል። ይህ ብቻ ነው ያለው። ያ ነው በቃ። አያችሁ፡ እርሱ ራሱ እግዚአብሔር ነው፡ ካልሆነ ግን እዚያ ተቀምጦ የነበረው ሰውዬ፡ ስልጣን የነበረው፡ አሁን ግን የሌለው ሆኗል ማለት ነው። አያችሁ? ስለዚህ ግራ—ልታጋቡት አይገባችሁም። እዚህ ተመሳሳይ ነገር በትክክል እንረዳለን። መልካም፡

... ሥልጣን ሁሉ በ... **በሰማይና በምድር ተሰጠኝ።**

**እንግዲህ ሂዱና፡... አሕዛብን ሁሉ በአብ፡ በወልድና፡ በመንፈስ ቅዱስ ስም፡ እያጠመቃችኋቸው፡**

**ያዘዝኋችሁንም ሁሉ እንዲጠብቁ እያስተማራችኋቸው ደቀ መዛሙርት አድርጓቸው፡... እነሆም፡ እኔ** እስከ **ዓለም ፍጻሜ ድረስ** ሁልጊዜ፡ **ከእናንተ ጋር ነኝ።**

107 የሐዋርያት ሥራ 2፡38 ላይ፡ አሁን አንድ ሰው ያንብብ። አንድ ደቂቃ ብቻ ጠብቁ። የሐዋርያት ሥራ፡ ምዕራፍ 2 ላይ፡ ቁጥር 38። አሁን፡ አሁን በደምብ አዳምጡ፡ በትዕግስት አዳምጡ፡ አሁን እናያለን። አሁን፡ ኢየሱስ አሁን ማቴዎስ 28፡19 ላይ፡ "እንግዲህ ሂዱና፡ አሕዛብን ሁሉ፡ በአባት፡ በልጅና፡ በመንፈስ ቅዱስ ስም እያጠመቃችኋቸው አስተምሯቸው።"

108 አሁን፡ እነ ጴጥሮስ፡ ከአሥር ቀናት በኋላ... ሌላ ስብከት አልሰበኩም። ወደ ኢየሩሳሌም ሰገነት ላይ ወጡ፡ መንፈስ ቅዱስም እስኪመጣ ድረስ (ለአሥር ቀን) ጠበቁ። ስንቶች ታውቃላችሁ ይህን? በዚህ ቦታ። ጴጥሮስም፡ ጴጥሮስ የመንግስተ ሰማያት ቁልፎች ይዟል። መልካም፡ እዚህ ምን እንዳደረገ እንመለከታለን። ማቴዎስ፡ ወይም የሐዋርያት ሥራ ምዕራፍ 2 ላይ፡ 36ኛውን ቁጥር እንመልከት፡

እንግዲህ **ይህን እናንተ የሰቀላችሁትን ኢየሱስን፡ እግዚአብሔር ጌታም፡ ክርስቶስም፡** እንዳደረገው **የእስራኤል ወገን ሁሉ በ... በእርግጥ ይወቅ።**

"ጌታም ክርስቶስም።" ምንም ጥያቄ የለውም፡ በሰማይና በምድር ያለው ኃይል ሁሉ ለእርሱ ተሰጥቷል።

**ይህንም በሰሙ ጊዜ፡ ልባቸው ተነካ፡ ጴጥሮስንና... ሌሎችንም ሐዋርያት፡ ወንድሞች** ሆይ፡ **ምን እናድርግ፡ አሉአቸው?**

ጴጥሮስም... **ንስሐ ግቡ፡ ኃጢአታችሁም፡** ይሰረይ ዘንድ፡ **እያንዳንዳችሁ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም** ተጠመቁ፡ **የመንፈስ ቅዱስንም ስጦታ ትቀበላላችሁ።**

109 አሁን፡ እዚህ ግጭት አለ፡ ማቴዎስ የሚለው፡ "በአባት፡ በልጅ፡ በመንፈስ ቅዱስ ስም፥ አጥምቁ፡" ጴጥሮስ በሐዋርያት ሥራ 2፡38 ላይ፡ ከአሥር ቀናት በኋላ፡ "ንስሐ ግቡ፡ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ተጠመቁ" አለ።

110 ከዚህ ቀጥሎ፡ በ—በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ፡ ስለ ንስሐ፡ ወይም ስለ ጥምቀት የተነገረው፡ በ—በሐዋርያት ሥራ ምዕራፍ 8 ሲሆን፡ ፊልጶስ ወደ ሳምራውያን ሄዶ… ሲ—ሲሰብክ እናየዋለን። መንፈስ ቅዱስንም ተቀበሉ፡ በኢየሱስ ክርስቶስም ስም ተጠመቁ።

111 ቀጣዩ ጊዜ የተጠቀሰው፡ አሕዛብ ሲቀበሉት ነበር፡ የሐዋርያት ሥራ 10፡49 ላይ፡

> **ጴጥሮስ**ም **ይህን እ… እየተናገረ ሳለ፡** እነሆ፡ **ቃሉን** በ**ሰሙ ሁሉ** ላይ… **መንፈስ ቅዱስ ወረደ።**
>
> በ**ልሳኖች ሲናገሩ፡ እግዚአብሔርን**ም **ሲያከብሩ ሰምተዋልና። በዚያን ጊዜ ጴጥሮስ እንዲህ** አለ፡
>
> **እነዚህ** እንደ እኛ ደግሞ **መንፈስ ቅዱስን** የተቀበሉ… **እንዳይጠመቁ፡ ውኃን ይከለክላቸው ዘንድ የሚችል ማን ነው?**
>
> በኢየሱስ ክርስቶስ **ስምም ይጠመቁ ዘንድ አዘዛቸው።**

112 አሁን እዚህ ላይ አንድ ነገር ላሳያችሁ፡ አንድ ትንሽ ነገር ላሳያችሁ ስለዚህ አትረሱትም፡ ትንሽ ምሳሌ ልስጣችሁ። በመላው… በመላው-… ዓለም ላይ ስንት አይነት ሕዝቦች አሉ? ሦስት ናቸው፡ የካም፡ የሴም፡ እና የያፌት ሰዎች። ስንቶቻችሁ ታውቃላችሁ? የመጣነው ከሦስቱ ከኖኅ ልጆች ነው። የካም ሰዎች፡ የሴም ሰዎች… የያፌት ሰዎች አንግሎ-ሳክሰን ናቸው፡ የሴም ሕዝብ ደግሞ… ሦስቱ ትውልዶች፡ ማለትም፡ አይሁድ፡ አሕዛብ፡ እና ግማሽ አይሁዳዊ እና አህዛብ። አሁን፡ አስተውሉ፡ እንግዲህ ያም… እና **እነዚህም** ሴ… ሴም፡ ካምና፡ ያፌት ናቸው።

113 አሁን፡ ለመጀመሪያ ጊዜ ስለ ጥምቀት የተነገረው፡ በመጥምቁ ዮሐንስ ነው። እውነት መሆኑን ስንቶቻችሁ ታውቃላችሁ? መልካም፡ **እዚህ** አመጣዋለሁ፡ እዚህ ጋር፡ መጥምቁ ዮሐንስን። ዮሐንስ ሕዝቡን በዮርዳኖስ ወንዝ ያጠምቅ ነበር፡ ንስሐ እንዲገቡና ከእግዚአብሔር ጋር እንዲታረቁ፡ ንብረታቸውን እንዲሸጡና፡ ለድሆች እንዲመግቡ፡ ወታደሮቹም ባላቸው ገንዘባቸው እንዲረኩና፡ ከእግዚአብሔር ጋር እንዲታረቁ ያዛቸው ነበር። ስንቶቻችሁ ታውቃላችሁ? በዮርዳኖስም ወንዝ አጠመቃቸው፡ አልረጨባቸውም፡ አላፈሰሰባቸውም፡ ነገር ግን አጠመቃቸው! የማታምኑ ከሆነ፡ እዚህ መዝገበ ቃል አለ፡ **ባፒቲዞ** የሚል ካልሆነ ተመልከቱ፡ ይህም "መጠመቅ፡ መጥለቅ፡ ወደ ውስጥ መግባት፡ መቀበር" ማለት ነው። አሁን፡ ጥምቀት ለመጀመሪያ ጊዜ የተነገረው፡ በዚያ ጊዜ ነበር።

114 ሁለተኛው ጥምቀት የተነገረው፡ ኢየሱስ በማቴዎስ 28:19፡ ሲያዝ ነው።

115 ቀጣይ ስለ ጥምቀት የተነገረው፡ በሐዋርያት ሥራ 2፡38 ላይ ነው።

116 የሚቀጥለው ጊዜ ስለ ጥምቀት የተነገረው፡ በሐዋርያት ሥራ ምዕራፍ 8 ላይ ነው።

117 የሚቀጥለው ጊዜ ስለ ጥምቀት የተነገረው፡ በ—በሐዋርያት ሥራ ምዕራፍ 10 ላይ ነው።

118 አሁንም እዚህ ጋር፡ ኢየሱስ ከተናገረው ጊዜ ይዘን፡ "እንግዲህ ሂዱና፡ አሕዛብን ሁሉ፡ በአባት፡ በልጅና፡ በመንፈስ ቅዱስ ስም አጥምቋቸው" ካለበት ቦታ ተነስተን ነው።

119 አሁን በመጀመሪያ፡ ይህንን ጥቅስ እናቃናው። "መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ አንዱ ጥቅስ ከሌላው ጋር እንደማይጋጭ" ነግሬአችሁአለሁ። ወደ እኔ እንድታመጡት እፈልጋለሁ። ይህን ጥያቄ ለሃያ-ስድስት ዓመታት ያህል ስጠይቅ ቆይቻለሁ፡ እስካሁን ድረስ ግን አንዱ ጥቅስ ከሌላ ጋር ሲጋጭ አላገኘሁትም። አንዱ ከአንዱ ጋር የሚጻረር ጥቅስ የለም-... የሚጋጭ ከሆነ፡ ሰው-የጻፈው ነው ማለት ነው። አይ፡ ወዳጄ፡ መጽሐፍ ቅዱስ እርስ በርሱ አይጋጭም!

120 አሁን እንዲህ ትላላችሁ፡ "**ይኼስ** እንዴት ነው? "

121 ኢየሱስ እዚህ ቆሞ፡ "እንግዲህ ሂዱና፡ አሕዛብን ሁሉ አስተምሩ፡ በአባት፡ በልጅ፡ በመንፈስ ቅዱስ ስም አጥምቋቸው" አላቸው።

122 ጴጥሮስም ወደ ኋላ ዘወር ብሎ፡ እንዲህ አለ፡ "እያንዳንዳችሁ፡ ንስሐ ግቡ፡ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ተጠመቁ።"

123 "ይሄው ግጭት አለ የሚትሉት።" ይመስላል። አሁን፡ በሥጋዊ አእምሮ የምታነቡ ከሆነ፡ ክፍት የሆነ ልብ ከሌላችሁ፡ እርስ በርስ የሚጋጭ ይሆናል።

124 ነገር ግን በተከፈተ-አእምሮ ካነበባችሁ፡ "መንፈስ ቅዱስ ይህን ከጠቢባንና ከአስተዋዮች ዐይን ሸሽጎታል፡" ኢየሱስም እንደዛ ብሎ፡ እግዚአብሔርንም አመሰግኗል፡ "ለሚማሩ ለሕፃናትም ገለጠ።" ራስ ወዳድነት የሌለበት፡ አስተሳሰብ ካላችሁ፡ ለመማር ፈቃደኛ የሆነ ልብ ካላችሁ፡ መንፈስ ቅዱስ እነዚህን ነገሮችን ያስተምራችኋል።

125 አሁን ካልተነፃፀረ... እንዲህ ትላላችሁ፡ "ትክክል መሆንህን በምን ታውቃለህ? " እንግዲህ፡ ከቅዱሳት መጻሕፍት ጋር ይስተያያል። ካላስተያያችሁ፡ እዚህ ግልጽ የሆነ ግራ መጋባት ይገጥማችኋል።

126 አሁን አንድ ጥያቄ ልጠይቃችሁ እፈልጋለሁ። ይህ የማቴዎስ ወንጌል የመጨረሻ ምዕራፍ ነው። እያንዳንዳችሁ ልጆች እንኳን እንዲረዱት፡ ቀስ አ... አድርጌ አመጣዋለው።

127 ለምሳሌ፡ አንድ የፍቅር ታሪክ ብታነቡ፡ ከበስተጀርባው እንዲህ ቢል፡ "ሜሪ እና ጆን ቀሪ ህይወታቸው በደስታ ኖሩ።" መልካም፡ ከዚያ በኋላ በደስታ የኖሩት ጆን እና ሜሪ እነማን እንደሆኑ ለማወቅ ትፈልግላችሁ። አሁን፡ ጆን እና ሜሪ ማን እንደሆኑ ማወቅ ከፈለጋችሁ፡ ወደ መጽሃፉ መጀመሪያ ተመልሳችሁ ጆን እና ሜሪ ማን እንደሆኑ ብታነቡ ይሻላችኋል። ከዚያም ወደ መጀመሪያው ቦታ ተመልሳችሁ ሜሪ ማን እንደነበረችና፡ ከየትኛው ቤተሰብ እንደመጣች፣ ጆን ማን እንደነበረና፡ ከየትኛው ቤተሰብ እንደመጣ፡ እንዲሁም ሰሙ ማን እንደነበረ፡ እንዴት እንደተጋቡ፡ ስለዚያ ሁሉ ለማወቅ ትሞክራላችሁ። እውነት ነው?

128 ደህና፡ እዚህም መጽሐፍ ቅዱስን ስናነብ ተመሳሳይ ነገር ነው። ተ... ተመልከቱ፡ ኢየሱስ ከቶ እንዲህ አላለም፡ "ሂዱና አህዛብን ሁሉ በአባት ስም፡ በልጅ ስም፡ በመንፈስ ቅዱስ ስም አጥምቁ" አላለም፡ ይህ የሥላሴ አማኞች

የሚያጠምቁበት መንገድ ነው። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ለዚህ የሚሆን ጥቅስ የለም። “በሰሞች (ሰ-ሞ-ች)፡ በሰሞች” ማለትም በአባት፡ በልጅና፡ በመንፈስ ቅዱስ ሰሞች፡ በፍጹም አላለም።

129 እርሱ ያለው፡ “በ (ሰ-ም) ሰም፡” በነጠላ ሰም ነው ያለው። በመጽሐፍ ቅዱሳችሁ ይህ እውነት እንደሆነ ተመልከቱ፡ ማቴዎስ 28ን፡ “**ሰም።**”

130 “በአባት ሰም፡ በልጅ ሰም… ” አይደለም፡ የሥላሴ ሰባኪዎች የሚያጠምቁበት መንገድ እንደዛ ነውና። “በአባት ሰም፡ በልጅ ሰም፡ በመንፈስ ቅዱስ ሰም።” ያ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ እንኳን የለም።

131 “ስለዚህ በሰም… ” እናንተም፡ “እንግዲህ፡ ይህን ‘በአባት፡ በልጅ እና በመንፈስ ቅዱስ’ ሰም ትላላችሁ።” እንደዚያ ከሆነ እንግዲያውስ ሰም አለ ማለት ነዋ።

132 መልካም፡ **አባት** ሰም ነውን? **አባት** ሰም እንዳልሆነ የምታውቁት ሰንቶቻችሁ ናችሁ? **አባት** የማዕረግ ሰም ነው። **ልጅ** ሰም አይደለም። **ልጅ** ሰም አለመሆኑን የምታውቁት ሰንቶቻችሁ ናችሁ? እዚህ ውስጥ ሰንት አባቶች አላችሁ? እጆቻችሁን አንሱ። እዚህ ውስጥ ሰንት ልጆች አላችሁ? እጆቻችሁን አንሱ። መልካም፡ ከእናንተ መካከል ሰሙን “ልጅ” ተብሎ የተሰየመው ማን አለ? ከእናንተ መካከል ሰሙን “አባት” ተብሎ የተሰየመው ማን ነው? መልካም፡ **መንፈስ ቅዱስ** ሰም አይደለም፡ **መንፈስ ቅዱስ** ማንነቱ ነው። እዚህ ውስጥ ሰንት የሰው ልጆች አላችሁ? እጆቻችሁን አንሱ። አያችሁ? እነሆ፡ መንፈስ ቅዱስም እንዲሁ ማንነቱ ነው። **አባት**፡ **ልጅ**፡ **መንፈስ ቅዱስ**፡ አንዳቸውም ቢሆኑ ሰሞች አይደሉም፡ ሰያሜ የለውም።

133 ታዲያ፡ ከዚያ፡ ኢየሱስ፡ “በአባት፡ በልጅ መንፈስ ቅዱስ ሰም አጥምቁ” ካለ፡ ወደ ኋላ መለስ ብለን አባት፡ ልጅ፡ መንፈስ ቅዱስ ማን እንደሆኑ ማወቅ አለብን። እስቲ ወደ ማቴዎስ ምዕራፍ 1 እንመለስ፡ በሰሙ እንጠመቃለን የተባለው ይህ ሰው ማን እንደሆነ እንመልከት። አሁን ደግሞ በማቴዎስ፡ ምዕራፍ 1 ላይ፡ እና ቁጥር 18 እንጀምራለን። ሁላችሁም፡ በጥሞና አንብቡ።

134 አሁን፡ ጥያቄውን የጠየቅከው፡ እዚጋ ትንሽ ምሳሌ ልሰጥህ። አሁን በግልፅ እንድትረዱት ሶሰት ነገሮችን እዚህ አሰቀምጣለሁ፡ (ምሳሌውን ተመልከቱ) እነዚህ መጽሐፍ ቅዱሶችንና ሌሎች መጽሐፍትን፡ በምሳሌነት ለመግለጽ እጠቀማለው።

135 መልካም፡ እያንዳንዳችሁ በቅርበት እንድትመለከቱኝና፡ እንድትከተሉኝ እፈልጋለሁ። እንግዲህ፡ **ይህ** እግዚአብሔር አባት ነው። **ይህ** እግዚአብሔር ልጅ ነው። **ይህ** እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ነው። አሁን፡ ሰንቶቻችሁ ናችሁ የተረዳችሁት? እኔ ምለውን ከእኔ በኋላ ትላላችሁ። **ይሄኛው** ማን ነው? [ጉባኤው፡ “መንፈስ ቅዱስ” አለ።—አርታዒ።] መንፈስ ቅዱስ። **ይሄኛውስ** ማን ነው? [“አባት።”] **ይሄኛውስ** ማን ነው? [“ልጅ።”] አሁን፡ የሥላሴ እምነት ተከታዮች የሚያምኑት በዚህ መንገድ ነው፡ አያችሁ፡ ይህ ደግሞ አረማውያን እንድንሆን፡ ያደርገናል።

136 አይሁዶች፥ ከአይሁድ ጋር ምንም ነገር ማድረግ የማትችሉበት ምክንያት ይህ ነው። እንዲህ አለ፡ “እግዚአብሔርን በሦስት ቁርጥራጮች ቆርጠህ ለአይሁዳዊ መስጠት አትችልም” አለ። ነገር ግን፡ በእውነትም አይቻልም፡

ለእኔም አይቻልም። አያችሁ? አይቻልም፡ ወዳጄ። እርሱ አንድ አምላክ ነው። በትክክል። ሦስት አማልክት አይደሉም። አሁን—ምን ያ—ያህል ቀላል እንደሆነ ልብ በሉ።

137 አሁን ለማወቅ እየሄድን ነው። አሁን፡ ማን ነው... **ይህ** ማን ነው? ድምፃችሁን ከፍ አድርጉ። እግዚአብሔር ልጅ። ትክክል ነው? **ይህ** ልጅ ነው። መልካም፡ አባቱ እግዚአብሔር ነው። ትክክል ነው? አባቱ አምላክ እንደሆነ የምታምኑ ስንቶቻችሁ ናችሁ? እጆቻችሁን አንሱ። እግዚአብሔር የኢየሱስ ክርስቶስ አባት እንደሆነ የምታምኑ ስንቶቻችሁ ናችሁ? ደህና።

**የኢየሱስ ክርስቶስም ልደት እንደዚህ ነበረ፡...**

138 አሁን ደግሞ ማቴዎስ "በስሙ አጥምቁ" ብሎ የተናገረውን አባት፡ ልጅ፡ መንፈስ ቅዱስ፡ ማን እንደሆኑ ለማወቅ ወደ ኋላ እንመለሳለን። አያችሁ፡ ስም፡ አሁን ስሞች አይደሉም፡ ምክንያቱም ስሞች ሊሆኑ ስለማይችሉ ነው፡ ምክንያቱም በዚያ ውስጥ ስም የለውም።

**የኢየሱስ ክርስቶስ ልደት በዚህ መንገድ ነበር፡ እ... እናቱ ማርያም ለዮሴፍ በታጨች ጊዜ፡ ሳይገናኙ፡** ከእግዚአብሔር አባት **ዘንድ ልጅ ጸንሳ ተገኘች።** (መጽሐፍ ቅዱስ እንደዚያ ይላልን? መጽሐፍ ቅዱስ ምን ይላል? )... **ከመንፈስ ቅዱስ ጸንሳ ተገኘች።**

139 እንግዲያውስ **ከሁለቱ** አባቱ ማን ነው? አሁን፡ መጽሐፍ ቅዱስ **ይህ** አባቱ እንደሆነ ተናግሯል፡ ኢየሱስም **ይህ** አባቴ ነው ብሏል። ታዲያ፡ አባቱ የትኛው ነው? ታዲያ፡ ሁለት አባቶች ነበሩት ማለት ነውን፡ ምን እናድርግ? ሁለት አባቶች ካሉት፡ ከጋብቻ ውጭ የተወለደ ልጅ ነው።

140 አሁን ትንሽ ወደፊት እናንብብ፡

**እጮኛዋ ዮሴፍም፡ ጻድቅ ሆኖ ሊገልጣት ስላልወደደ፡ በግልጽ ይፋዊ ምሳሌ ሊያደርጋት** ፍቃደኛ **ስላልሆነ፡** ነገር ግን **በሰውር ሊተዋት አሰበ።**

**እርሱ ግን ይህን ሲያስብ፡ እነሆ፡ የጌታ መልአክ በሕልም ታየው፡ እንዲህም አለ፡ የዳዊት ልጅ፡ ዮሴፍ ሆይ፡ እጮኛህን ማርያምን ለመውሰድ አትፍራ፡ ከእርሰዋ የተፀነሰው...** [ ጉባኤው፡ "ከመንፈስ ቅዱስ ነውና" አሉ—እርታዒ።]

141 ከ**ምን**? ከመንፈስ ቅዱስ? ታዲያ፡ በተመሳሳይ ጊዜ አባት የእሱ አባት፡ መንፈስ ቅዱስም ደግሞ የእሱ አባት እንዴት ይሆናል? አሁን፡ ያ ትክክል ከሆነ፡ ሁለት አባቶች ነበሩት ማለት ነው። አይደለም፡ ወዳጄ! መንፈስ ቅዱስ እግዚአብሔር ነው። መንፈስ ቅዱስ **እግዚአብሔር** ነው። ስለዚህ እግዚአብሔርና መንፈስ ቅዱስ አንድ አካል ናቸው፡ ወይም ሁለት አባቶች ነበሩት ማለት ነው።

142 አያችሁ፡ **ጆን እና ሜሪ፡** ማን እንደሆኑ ከተወሰነ ጊዜ በኋላ አወቅን። እሺ፡ ጴጥሮስ እና ማቴዎስ እርስ በርስ ለመጋጨት እየሞከሩ እንደሆነ እና እንዳልሆነ አውቀናል፡ ቅዱሳት መጻሕፍት እርስ በርስ የሚጋጩ ከሆኑ እንመልከት። የመንፈሳዊ ግንዛቤ ማነስ ነው። በትክክል።

**እርሱ ግን ይህን ሲያስብ...**

143 ያንን 20ኛው ቁጥር ነው፡ ያነበብኩት። አሁን 21ኛው፡

> **ወንድ ልጅም ትወልዳለች፡**... (ይህ ሰው፡ **ከእነዚህ** የትኛው ነበር? አንድ አካል፡ እግዚአብሔር ነው።) ... **ሰሙንም ማን ትለዋለህ**... **(ማን?)** [ጉባኤው ሲመልስ፡ "**ኢየሱስ**" አለ—አርታዒ።] ... **እርሱ ሕዝቡን ከኃጢአታቸው ያድናቸዋልና።**
>
> ... **በነቢይ ከጌታ** ዘንድ፡ **እነሆ... ድንግል ትፀንሳለች ልጅም ትወልዳለች፡ ሰሙንም አማኑኤል፡**
>
> **ይሉታል፡ የተባለው ይፈጸም ዘንድ፡ ይህ ሁሉ ሆኖአል፡ ሰሙንም አማኑኤል ይሉታል፡**... ትርጓሜውም፡ **እግዚአብሔር ከእኛ ጋር የሚል ነው።**

144 ታዲያ ለዘላለም በደስታ የኖሩ **ጆን እና ሜሪ** እነማን ነበሩ? እንዲህ የተናገረው ማን ነበረ፡ "እንግዲህ ሂዱና፡ አሕዛብን ሁሉ፡ በአባት፡ ልጅ፡ መንፈስ ቅዱስ እያጠመቃችኋቸው አስተምሯቸው ያላቸው ማን ነው"? አባቱ ማን ነበር? አባት፡ ልጅ፡ መንፈስ ቅዱስ ሰም ማን ነው? [አንድ ሰው፡ "ኢየሱስ" በማለት መለሰ።—አርታዒ።] በትክክል፡ ነው። በእርግጥ፡ ከዚህ ጋር የሚቃረን ነገር የለም። በትንሹም ቢሆን እንኳ አይቃረንም። ጥቅሱን ያቃናል። እሱ አባት፡ ልጅ፡ መንፈስ ቅዱስ ነበር። እግዚአብኤር (አማኑኤል) ከእኛ ጋር ኖረ፡ "ኢየሱስ" በሚባል አካል ውስጥ ተገለጠ።

145 አሁን፡ የዋንነስ ቤተ ክርስቲያን ዋንነስ ትምህርት፡ እኔ በእርግጠኝነት በዚህ፡ ኢየሱስ እንደ ጣታችሁ አንድ ነው ብሎ በማሰብ አልስማማም። አባት ሊኖረው ይገባል። ባይሆንስ፡ እንዴት የራሱ አባት ሊሆን ይችላል? አባቱ ሥላሴዎች እንደሚሉት ሰው ከሆነ፡ እንግዲያውስ ከሁለት አባቶች በሕገወጥ መንገድ ተወለደ ነው ማለት ነዋ። ስለዚህ፡ እያችሁ፡ ሁለታችሁም በክርክራችሁ ተሳስታችኋል። እያችሁ?

146 እውነታው ግን፡ አባትና፡ ልጅ፡ መንፈስ ቅዱስ፡ አንድ አካል መሆናቸው ነው። [በቴፕ ላይ ባዶ ቦታ—አርታዒ።] ... የዓለምን ኃጢአትን ለማስወገድ፡ በሥጋ ድንኳን አደረ። ይህ በትክክል እውነት ነው፡ "እግዚአብሔር ከኛ ጋር።" አሁን፡ ስለዚህ፡ ማቴዎስ 28፡19...

147 አሁን፡ በሰላሴ የተጠመቀ አንድ ሰው ካለ፡ በቅዱሳን ጽሑፎች ውስጥ ፈልጉ... (አሁን አስቡበት፡ አሁን ይህ እንዲያልፋችሁ።) ... በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ አንድ ሰው "በአባት፡" "በልጅ" እና "በመንፈስ ቅዱስ" ሰም፡ የተጠመቀበት ቦታ ካገኛችሁ፡ ወደ እኔ ተመልሳችሁ ኑና ግብዝ እንደሆንኩ ንገሩኝ፡ እኔም በጀርባዬ ላይ ምልክት አድርጌ በከተማው ውስጥ እዞራለሁ። ከዘፍጥረት እስከ ራዕይ ድረስ፡ በቅዱሳት መጻሕፍት ውስጥ የለም። ነገር ግን በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ያለ እያንዳንዱ ሰው በኢየሱስ ክርስቶስ ሰም ተጠመቀ!

148 "ቆይ ቆይ፡ ሰባኪው። ዮሐንስስ? በምንም አይነት ሰም አላጠመቀም!" ትላላችሁ፡

149 መልካም፡ ምን እንደሆነ እናያለን፡ የ—የ—የሐዋሪያት ስራ፡ ምዕራፍ 19ኛን እንክፈት። እዚያም የዮሐንስን ደቀ መዛሙርት እናገኛለን። እነዚህን ቡድን

እስከሚናገኝ ድረስ፡ እያንዳንዱ ሰው በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ተጠምቋል። የሐዋርያት ሥራ፡ ምዕራፍ 19። አሁን ንባቡን እንጀምር፡ እዚያ የዮሐንስን ደቀ መዛሙርቶችን እናገኛለን፡

**እንዲህም ሆነ፡... አጵሎስም** (የሕግ ባለሙያ የነበረ፡ የተቀየረው) **በቆሮንቶስ ሳለ፡ ጳውሎስ በላይኛው አገር አልፎ** ወ... ወደ **ኤፌሶን መጣ፡ አንዳንድ ደቀ መዛሙርትንም** አገኘ፡ (የኢየሱስ ተከታዮች ነበሩ)

150 ከዚህ በፊት የነበረውን ምዕራፍ ልብ ብላችሁ ካነበባችሁ፡ በጣም ጥሩ ጊዜ ያሳለፉ ከመሆኑም በላይ ይጮኹና ይደሰቱ ነበር። ሰንቶቻችሁ ታውቃላችሁ? አቂላና ጵርስቅላ በስብሰባው ላይ ተገኝተው ነበር። ጳውሎስና ሲላስ ተደበደቡ፡ ቆስለው ወደ እስር ቤት ተጣሉ። ትክክል ነው? ወደዚህም መጥተው፡ አቂላንና ጵርስቅላን አገኙ። በባፕትስት ሰባኪ በአጵሎስ፡ ረቫይቫል እያደረጉ ነበር፡ "ኢየሱስ ክርስቶስ" መሆኑን በቅዱሳን ጽሑፎች አማካኝነት ያረጋግጥ ነበር። አሁን ደግሞ ጳውሎስ አገኘው፥

... **ጳውሎስ በላይኛው አገር አልፎ** ወ... **ወደ ኤፌሶን መጣ፡... አንዳንድ ደቀ መዛሙርትንም** አገኘ፡

**እንዲህም አላቸው፡ ባመናችሁ ጊዜ መንፈስ ቅዱስን ተቀበላች**ሁን?...

151 አሁን፡ አንተ ውድ የባፕትስት እምነት ወዳጅ ሆይ፡ ሙሉ ለሙሉ የሰነ መለኮት ትምህርት**ህን** የሚፈታተን ካልሆነ ተመልከት፡ በተለይ "ባመናችሁ **ጊዜ** መንፈስ ቅዱስን ትቀበላላችሁ" ትላላችሁና።

152 ነገር ግን ጳውሎስ እነዚህን ባፒትስቶችን እንዲህ ብሎ መጠየቅ ፈለገ፡ "ባመናችሁ **ጊዜ** መንፈስ ቅዱስን ተቀበላችሁን? " አሁን የመለሱትን ተመልከቱ፡

**... አልተቀበልንም፡ መንፈስ ቅዱስ እንዳለ... ሰንኳ** አልሰማንም **አሉት።**

**እርሱም እንዲህ አላቸው፡ እንኪያ...** (አሁን፡ የግሪክ መዝገበ ቃላት ማየት ከፈለጋችሁ፡ አሳያችኋለው፡ "እንኪያ **እንዴት** ተጠመቃችሁ? ")... **እንኪያ እንዴት... ተጠመቃችሁ** አላቸው? **እነርሱም፡** በዮሐንስ ጥምቀት አሉት። ዮሐንስ አጠመቀን።

153 አሁን ልጠይቃችሁ የምፈልገው ነገር ቢኖር፡ እንዲህ ዓይነት ጥምቀት ቢታገኙ፡ በዚያ ትረካላችሁ? ኢየሱስን ከወንዙ ውስጥ ያወጣውና፡ ኢየሱስ ክርስቶስን ያጠመቀው፡ ያው ሰው እነዚህን ሰዎች ያጠመቃቸው እርሱ ነው። ያ በጣም ጥሩ ጥምቀት ነው፡ መርጬት አይደለም፡ ማፍሰስ አይደለም፡ ነገር ግን ኢየሱስ በተጠመቀበት በዚያው የድሮ ጭቃማ የዮርዳኖስ ወንዝ ውስጥ መጥለቅ ነው። እስቲ አስቡበት።

154 ጳውሎስ፡ "ከማመናችሁ በኋላ መንፈስ ቅዱስን ተቀብላችኋል? " አላቸው... እነርሱ...

እንዲህ አሉ፡ "አልተቀበልንም... መንፈስ ቅዱስ እንዳለ ሰንኳ አልሰማንም" አሉት።

እርሱም፡ “እንኪያ በምን ተጠመቃችሁ” አላቸው?

እነርሱም፡ “ተጠምቀናል” አሉ።

“እንኪያ በምን ተጠመቃችሁ? ”

“በዮሐንስ ጥምቀት!”

155 አሁን ጳውሎስ የተናገረውን ተመልከቱ። እዚህ ተመልከቱ፡

> **እርሱም እንዲህ አላቸው፡...** **በ**ዮሐንስ ጥምቀት-... **ነውን**... ከእርሱ በኋላ...
>
> **ከእርሱ** በኋላ **በሚመጣው፡ በኢየሱስ ክርስቶስ ያምኑ...** ዘንድ-... **ለሕዝብ፡ እ... እየተናገረ፡ ... በንስሐ፡ ጥምቀት፡ አጠመቃቸው።**

156 አያችሁ፡ ዮሐንስ **ለ**ንስሐ ብቻ ያጠምቅ ነበር፡ ነገር ግን የውኃ ጥምቀት በኢየሱስ ስም ለኃጢአት ስርየት ነው። በወቅቱ የኃጢአት ስርየት ገና አልተደረገም፡ ኃጢአትም ሊሰረዝ አልቻለም ነበር። በ... በሕግ መሠረት፡ ስለ ኅሊና መልስ መስጠት ብቻ ነበር። ሉቃስ 16፡16 ላይ፡ እንዲህ ይላል፡ “ሕጉና ነቢያት እስከ ዮሐንስ ድረስ ተናገሩ፡ ከዚያ ጊዜ ጀምሮ የመንግሥቱ ወንጌል ይሰበካል።” አሁን ተመልከቱ። ተ... ተመልከቱ።

> ጳውሎስም **እንዲህ አለ-...** (አሁን ተመልከቱ)... **ተቀብላችኋል...**

157 5—5ኛ ቁጥር፡

> **ይህን**ም **በሰሙ ጊዜ፡** (እንደገና) በኢየሱስ ክርስቶስ ስም... **ተጠመቁ**

158 ልክ ነው? ከዚያም እነዚህ ሰዎች፡ በሐዋርያት ሥራ 2 ላይ የተጠቀሱት ሰዎች፡ የተጠመቁት በኢየሱስ ስም ነው። አይሁዶች በኢየሱስ ስም ተጠመቁ። አሕዛብ በኢየሱስ ስም ተጠመቁ። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ያሉት ሁሉም ሰዎች በኢየሱስ ስም ተጠመቁ።

159 አንድም ሰው በሌላ መንገድ የተጠመቀበት አንድ ቦታ ካለ ፈልጉ፡ ወደዚህ ተመልሼ የካቶሊክ ቤተክርስቲያን ይህን የቱ ጋር እንደተቀበለችውና፡ እናንተም እንሰግድላታለን ትላላችሁ። እንዲህም ትላላችሁ፡ “አንዳንድ ፕሮቴስታንቶች ሊድኑ የሚችሉት በካቶሊክ እምነት ውስጥ ያሉትን አንዳንድ ትምህርቶች በመያዛቸው፡ ‘የአባት፡ የልጅና፡ የመንፈስ ቅዱስ ስም’ ጥምቀት ስላላቸው ይመስላቸዋል’፥ ቅዱስ ካቶሊካዊት ቤተ ክርስቲያን ይህን ሥነ ሥርዓት ከኢየሱስ ስም ወደ፡ ‘አባት፡ ልጅና፡ መንፈስ ቅዱስ፡’ የመቀየር መብት እንዳላት የፕሮቴስታንት ቤተ ክርስቲያንም ትቀበላለች።” ይህም አልቀበልም፡ ከመጽሐፍ ቅዱስ ጋር እወግናለሁ። መጽሐፍ ቅዱስ እምናለው።

160 እንዲህ ትላላችሁ፡ “ወንድም ብራንሃም፡ ሰዎች ዳግመኛ እንዲጠመቁ ታዛለህን? ” በትክክል! ጳውሎስ እዚህ፡ አድርጎታልና።

161 አሁን ተመልከቱ፡ በገላትያ 1፡8 ላይ፡ ጳውሎስ ምን እንደተናገረ እንመልከት፡

## ... እኛ ብንሆን፡ ወይም ከሰማይ መልአክ፡ ምንም ወንጌልን ቢሰብክላችሁ... የተረገመ ይሁን።

162 ይሄውላችሁ፡ "እኛ ብንሆን ወይም መልአክ ብሆን።" ይህ ጳውሎስ፡ የተባለ ሰው፡ ወንድሜ ሆይ፡ እናንተ ከተጠመቃችሁት ጥምቀት በብዙ የሚሻል ጥምቀት የተጠመቁትን ሰዎች እንደገና እንዲጠመቁ አዘዘ፥ ምክንያቱም መጥምቁ ዮሐንስ ለኢየሱስ የአጎቱ ልጅ፡ ሁለተኛ የአጎቱ ልጅ ነበርና፥ የራሱን የአጎት ልጅ በዮርዳኖስ ወንዝ ያጠምቅ ነበር፡ ቀጥሎም ዞር ብሎ የዮሐንስን ደቀ መዛሙርት አጠመቀ። ኢየሱስም፡ "ይህ አይሠራም!" አለ ጳውሎስ ማለቴ ነው፡ ከጮኹና እግዚአብሔርን እያመሰገኑ ብዙ ጊዜም ካሳለፉ በኋላ፣ መንፈስ ቅዱስን ከመቀበላቸው በፊት በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ዳግመኛ እንዲጠመቁ አዘዛቸው፡ ኢየሱስ ክርስቶስ መሆኑን በ—በመጽሐፍ ቅዱስ (በሥነ መለኮታቸው) በማረጋገጥ፡ ታላቅ መነቃቃት እያሳዩ ሳለ ነው በግዳሜ እንዲጠመቁ ያደረገው። መጽሐፍ ቅዱስ መሆኑን ሰንቶቻችሁ ታውቃላችሁ? ምዕራፍ 18። በእርግጠኝነት ነው። ይኼውላችሁ። ምንም ጥያቄ የለውም።

163 አሁን ትንሽ ቁልፍ ማስታወሻ ልሰጣችሁ። ስለዚህ፡ ከስርዓት ወጥቶ አያውቅም፡ በሉቃስ ግን... የማቴዎስ ወንጌል፡ ምዕራፍ 16። ኢየሱስም፡ ከተራራው ከወረዱ በኋላ፡ እንዲህ አለ፡ "ሰዎች የሰውን ልጅ ማን እንደ ሆንሁ ይሉኛል? "

164 "አንዳንዶች 'ኤልያስ' ነህ ይላሉ፡ አንዳንዶች 'ነቢይ' ነህ ይላሉ፡ አንዳንዶች '**ይህ፡ ያ**' ይሉሃል።"

165 እንዲህም አላቸው፡ "እናንተስ ማን እንደሆንሁ ትላላችሁ? "

166 ጴጥሮስም፡ "አንተ ክርስቶስ፡ የሕያው እግዚአብሔር ልጅ ነህ" አለው።

167 ተመልከቱ! "ባር-ዮናስ (የዮና ልጅ) ስምዖን ሆይ፡ ብፁዕ ነህ፡ ሥጋና ደም ይህን ከቶ አልገለጠልህም።" አሜን!

168 እያችሁ፡ መንፈሳዊ መገለጥ መምጣት አለበት። አቤል እንደተሳሳተ (ቃየን፡ እንደሳተ)፡ "ቃየን እንደተሳሳተ" ለአቤል ሥጋና ደም በጭራሽ አልነገረውም። ነገር ግን አቤል ያገኘው መገለጥ ነበር፡ "ደም ነበር!" ወደዚያ ጥያቄ በጥቂት ደቂቃዎች ውስጥ እንመጣለን። እኛን ከኤደን ገነት ያሰወጣን፡ ፍሬ ሳይሆን፡ ደም ነበር። "ደም ነበር፡" አቤልም፡ ደም መሆኑን፡ ከእግዚአብሔር በተገለጠ መንፈሳዊ መገለጥ ተገለጠለት፡ እርሱም፡ "በእምነት፡" ዕብራውያን 11፡ 1 እንዲህ ይላል፡ "ከቃየል ይልቅ የሚበልጥ መሥዋዕትን ለእግዚአብሔር አቀረበ። ስለዚህም፡ እግዚአብሔር መሰዋዕቱን ተቀበለው።" ይሄው እናንተን። እያችሁ፡ በእምነት፡ በመገለጥ አቀረበ።

169 አሁን ተመልከቱ፡ "ሥጋና ደም ይህን አልገለጠልህም፡" (ለጌታ ኢየሱስ ተማረከ) "ነገር ግን በሰማያት ያለው አባቴ ይህን ገልጦልሃል። በዚህም ዓለት ላይ (በኢየሱስ ክርስቶስ መገለጥ ላይ)... በዚህች ዓለት ላይ ቤተ ክርስቲያኔን እሠራለሁ፡ የገሃነም ደጆችም አይችሏትም።" እሱ የተናገረው ይህን ነው። መንፈሳዊ መገለጥ-... "አንተ ጴጥሮስ ነህ፡ የመንግሥተ ሰማያት ቁልፎችን እሰጥሃለሁ። ምንም ይሁን ማን... በዚህና በሰማይ መካከል የተከፈተ መንፈሳዊ ቻናል አግኝተሃልና። ስጋና ደም አልገለጠልህም፡ ሴሚናሪ አልገባህም፡ ትምህርት ቤት አልገባህም፡ የ—የ—የሃይማኖት ትምህርት ቤት

አልገባህም። ነገር ግን በእግዚአብሄር ተደገፍክ፡ እግዚአብሄርም ገለጠልህ፡ ይህን የሚያይዝ ግልጽ የሆነው መጽሐፍ ቅዱስ ነው። እኔም እልሃለሁ፡ አንተ ጴጥሮስ ነህ፡ የመንግሥተ ሰማያትንም መክፈቻዋች እሰጥሃለሁ፣ በምድር የምታስረው ሁሉ፡ በሰማያት የታሰረ ይሆናል፣ በምድርም የምትፈታው፡ ሁሉ በሰማያት የተፈታ ይሆናል።"

170 ጴጥሮስም በጴንጤቆስጤ ቀን ቃል አቀባይ ነበረ፡ ሁሉም ለመናገር በፈሩ ጊዜ፡ ተናገረና እንዲህ አለ፡ "አይሁድ በኢየሩሳሌምም የምትኖሩ ሁላችሁ፡ ይህ በእናንተ ዘንድ የታወቀ ይሁን ቃሎቼንም አድምጡ። ለእናንተ እንደ መሰላችሁ እነዚህ የሰከሩ አይደሉም፡ ከቀኑ ሦስተኛ ሰዓት ነውና፡ ነገር ግን ይህ በነቢዩ በኢዩኤል የተባለው ነው። እግዚአብሔር ይላል፡ 'በመጨረሻው ቀን እንዲህ ይሆናል፡' 'ሥጋ በለበሰ ሁሉ ላይ ከመንፈሴ አፈሳለሁ። ወንዶችና ሴቶች ልጆቻችሁም ትንቢት ይናገራሉ። ደግሞም በዚያች ወራት፡ በወንዶችና በሴቶች ባሪያዎቼ ላይ፡ ከመንፈሴ አፈሳለሁ። ድንቆችን በላይ በሰማይ ምልክቶችንም በታች በምድር እሰጣለሁ፡ ደምም እሳትም የጢስ ጭጋግም ይሆናል። ታላቅ የሆነ የተሰማም የጌታ ቀን ሳይመጣ፡ የጌታን ስም የሚጠራም ሁሉ ይድናል።'" ይሄው። ኦህ፡ ማይ።

171 "ስለ አባታችን ስለ ዳዊት በነጻነት ልነግራችሁ እወዳለሁ፡" እንዲህ አለ፡ "ሞተም እንደ ተቀበረም፡ መቃብሩም እስከ ዛሬ በእኛ ዘንድ አለ። ስለዚህ፡ ነቢይ ስለ ሆነ፡ አስቀድሞም... በቀኙ እንደሆነ አይቶ፡ 'አልናወጥም። ስጋዬም በሰላም ታርፋለች ምክንያቱም ነፍሴን በሲኦል አይተዋትምና፡ ሥጋዬም መበስበስን አያይም'" ሲል ተናገረ።

172 "ዳዊትም ሞተ፡" እንዲሁም፡ "ተቀበረ፡ መቃብሩም እስከ ዛሬ በእኛ ዘንድ ነው። ነቢይ ስለነበረ፡ እግዚአብሔር ጌታም ክርስቶስም ያደረገውን፡ የጻድቁን መምጣት አስቀድሞ አይቷል።" ኦህ፡ ማይ። ይሄው ጥቅሳችሁ። ነገሩ ይህ ነው። ያ ነው በቃ።

173 ከዚህ በመነሳት፡ ትክክለኛው መንገድ፡ እውነተኛውን መንገድና፡ ከመጀመሪያ ጀምሮ የተዘጋጀውን ብቸኛውን መንገድ፡ እንገነዘባለን... ጴጥሮስ በሚሰብክበት ቀን፡ ቁልፎቹን ይዞ ነበር፡ አ... አሁን ተመልከቱ፡ የመጀመሪያዋ ቤተክርስቲያን እዚህ ጋር ጀመረች። እናንተ ካቶሊኮች ይህን ስሙ። እናንተ ካምቤሊቶች ይህን ስሙ። እናንተ ባፕቲስቶች እና ሜቶዲስቶች ይህንን ስሙ። እናንተ ጴንጤዎችም ይህን ስሙ። ቸርች ኦፍ ጋድ፡ ናዝራውያን፡ ፒልግሪም ሆሊነስ፡ ይህን ስሙ።

174 ጴጥሮስ ቁልፍ ነበረው፡ ደግሞ ሥልጣን ነበረው፡ ካልሆነ ግን ኢየሱስ ዋሽቷል ማለት ነው። እርሱ ይዋሽ ዘንድ አይችልምና፡ "ሁለት የማይለወጡ ነገሮች፡ እግዚአብሔር ሊዋሽ አይችልም።" ቁልፎቹ ነበሩት። ኢየሱስ ቁልፎችን ሰጠው። ኢየሱስ በ—በሦስተኛው ቀን ተነሣ፡ የሞትና፡ የሲኦል ቁልፎች ይዞ ነበረ፡ የመንግስተ ሰማያት ቁልፎች ግን ከሱ ጋር አልነበሩም። ጴጥሮስ ጋር ነበሩ! በትክክል።

175 አሁን ተመልከቱ፡ ጴጥሮስ ሆይ፡ ቁልፎቹ ከጎንህ ተንጠልጥለዋል፡ አንተም እየሰበክህ ነህ። ጥያቄው የሚነሣው፡ ከአዲሲቱ ቤተክርስቲያን የመጀመሪያ ተከታዮች ነው። የጥንቷ የክርስቲያን ቤተክርስቲያን። አሁን ካቶሊክ፡ ባፕቲስት፡

ሜቶዲስት፡ ፕሪስባይቴሪያን፡ በአዲስ ቤተክርስቲያን አስተምህሮ ላይ ናችሁን? መሆናችሁን አረጋግጡ።

> … ሰዎች **እና ወንድሞች ሆይ፡ ምን እናድርግ? አሉአቸው**
>
> … **ጴጥሮስም** ተነሥቶ እንዲህ **አላቸው… ንስሐ ግቡ፡… እያንዳንዳችሁም…** (ተመልከት፡ አንተ ልጅ፣ አንተ እነዚህን ቁልፎች የምታስቀምጥበት መንገድ፡ ክርስቶስ በሰማይ ያጸድቀዋል) … **ንስሐ ግቡ፡** እያንዳንዳችሁም፡ **በኢየሱስ ክርስቶስም ስም ተጠመቁ…** (ወደዚህ መግቢያው መንገድ ይህ ነው) … ለኃጢአታችሁም **ስርየት በኢየሱስ ክርስቶስም ስም ተጠመቁ፡ የመንፈስ ቅዱስን ስጦታ ትቀበላላችሁ።**

176 ቁልፎቹ እዚህ ጋር “ገጭ”፡ እዚያ ጋርም “ገጭ” አሉ። ለዚህም ነው የዮሐንስ ደቀ መዛሙርት መጥተው፡ እንደገና፡ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም መጠመቅ የነበረባቸው (ወደ መንግሥተ ሰማይ ከመግባታቸው በፊት የተጠመቁት)፡ መንፈስ ቅዱስን ለማግኘት። ቃሉን ጠበቀ። ስለዚህ አሁን እያደናግራችሁም፡ አይደል? እያችሁ? በእርግጠኝነት፡ ማቴዎስ 28:19 ላይ ያሉት መጠሪያዎች እንጂ፡ ስም አልነበሩም።

177 መልካም፡ ምን ያህል ጊዜ አለን? ሁለት ተጨማሪ ጥያቄዎችን በፍጥነት ለመመለስ አስራ አምስት ደቂቃ ይኖረን ይሆን? እንችላለን? መልካም፡ በፍጥነት እንጣደፋለን። እዚህ ጋር ከሰር ሁለት አሉብኝ፡ ከቻልኩ፡ ከዚህ ጋር በቀጥታ ለመቀላቀል፡ በፍጥነት ለመድረስ እፈልጋለሁ። ከዚያ የቀሩትን እሁድ ጠዋት እመልሳቸዋለሁ።

**57. ቃየን የእባቡ ዘር ነበርን?** (ይህ ጥሩ ጥያቄ ነው።) **ከሆነ፡ሔዋን አዳም እስከሚያውቃት ድረስ ለምን አልጸነሰችም?**

የ… የሚቀጥለው ጥያቄ ተመሳሳይ ነው፡-

**58. ሔዋን ፍሬውን የ—የበላችበት ዛፍ እውነተኛው ዛፍ ነውን? ለመብላትም ያማሬ እንደሆነ ተመልክታለችና።**

178 እሺ፡ ወንድሜ፡ እኅቴ፡ ማንም ሁን፡ ተመልሰን ወደ ዘፍጥረት እንሂድና አንድ ነገር እንመልከት። ፍቃደኛ ከሆናችሁ፡ ወደ ዘፍጥረት 3፡8 እንሂድ። እሺ፡ አሁን በደምብ አዳምጡ።

179 አሁን ታሪኩን አመጣዋለሁ። ነገር ሁሉ ንጹህና ቅዱስ ነበር፡ ኃጢአት ወይም እድፈት አልነበረም። አሁን… የመጀመሪያ… ጥያቅያችሁን እመልሳለሁ። በህይወት ዛፍ ውስጥ… በገነት መካከል፡ በዛፉ መካከል። **ዛፉ** “ሴትየዋ” ነበረች። አሁን ለጥቂት ደቂቃዎች ብቻ ከታገሳችሁ በቅዱሳት መጻሕፍት አረጋግጥላችኋለሁ።

180 ከአዳም ጋር ከ… ከመገናኘቷ በፊት ፀነሰች ወይስ አልፀነሰችም የሚለውን በቅድሚያ እናያለን፡ ወይም… አዳምጡ፡

> **እነርሱም ቀኑ በመሸ ጊዜ፡ የእግዚአብሔርን የአምላክን ድምፅ ከገነት ውስጥ ሲመላለስ ሰሙ፡ አዳምና ሚስቱም ከእግዚአብሔር ከአምላክ ፊት በገነት ዛፎች** መካከል **ተሸሸጉ።**

**እግዚአብሔር አምላክም... አዳምን ጠርቶ፡ ወዴት ነህ? አለው...**

**እርሱም አለ፡ በገነት ድምፅህን ሰማሁ፡ ዕራቁቴንም፡ ስለ ሆንሁ ፈራሁ፣...** (አሁን፡ ከትናንት በፊት አላወቀም ነበር፡ የሆነ ነገር ተፈተረ፡ ራቁቱን እንደሆነ ተገለጠለት) **ተሸሸግሁም።**

**እግዚአብሔርም አለው፡ ዕራቁትህን** እንደ **ሆንህ ማን ነገረህ?** ከእርሱ **እንዳትበላ ካዘዝሁህ ዛፍ በውኑ በላህን፡... ?**

181 ከዛፉ መብላቱ እርቃኑን እንዲገነዘብ ያደርገዋልን? ብዙ ጊዜ እንዳልኩት፡ (ይህ ቀልድ አይደለም፡ ለቀልድ አይደለም የምለው) "ነገር ግን አፕል መብላት ሴቶች እርቃናቸውን መሆናቸውን እንዲገነዘቡ ካደረጋቸው፡ አፕል እንደገና ብንሰጣቸው ይሻላል።" አያችሁ? እርቃን አልነበረም። የበሉት ዛፍ አልነበረም፡ አፕል አይደለም፡ ነገሩ ወሲባዊ ነበር። ተመልከቱ፡

... **ከእርሱ እንዳትበላ ካዘዝሁህ ዛፍ በውኑ** በላህን?

**አዳምም አለ፡ ከእኔ ጋር እንድትሆን፡ የሰጠኸኝ ሴት፡ እርሰዋ ከ... ከዛፉ** ሰጠችኝና፡ **በላሁ።**

**እግዚአብሔር አምላክም... ሴቲቱን፡ ይህ** ያደረግሽው **ምንድር ነው? አላት። ሴቲቱም አለች፡ እባብ፡ አሳተኝና፡...** (ኧሃ? )... **እባቡ አሳተኝና፡ በላሁ።** (ከአዳም ከመፀነሷ፡ ከረጅም ጊዜ በፊት፡ አያችሁ።)

182 አዳምም አወቃት፡ ፀነሰችም አ—አቤልንም ወለደች።

183 ነገር ግን ቃል በቃል አንጻር፡ ልጠይቃችሁ እፈልጋለሁ። አሁን እሷ ዛፍ መሆኗን ላረጋግጥላችሁ፡ እያንዳንዱ ሴት የፍሬ ዛፍ ናት። ይህን ስንቶቻችሁ ታውቃላችሁ? የእናታችሁ ፍሬ አይደላችሁምን? በእርግጠኝነት፡ ናችሁ። "በፍሬው መካከል፡ ወይም በዛፉ መካከል፡ የማትነካው ፍሬ ነበረች።"

184 ካስተዋላችሁ፡ ኢየሱስስ የሕይወት ዛፍ አልነበረምን? በቅዱስ ማቴዎስ፡ ወይም፡ በቅዱስ ዮሐንስ፡ ምዕራፍ 6 ላይ፡ "እኔ ከሰማይ ከእግዚአብሔር ዘንድ የመጣሁ የሕይወት እንጀራ ነኝ ብሎ ተሰፋ አልሰጠምን? "

185 ወንድ ከሴቲቱ ዘንድ ቢበላ... እና ተመልከቱ፡ ከሴቲቱ... በመወለዳችን ምክንያት፡ ሁላችንም ሟች ነን፥ ምክንያቱም በሴቲቱ መወለድ ምክንያት (ትክክል ነው? ) ለሞት ተዳርገናል። በሰው ልጅ መወለድ ምክንያትም፡ ሁላችንም ለዘላለም እንኖራለን። ሴትየዋ የሞት ዛፍ ናት፡ ወንዱ የሕይወት ዛፍ ነው፣ ሴቲቱ ውስጧ ሕይወትን እንኳን አይኖራትምና። ይህ ትክክል ነው። የ—የህይወት ዘር ከሰውየው ይወጣል፡ በትክክል። ወደ ሴቲቱም ይገባል፡ ሴቲቱ ከማቀፊያነት በስተቀር ሌላ ነገር አይደለችም፣ ህፃኑ ከእርሷ ጋር አይገናኝም፡ እምብርት ብቻ ነው የሚገናኘው። በሕፃኑ ውስጥ የእናትየው ደም አንድም ቅንጣት እንኳ የለም፣ በደሟ የተወለደ ነው፡ ነገር ግን በሕፃኑ ውስጥ አንዲት ነጥብ **አይገባም**። ሂዱ... ወይም የዶክተር መጽሐፍ አንብቡ፡ ወይም ዶክተራችሁን ጠይቁ፡ ታያላችሁ። የእናት ደም በህጻኑ ውስጥ፡ አይ፡ ወዳጄ፡ ከነጭራሹ አንድ ነጥብ እንኳ የለም። እሷ እንቁላል ብቻ ነች፡ ያ ነው በቃ። ሕይወትም የሚመጣው ከወንድ ነው።

186 ያ በሴቲቱ በኩል በተፈጥሮ በመወለድ፡ ሁላችንም መሞት እንዳለብን፡ የሚያሣይ የሚያምር ጥላ ነው፡ ምክንያቱም ከመጀመሪያው ሞተን ነበርና፡ በሕይወት የምንኖረው በክርስቶስ ኢየሱስ በኩል ብቻ ነው። ስለዚህ በኤደን ገነት ውስጥ ሁለቱ ዛፎች አሉ። አይታያችሁምን?

187 ተመልከቱ! በዚያም ቀን ይህን ዛፍ የሚጠብቅ ኪሩቤል ተመድቦ ነበረ። ያንን የሕይወት ዛፍ ከቀመሱ፡ ሁሉም ለዘላለም ይኖራሉ። ሰንቶቻችሁ ታውቃላችሁ? ሁሉም ለዘላለም ይኖራሉ። ለመጀመሪያ ጊዜ ሊቀምሱት... መልአኩም እንዲህ አለ፡ "እንጋርደዋለን።" ይጠብቁት ዘንድ በዚያ የሚንበለበሉትን ሰይፎች የያዙ ኪሩቤሎች ወደ ምሥራቅ አደረጉ። ወደ ምስራቅ ወሰዱትና፡ ያንን ዛፍ (ይህን ዛፍ) ማግኘት እንዳይችሉ በእሳት ሰይፍ ጠበቁት።

188 ኢየሱስም በመጣ ጊዜ፡ እንዲህ አለ፡ "የሕይወት እንጀራ እኔ ነኝ፡ ከዚህ እንጀራ የሚበላ ሰው ለዘላለም አይሞትም።" ዛፉችሁ ይኸው ነው።

189 ይቺት ሴቲቷችሁ፡ ሞትን የሚያመጣው ወሲባችሁም ይህ ነው። የጾታ ፍላጎት እስካለ ድረስ፡ ሞትም እንደሚኖር የታወቀ ነው። መንፈሳዊ መወለድ እንዳለ ሁሉ፡ ዘላለማዊ ሕይወትም አለ ማለት ነው። ሞት የሚመጣው ከሴት በመወለድ ሲሆን፡ ሕይወት የሚመጣው ደግሞ ከወንድ በመወለድ ነው። አሜን! አያችሁ።

190 አሁን ወደ ቃየን እንመለስ። ያ መንፈስና ያ ተንኮል ከየት እንደመጣ ልትነግሩኝ ትችላላችሁ? ተ... ተመልከቱ፡ ቃየን የእግዚአብሔር ልጅ ከሆነው ከአዳም የተወለደ ልጅ ከሆነ፡ ያ ክፋት ከወዴት መጣበት? በተወለደበት ጊዜ የመጀመሪያው ነገር፡ ጥላቻ አሳየ፡ ገዳይ ነበር፡ ምቀኛ ሆነ። አሁን የአባቱን ተፈጥሮ ተመልከቱ፡ ከመጀመሪያ ከጅምሩ፡ ሉሲፈር፡ እርሱም ከመጀመሪያም... በሚካኤል ላይ ቀናበት፡ ያ ነው ሁሉንም ችግር ያስጀመረው። ሰንቶቻችሁ ታውቃላችሁ? ቃየንም በወንድሙ ቀንቶ የገደለው፡ የአባቱ ባሕርይ ስለሆነ ነው። ከዚያ ንጽሕና... ያ ተፈጥሮ ከዚያ ንጹህ ጅረት ሊወጣ አይችልም። ከ... ከዚህ ጠማማ ጅረት መውጣት ነበረበት። ቃየንም ልክ እንደተወለደ፡ ይህን አስተውሉ።

191 ከዚያ አቤል ከእርሱ በኋላ ተወለደ፡ ከዚያም በኋላም ከአዳም ፀነሰች። እርሱም እ—አወቃትና ልጅንም አቤልን ወለደች። አቤልም የክርስቶስ ምሳሌ ነበር፣ እ—አቤል በተገደለ ጊዜ፡ ሴት የእሱን ስፍራ ተካ፣ ይህ የክርስቶን ሞት፡ መቀበርንና፡ ትንሣኤውን፡ በጥላ ያሳያል።

192 ነገር ግን፡ አሁን፡ ይህ ቃየን አምልኮ አቀረበ፣ ሥጋዊ ሥራዎቹ ሁሉ፡ ልክ እንደ ዛሬ ሥጋዊ ቤተ ክርስቲያን ነው፡ ወደ ቤተ ክርስቲያን ይሄዳሉ፡ ያመልኩታል። ቃየን አመለከ፣ እሱ አምልኮ የማያውቅ አልነበረም፡ ኮሚኒስት አልነበረም። ቃየን አማኝ ነበር፣ ወደ እግዚአብሔር ሄደ፡ መሠዊያም ሠራ። አቤል ያደረጋቸውን ሃይማኖታዊ ነገሮች ሁሉ አድርጓል፡ ነገር ግን የእግዚአብሔር ፈቃድ መንፈሳዊ መገለጥ አልነበረውም። የጌታ ሰም የተባረከ ይሁን! አያችሁ። አያችሁ? መንፈሳዊ መገለጥ አልነበረውም፡ ዛሬም የቤተክርስቲያን ችግር ይህ ነው። ኢየሱስ ቤተክርስቲያኑን በዚያ መንፈሳዊ መገለጥ ላይ እንደሚሰራ ተናግሯል።

ተረድታችኋል? ኦህ፡ ማይ፡ አይኖቻችሁ አሁን ሊከፈቱ ይችላሉ። አያችሁ፡ መንፈሳዊ መገለጥ።

193 ቃየን መጥቶ፡ መሠዊያ ሠራ፡ አመለከም፡ መሥዋዕትንም አቀረበ፡ ተንበረከከ፡ እግዚአብሔርን አመሰገነ፡ እግዚአብሔርን አመለከ፡ አቤል ያደረገውን ሃይማኖታዊ ነገር ሁሉ አደረገ። መንፈሳዊ መገለጥ ስላልነበረው እግዚአብሔር በፍጹም አልተቀበለውም!

194 ያንኑ የቃየንን መንገድ፡ እስከ መርከቡ ድረስ፡ ከመርከቡም እስከ እስራኤል ድረስ፡ ከእስራኤል እስከ ኢየሱስ ድረስ፡ ከኢየሱስም እስከ ዛሬ ድረስ ተከትለውታል፣ ይህች ሥጋዊ፡ ወግ አጥባቂዋ፡ ደንዳና እና ግትር የሆነች፡ ምሁራዊት ቤተ ክርስቲያን ተመልከቷት፡ ማለትም ቅዱሳት መጻሕፍትን የያዙ፡ ትምህርቱንና ሥነ መለኮቱን ሁሉ የሚያውቁ ሰዎች ያሉባት፡ ልክ **እንደዛው**፡ ሊያብራሩት ይችላሉ፡ ወዳጄ፡ ነገር ግን መንፈሳዊ መገለጥ ካልተገለጠላቸው በስተቀር! [ወንድም ብራንሃም በጣቱ ምልክት በማሳየት አይቻልም አለ—አርታዒ።] በትክክል። ይህ የቃየን ትምህርት ነው።

195 መጽሐፍ ቅዱስም፡ “ወዮላቸው! የቃየንን ትምህርት ተከተሉ፡ በበለዓምም ስህተት ዘነበዱ፡ በቆሬም ዓመፅ ጠፍተዋልና” ይላቸዋል። ያው መጽሐፍ፡ ይሁዳ፡ እንዲህ አለ፡ “ለዚህ ጥፋት አስቀድሞ ተወስነዋል።” በእርግጠኝነት፡ ተወስነዋል። አያችሁ? በለዓም ምን ነበር? ቢሾፕ ነበር። እርሱ በቤተ ክርስቲያን ሁሉ የበላይ ነበረ። ወግ አጥባቂ መሆን በሚችለው ሁሉ ሆኖ ነው የመጣው። በ... በዝናው ታዋቂነት ቆሞ ተመልከቱት፡ በታላቁ ታዋቂነት ቆሟል። እነሱም እምነት አልባ አልነበሩም፡ አማኞችም ነበሩ።

196 ከሎጥ ሴት ልጅ የመጣ ያ—የሞዓባውያን ነገድ። ከ... ከአባቷ ጋር ትኖር የነበረችው የሎጥ ልጅ፡ ፀነሰችና ልጅ ወለደችለት፡ የ... የሞዓብ ነገድ ተወለደ። ታላቅ የሃይማኖት ተቋም ነበሩ። ታላላቅ፡ አበቦች ያፈሩ ሕዝቦች፡ መኳንንትና ነገሥታትና ዝነኞች ነበሯቸው። ጳጳሳት እና ካርዲናሎችና ሁሉም ነገር ነበሯቸው።

197 በሌላ በኩል ደግሞ፡ እስራኤል፡ የሆሊ ሮለሮች መንጋ መጣች፥ ከሃይማኖት ተቋም ውጪ የሆነች፡ የሃይማኖት ልዩነት የሌለባት ትንሿ የመጀመሪያዋ መንጋ። እና በካርታው ላይ ያገኙት ነገር ሁሉ አደረጉ፡ መጥፎም ጭምር። ነገር ግን ምን ነበራቸው፡ መንፈሳዊ መገለጥ ነበራቸው፡ እግዚአብሔርም ከእነርሱ ጋር በእሳት ዓምድ ውስጥ ነበር።

198 ኦህ፡ ሥጋዊ ነገር እ—እንደነበራቸው አውቃለሁ፡ ሰዎቹም እንዲህ አሏቸው፡ “እነዚህ የማይጠቅሙ ሰዎች፡ እነሱን ውጪ ከመጣል በስተቀር ምንም ለምንም አይጠቅሙም።” ነገር ግን መንፈሳዊ መገለጥ ነበራቸው፡ የተመታ አለት ነበራቸው፡ የናስ እባብ ነበራቸው፡ ከእነርሱ ጋር የሚሄድ የእሳት ዓምድ ነበራቸው። ሃሌ ሉያ! ሞቅ ሞቅ ብሎታል ብላችሁ እንደምታስቡኝ—አውቃለሁ፡ ግን አይደለም። ደስ ሰላለኛ ነው።

199 አስተውሉ! “ያው አምላክ፡ ዛሬም፡ ከእኛ ጋር እንዳለ፡” ሳስብ። ዛሬም በቃሉ መንፈሳዊ መገለጥ ነው። በእርግጠኝነት፡ ነው። ለዘላለም ትክክል ነው። የጌታ ስም የተባረከ ይሁን! አዎን፡ ወዳጄ።

200 ይሄው ወግ አጥባቂዎቹ፡ ማዶ ላይ ቆሟል፥ ባፒቲስቶችና የፕሬስባይቴሪያን መንጎች በኮረብታው ላይ ቆመው፡ ቢሾፓቸውን ተራራው ጫፍ ላይ አወጡ። ሃይማኖተኞች ናቸው፡ ሃይማኖታቸው አንድ አይነት ነበረ። አንድ አምላክን ያመልካሉና። እንዲህ አሉ፡ "እነዚህ እርባና ቢሶቹን ተመልከቷቸው። ይኸውላችሁ፡ የሃይማኖት ተቋም እንኳን የላቸውም። ዝም ብለው ይጮኻሉ፡ የማይረቡ፡ ሆሊ ሮለሮች ናቸው።"

201 ልክ ነው? በትክክል፡ እንደዛ ነበሩ። ሆሊ ሮለቶች እንደነበሩ ካላመናችሁ፡ በዘፍጥረት ውስጥ ተመልሳችሁ ሲሻገሩ እንዴት እንደሆኑ እዩአቸው። ተአምርም በሆነ ጊዜ፡ ማርያም ከበሮ ይዛ ወደ ባህር ዳር ወረደች፡ ከበሮውን እየመታች፣ በመንፈስ ተንቀሳቀሰች፡ ሙሴም በመንፈስ ሲዘምር ነበር። ያ የሆሊ ሮለር ስብሰብ ካ… ካልሆነ፡ መዘመርና መዝለልና ማመስገን፥ ምን እንደሆነ አላውቅም። ሁልጊዜም አሕዛብ ይጠሏቸው ነበር፡ እግዚአብሔር ግን ከእነርሱ ጋር ነበረ። መንፈሳዊ መገለጥ ነበራቸው፡ ያንን የእሳት ዓምድ እየተከተሉ ነበርና።

202 ሞዓብም እንዲህ አለ፡ "አሁን፡ ተመልከቱ። ካርዲናሎች እና ጳጳሳት ሁሉ እንጠራቸዋለን፡ ፕሪስባይተሮችን ሁሉ፡ እናመጣቸዋለን። አንድ ነገር እናደርጋለን፡ ምክንያቱም እኛ ሃይማኖተኛ ሕዝብ ነን። ያንን ፕሮፓጋንዳ ከተወደደው የሃይማኖት ተቋማችን ጋር እንዲቀላቀል አንፈቅድም አሉ።"

203 በመቀጠልም ወደዚያ አወጧቸው። አሥራ ሁለትም መሠዊያዎች ሠሩ፣ አሥራ ሁለት መሠዊያዎች፡ ልክ እንደ እስራኤል። በላዩም ወይፈኖች፡ አሥራ ሁለት መሥዋዕት አቀረቡ፣ ልክ እንደ እስራኤላውያን፡ እግዚአብሔር ከእነርሱ የሚፈልገውን አይነት። የጌታን የኢየሱስ ክርስቶስን መምጣት የሚወክሉ፡ አሥራ ሁለት በጎችን አኖሩበት፣ በሁሉም ቦታዎች አሥራ ሁለት በጎች።

204 ሁሉም ታዋቂ ሰዎች፡ ጳጳሳቱና ሁሉም፡ በዙሪያው ቆሙ። መስዋዕቱን እሳት ጨመሩበት። ጸለዩ፡ እጆቻቸውንም ወደ ይሖዋ አነሡተው፡ "ይሖዋ ሆይ፡ ስማን!" ምን ለማድረግ እየሞከሩ ነበር? በልዓማቸውም እንዲህ እየሆነ ወጣ፡ መንፈስም በእርሱ ላይ ወረደ። በትክክል (ነገር ግን ሥጋዊ ነበር)።

205 መንፈስ በግብዝ ላይም ሊወርድ ይችላል፡ ይላል መጽሐፍ። መቼም፡ ያንን ሳስተምር ሰምታችኋል። "ዝናብ በጻድቃንና በሃጥያተኞች ላይም ይወርዳል።" ነገር ግን ከቃሉ ጋር መስተያየት አለበት፡ ልዩነቱን የምታገኙት እዚያ ጋር ነውና።

206 ከዚያም ሲወርድበት፡ ቢሆንም፡ መ… መንፈስ በእርሱ ላይ፡ እውነትን በተናገረ ጊዜ፡ እስራኤልን ሊረግም ሞከረና፡ እስራኤልንም ባረከ።

207 እንግዲህ፡ እግዚአብሔር መልካም ቤተ ክርስቲያንንና፡ ጥሩ ጳጳስንና፡ ድንቅ ፓስተርን፡ የምሁራን ጉባኤ አክባሪ ከሆነ፡ ያንን መስዋዕትም የመቀበል ግዴታ ነበረበት፡ ምክንያቱም እርሱም ልክ እንደ እስራኤል ትክክል ነበር፣ ነገር ግን የቃሉ እና የእግዚአብሔር ፈቃድ መንፈሳዊ መገለጥ አልነበረውም። አያችሁ፡ ዛሬ ያለው ልዩነቱ ያ ነው።

208 ኢየሱስን ተመልከቱት። እንዲህም አሉት፡ "ከዚያ ሰው ራቁ። ሳምራዊ መሆኑን እናውቃለን። እብድ ነው። አንተ እኛን ታስተምራለህን? አንተ'ኮ፡ በዝሙት ነው የተወለድከው። አንተ ዲቃላ ነህ እንጂ ሌላ ነገር ምን አለህ። አባትህ ማን ነው? እግዚአብሔር አባቴ ነው ትላለህ፡ አንተ ተሳዳቢ! ደግሞ፡

እኛን ትናገራለህን? እኛ ሰባኪዎች፡ ጳጳሳት ሆነን የኖርን፥ በቅድመ-ቅድመ-ቅድመ-ቅድመ-ቅድመ-ቅድመ-ቅድመ-አያቶቻችን ሰባኪዎችና ጳጳሳት ነበርን። ተወልደን ያደግነው በቤተክርስቲያን ነው። ከፍተኛውን ሴሚናሮች ውስጥ አልፈናል። እያንዳንዱን ቃል እናውቃለን። እኛን ለማስተማር ትሞክራለህን? የት ትምህርት ቤት ገብተህ ታውቃለህ? ይህን ትምህርት ያገኘኸው ከየት ነው?

209 እርሱም፡ "እናንተ ከአባታችሁ... ከዲያብሎስ ናችሁ፡" አለ ኢየሱስ።

210 በመካከላቸውም ምልክትና ድንቅ ነገር አልነበራቸውም። በመካከላቸው መለኮታዊ ፈውሶች እና ነገሮች አልነበራቸውም። በመካከላቸው ምንም በረከት አልነበራቸውም። ኢየሱስ ግን ፍጹም መንፈሳዊ የቅዱሳት መጻሕፍት መገለጥ ነበር።

211 እንዲህም አሉ፡ "ለምን፡ **እንዲህ-እና-እንዲያ** ተጽፏል።"

212 ኢየሱስም፡ "አዎን፡ እንዲህም ደግሞ ተጽፏል።" እግዚአብሔር ግን የራሱን ሰው በምልክቱ አጸደቀ።

213 ጴጥሮስም እንዲሁ፡ በሐዋርያት ሥራ 2 ላይ፡ እንዲህ አለ። "የእስራኤል ሰዎች ሆይ፣ ይህን ቃል ስሙ ራሳችሁ እንደምታውቁ፡ የናዝሬቱ ኢየሱስ፡ እግዚአብሔር በመካከላችሁ በእርሱ በኩል ባደረገው ተአምራትና ድንቆች፡ በምልክቶችም ከእግዚአብሔር ዘንድ ለእናንተ የተገለጠ ሰው ነበረ።" (ይሄው) "እሱ ነፃ ሲወጣ... በ-... በዚያ በነበረው ታላቁ የሳንሄድሪን ምክር ቤት። በእግዚአብሔር ግን በቀድሞ እውቀቱ እግዚአብሔር በዚህ ሞት እንዲሞት አስቀድሞ ወስኗል። በዓመፀኞች እጅና በክፉ እጆች አሳልፋችሁ ሰጣችሁት። እግዚአብሔር ያስነሣውን፡ የሕይወትን ልዑል ሰቀላችሁት። ለዚህም ምስክሮች ነን።"

214 ኸረ እንዴት ያለ፡ ሰባኪ ነው! የ—የራሱን ስም እንኳ መፈረም የማይችል፡ ነገር ግን እግዚአብሔርን ያውቅ ነበር። እነሱም "ከኢየሱስ ጋር እንደ ነበረ ተገነዘቡ።" በእርግጠኝነት፡ መንፈሳዊ መገለጥ ነው። ኦህ፡ ማይ። አሁን፡ ተመልከቱ።

215 ቃየን በዚያኛው መንገድ ነበር፡ ያ ሥጋዊ ቤተ ክርስቲያን ዛሬም በተመሳሳይ መንገርድ ላይ ትገኛለች። መንፈሳዊቷ ቤተ ክርስቲያን ግን አሁንም የእሳት አምድ አላት፡ አሁንም ምልክቶች፡ ድንቆች፡ አሁንም ያው ክርስቶስ አላት፣ ይህም በኤደን ገነት ከሚሞተው በግ አንሥቶ፡ እስከ የበጉ ሁለተኛ ምጽአት ድረስ ያለውን መንገድ ሁሉ፡ የሚያረጋግጥ ነው። በእርግጠኝነት፡ ትናንት፡ ዛሬና፡ ለዘላለም ያው ነው።

216 የቃየን መንገድ፡ ሃይማኖታዊነት እና የተጣራ ምሁራዊነት፡ በተዋረድ በትክክል ተመሳሳይ ሆኖ መጣ፣ ተመሳሳይ ነው፡ በየቀኑ ተመሳሳይ ነው። ተቺዎች እና አሳዳጆች፡ ቃየን በአቤል ላይ እንደነበረው ሁሉ፡ ዛሬም እንዲሁ ናቸው። ሥጋውያን፡ የማያምኑ ነበሩ፡ ወደፊትም ይኖራሉ። በትክክል።

217 አሁን ዘፍጥረት 3፡8፡ ደግሞም 20 እዚህ ይዤዋለሁ፡ ከጥቂት ጊዜ በፊት እያየሁት ነበር፡

**አ... አዳምም** ሚስቱን... **ሔዋን ብሎ ጠራት፥ የሕያዋን ሁሉ እናት ነበረችና።** (አያችሁ፡ ይህ ሁሉ ስህተት ከተደረገ በኋላ ነበር)

218 ቃየን… “አሁን ቆዩ!” ትላላችሁ፡ “እባብ፡ እፉኝት እንዴት እንዲህ ሊሆን ይችላል? ”

219 ነገር ግን፡ ወንድሜ፡ እዚህ ተመልከት፡ መጽሐፍ ቅዱስ እባብ ነበር አይልም፣ መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይላል፡ “ከምድር አውሬ ሁሉ ይልቅ ተንኰለኛ ነበረ።” እሱ ተሳቢ እባብ አልነበረም፡ አውሬ ነበር። እሱ እ… እዚያ…

220 ፍቃደኛ ከሆናችሁ፡ በመካከላችን ትንሽ ምልክት ልሰጣችሁ። ሳይንሰ ግራ የተጋባበት ቦታ ይህ ነው። ለሰው ልጆች በጣም ቅርብ ሆኖ ያገኙት ነገር፡ ቺምፓንዚ ነው። ሰንቶቻችሁ ታውቃላችሁ? በዚያ መካከል ግን የሆነ ነገር አለ። እጅግ የቀረበው ቢሆንም፡ የቺምፓንዚ አጥንቶች ከሰው አጥንት ጋር እንዲገናኙ ማድረግ አይችሉም። ከእንቁራሪት ትል ሊያሳድጉት ይችላሉ። ከእንቁራሪት እጭ ሊያሰጀምሩት ይችላሉ። ወደ እንሰሳ ወደ እያንዳንዱ እንሰሳ ሊያሸጋግሩ ይችላሉ። ወደ ድብ ሊያሳድጉት ይችላሉ። ድብ ወሰዳችሁ ቆዳውን ገፋችሁ ብታዩት፡ ልክ እንደ ሴት ነው። ልክ ተመሳሳይ ነገር ነው። እሷንና ሁሉንም ነገር ወሰዳችሁ፡ እ… አቁሟቸውና፡ ሴቷን እንደዛ አቁሟት። ከድብ ጋር ተ—ተ—ተመሳሳይ ነው። እግሩ በተመሳሳይ መንገድ ነው፡ እጅም ልክ እንደ ሰው፡ እንደዚህ ይሆናል። ቺምፓንዚ ግን ከዚያ ሁሉ በበለጠ ቅርብ ነው። በጣም ይመሳሰላል፡ ሊደርሱበት ግን አይችሉም።

221 ለማወቅ ከፈለጋችሁ፡ ትንሽ ሚሰጥር ይኸውና። ምን ላይ እንደሆነ ታውቃላችሁ? የፈልጉትን አጥንቶች ሁሉ ይቆፍሩ። ለእነርሱ ተደብቆባቸዋል። መቆፈር ይችላሉ… ቆፋሪዎች መቆፈር ይችላሉ፡ ሳይንሱና፡ የ—የጊዜ አቆጣጠር ተመራማሪዎቹ የአቶሚክ መለኪያዎችን በመጠቀም የጊዜን ስኬል መለካት ቢችሉም፡ ሊደርሱበት አይችሉም። በምድር ላይ ከነበረው ከማንኛውም ነገር በላይ ሰው ይመስል የነበረው እባብ ነበር፡ እግዚአብሔርም ረገመው፡ በሆዱም እንዲሄድ አደረገው፡ ወዲያውም ሰው የማይመስል እባብ ሆነ። አሁን እነዚያ ሳይንቲሰቶች፡ ጭንቅላታቸው ይከኩ፡ ተውአቸው ለተወሰነ ጊዜ ያንን ይዘው ይጓዙ።

222 ይሁን እንጂ መጽሐፍ ቅዱስ “ከምድር አራዊት ሁሉ እጅግ ተንከለኛ ነበር፡” ይለዋል። በትክክል። እርሱ በሰውና በዝንጀሮ መካከል ያለ አያያዥ ነበር፡ እግዚአብሔርም ረገመውና በሠራው ነገር ምክንያት በ—በሆዱ እንድሄድ አደረገው። ይህችን ሴት አሳታት፡ ሴቲቱም የመጀመሪያ ልጇን ቃየንን ወለደች፡ እርሱንም እንደ እባብ ተፈጥሮ ተወለደ፡ እባብ ውስጥ የገባው፡ ዲያብሎስ፡ ይህን አደረገ።

223 ከዚያም ፀንሳ ወለደች፡ ከተታለለችም በኋላ እንደገና ፀነሰች። አሁን ተመልከቱ፡ ተሳሳተች፡ እሺ፡ ስ… ሰህተት ሰርታለች። ነገር ግን፡ ቃል በቃል፡ ከባሏ በፀነሰች ጊዜ ሕጋዊ ነበረች፡ ከዚያም ብዙ፡ ብዙ ጊዜ በኋላ፡ ከብዙ ወሮችና ብዙ ቀናት በኋላ ሊሆን ይችላል፣ ይህን መናገር አትችሉም፡ አናውቅም፡ ነገር ግን ከአዳም ወለደችው።

224 አንድ ሰው ጥያቄ ጠይቆ ነበር፡ እንዲህ ሲል፡ “እና፡ ስለ ልጁ… እንዲህ ተባለ እርሷም… ቃየን እንደተወለደ፡ እንዲህ አለች ‘ከጌታ ዘንድ ልጅ አገኘው።” አዎን፡ በእርግጠኛነት፡ መሆን ነበረበት። የተፈጥሮ ህግ ነበርና። ልክ ዛሬም እናንተ ያላችሁት በዚሁ ሁኔታ ነው። ልክ ሰትወለዱ፡ እግዚአብሔር

ወርዶ አይሰራችሁም። የአባታችሁና የእናታችሁ ዘር ናችሁ። እናንተም... እንዲሁ ትሆናላችሁ... ልጆቻችሁ የእናንተ ዘር ይሆናሉ። ልክ እንደ ዛፎች ፍሬና፡ እንደ መሳሰሉት ነገሮች፡ ያለማቋረጥ መባዛት ነው፡ ነገር ግን ወደ መጀመሪያው ይመለሳል። ይህ እንደሚያብራራው ተስፋ አደርጋለሁ።

225 ምን ያህል ጊዜ አለን? ብዙ የለንም። ቀጣይ እሑድ የምናየውን... ይህን ጥሩ ጥያቄ አዳምጡት፦ "በአንድ መንፈስ ሁላችንም አንድ አካል እንድንሆን ተጠምቀናል... " (ይህንን ማወቅ እንፈልጋለን።) "... ክርስቶስ።" በወቅቱ... አሁን፡ አንዳንድ ቅዱሳን መጻሕፍትን ይዣያለው፡ ጥሩ ጥቅሶችን [ወንድም ብራንሃም ይሄኛውን በክፍል ሁለት፡ ከጥያቄ 60 ጀምሮ መልስ ሰጥቶበታል—አርታዒ።]።

226 ይሄው ጥሩ ጥያቄው ነው፡ ይ... ይህን ለመመለስ አንድ ወይም ሁለት ደቂቃ፡ መጠበቅ ትችላላችሁ? እራሱን መመለስ ይችላል።

**59. "ክፉዎች ለዘላለም አይቃጠሉም፡" ሰ—ሰትል...** (መልካም፡ ጂሆቫ ዊትነሶችን አገኘኋቸው፡ አይደል?) **... ክፉዎች ለዘላለም አይቃጠሉም ሰትል፡ በገሃነም ወይስ በእሳት ባሕር ውስጥ ማለትህ ነው? በራዕይ** (ምዕራፍ 20 ላይ) **ሲኦል በእሳት ባሕር ውስጥ እንደሚጣል አውቃለሁ። እነሱ ለዘላለም አይቃጠሉም፡ ታዲያ እነሱ ምን ይሆናሉ?**

227 አስቀድሜ እንደተናገርኩት፡ ወንድም፡ ወይም እህት፡ ማንም ሁን፡ እነዚያ ይጠፋሉ፡ ምናቸውም አይቀርም ይጠፋሉ። መጀመሪያ ነበራቸው፡ በዚያም ያበቃላቸዋል፣ ምንም አይደሉም። ለምን... ያህል ጊዜ ይቃጠላሉ፡ ይህ በጣም አስቸጋሪ ነው። ነገር ግን፡ ተ... ተልከቱ፡

228 ይህንን በአዕምሯችሁ ውስጥ ማምጣት ከቻላችሁ፡ አያችሁ፡ በጣም ቀላል ነው። የዘላለም ሕይወት አንድ ብቻ ነው፡ እርሱም የሚመጣው በእግዚአብሔር በራሱ ነው። የዘላለም ሕይወትም እግዚአብሔር ራሱ ብቻ ነው። እዚ መዝገበ ቃላት ውስጥ ካያችሁ፡ **ዞዊ** የሚለውን የግሪክ ቃል ተመልከቱ። **ዞዊ** ማለት "የዘላለም ሕይወት" ማለት ነው። **የዘላለም ሕይወት** "እግዚአብሔር" ነው። ኢየሱስም ሲናገር፡ "የዘላለም ሕይወትን እሰጣቸዋለሁ።" እዚህ መዝገበ ቃላት ላይ ብትመለከቱ፡ እንዲህ ይላል፡ "ዞዊ።" ያ ብቸኛው የዘላለም ሕይወት ነው። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በዘላለም ሲኦል ይቃጠላሉ የሚልበት ቦታ የለም፡ የተባለው እንዲህ ነው "forever and ever" ለዘመን እና ለዘመናት።

229 አሁን፡ forever ዘመናት የሚለውን ቃሉን ለማየት፡ aeon የሚል ቃል፡ ተመልከቱ። **እዚህ** በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ፡ አስተውላችኋል? "ለዘመናት እና ለዘ-... " ሲባል፡ ሰንቶቻችሁ ሰምታችኋል? **ኤዮን** ማለት "የተወሰነ ዘመን" ማለት መሆኑን ሰንቶች ታውቃላችሁ? ለምን፡ አዎን፡ ማንም ሰው **ኤዮን** "የተወሰነ ዘመን" እንደሆነ ያውቃል።

230 "ለተወሰነ ዘመን ይቃጠላሉ፡" ያ የጊዜ ክፍተት ማለት ነው። "ወደ እሳቱ ባሕር ይጣላሉ፡ ለተወሰነ ዘመን ይቃጠላሉ።" **ኤዮን** ማለት "የተወሰነ ጊዜ" ማለት ነው። ለመቶ ሚሊዮን ዓመታት በቅጣት ሊቃጠሉ ይችላሉ ነገር ግን፡ በመጨረሻም፡ ወደ መጨረሻው መምጣት አለባቸው፣ በአጠቃላይ፡

ለመጥፋት። አያችሁ፡ ምክንያቱም ፍጹም ያልሆነው ሁሉ ፍጹም ከሆነው ነገር ተጣሞ የወጣ ነውና፥ መጀመሪያም ነበረው፡ ስለዚህም ፍጻሜ ሊኖረው ይገባል።

231 እኛ ግን በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ የምናምን **ዞዊ** አለን፡ "የእግዚአብሔር የራሱ ሕይወት" በእኛ ውስጥ፡ የዘላለም ሕይወት አለን። የዘመን እና ዘመናት ብቻ ሕይወት የለንም፡ የኃጢአተኛ ሕይወት ግን የዘመን እና የዘመናት ነው፡ እኛ ግን "የዘላለም ሕይወት" አለን።

232 በቅርብ ጊዜ፡ ወንድም ኮክስ፡ ድንጋዮቹን እዚያ ካገኘን በኋላ... በረንዳዬም እያስተካከልን ነበር፡ አንድ ትንሽ፡ ዘማንት ያስቆጠረ ቅሪተ አካል አነሣና፡ እንዲህ አለ፡ "ወንድም ብራንሀም፡ ይህ ስንት ዓመቱ ነው? "

233 "ኦህ፡" እንዲህ አልኩት፡ "በክሮኖሎጂካል፡ አሥር ሺህ ዓመታት ነው ማለት ትችላለህ። በአንድ ወቅት የኖረ፡ አንድ ትንሽ የጥንት የባሕር ጭራቅ፡ ትንሹ የባሕር እንስሳ፡ ባለፋት ዘመናት የኖረ ሊሆን ይችላል።"

234 እንዲህ አለ፡ "የሰው ሕይወት **ከዚያ** ሕይወት ጋር ሲነጻጸር ምን ያህል አጭር እንደሆነ አሰበው።"

235 እኔም አልኩት፡ "ኦህ፡ ነገር ግን፡ ወንድሜ፡ ያ መጨረሻ አለው፡ በክርስቶስ ያለን ህይወት ግን ፍጻሜ የለውም። ያ ሁለት ወይም ሶስት ዘመንና **ዘመናት** ሊኖር ይችላል፡ የዘላለም ህይወት ግን ፈጽሞ አይኖረውም፡ ምክንያቱም የዘላለም ህይወት የሚመጣው ከእግዚአብሔር ብቻ ነው።"

236 ዘላለማዊ፡ "ቃሌን የሚሰማ የላከኝንም የሚያምን፡ የዘላለም ሕይወት አለው ከሞትም ወደ ሕይወት ተሻገረ እንጂ ወደ ፍርድ **ፈጽሞ** አይመጣም።" አያችሁ፡ አማኝ በመሆናችሁ የዘላለም ህይወት ታገኛላችሁ። የማያምን የዘመናት የሆነ ሕይወት አለው። እ... አማኝ የዘላለም ሕይወት አለው፡ ሊጠፋም አይችልም ምክንያቱም ዘላለማዊ ነው።

237 አማኝ ግን፡ ይሄዳል... የማያምን ሰው በአለም ውስጥ ያልፋል፡ መከራዎች፡ ወዮታዎች፡ ያጋጥመዋል፣ እሱ የሚለው ዘና እያልን ነው፡ "ሁኡኡፒ፡ ዘና እያልን ነው።" በሴቶች፡ በወይን፡ ዘና እያልን ነው፡ እየኖረ እንደሆነ ያስባል። ይሞታል፡ ወደሚቃጠል ወደ እሳቱና ወደ ዲኑ ባሕር ይሄዳል፡ እሳቱም ከዘመንና ዘመናት ወደሚሆንበት፡ ምናልባትም ለአንድ መቶ ሚሊዮን አመታት ነፍሱ በእሳት እና በዲን ባህር ውስጥ ሊሰቃይ ይችላል።

238 እ... እናንተም፡ "ልክ እንደ መደበኛ እሳት ነውን? " ከዚያ አንድ ሚሊዮን እጥፍ የከፋ እንደሚሆን አምናለሁ። በእሳት፡ እሳት በሚለው ቃል ልትገልጸው እንደማትችሉ አምናለሁ። "እሳት፡" ተብሎ የተቀመጠበት ብቸኛው ምክንያት እሳት ፈጂ ከምንላቸው ካሉን ነገሮች ሁሉ የሚባላ ነገር ስለሆነ ነው። ሁሉንም ነገር ፈጽሞ ይበላል ያጠፋልም፡ እሳት ይህን ያደርጋል። መልካም፡ ከዚያም፡ እዚያ ውስጥ ይጣላል፡ ነገር ግን በሆነ ዓይነት መንገድ የሚቀጣ ነፍስ ይኖራችኋል...

239 አሁን፡ **እሳት** የሚለውን ቃል በጥንቃቄ መመልከት አለባችሁ፡ ምክንያቱም መንፈስ ቅዱስም "መንፈስ ቅዱስ እና እሳት" ተብሎ ተጠቅሷል፡ የመንፈስ ቅዱስ እሳት ኃጢአትን ያቃጥላል፡ አያችሁ፡ ያነጻልም።

240 ነገር ግን **ይህ** እሳት፡ ከገሃነም የመጣ ነው፡ እንዲህ ተብሏል "የእሳት ባህር።" ምንም ይሁን ምን፡ ሰቃይ ያለበት ቅጣት ነው። ባለጠጋው በሲኦል ውስጥ ሆኖ፡ ዓይኖቹን አንሥቶ፡ እንዲህ አለ፡ "አልዓዛርን በጣቶቹ ላይ ጥቂት ውኃ ይዞ፡ ከንፈሮቼን እንዲያሰነካ ላክልኝ፡ ነበልባሉ ያሠቃየኛልና" አለ። የሚነድ ገሃነም የለም ብለህ አታስብ፡ ቃል በቃል ገሃነም፡ አለ። ቃል በቃል ዲያብሎስ ካለ፡ ቃል በቃል ገሃነም አለ።

241 ነገር ግን፡ አያችሁ፡ የተበላሸ ነገር ሁሉ መጨረሻ አለው፡ ምክንያቱም በመጨረሻ ወደዚያ ንጽሕናና ወደ እግዚአብሔር ቅድስና መመለስ አለበት። እግዚአብሔር ዘላለማዊ ነው፡ ዘላለማዊ ሕይወት ካለን፡ እግዚአብሔር በእኛ ውስጥ ነው፡ እግዚአብሔርም እንደማይሞት ሁሉ እኛም ልንሞት አንችልም። አያችሁ።

242 አሁን፡ ጽሑፉ በእውነቱ እራሱን ያብራራል፡ አያችሁ፡ ትክክል ያደርገዋል። አሁን፡ እስቲ እንመልከት፡... ምን እንደሆነ አ... አላውቅም፡

**"ም—ምን ይሆናሉ?"**

243 እነዚህ ሁሉ ይጠፋሉ፡ ከእንግዲህ ወዲህ አይኖሩም። ነፍስ ትጠፋለች፡ መንፈስ ትጠፋለች፡ ሕይወት ትጠፋለች፡ ሰውነት ትጠፋለች፡ ሃሳብ ትጠፋለች፡ ትውስታ ትጠፋለች።

244 በዚያ በክብር ውስጥ፡ ምንም የክፋት ሀሳቦች አይኖሩም፡ ወይም በጭራሽ፡ በጭራሽ አይኖሩም። ይህ ትክክል ነው፡ ይህ ሁሉ ይሆናል... በዚህ ክፍል ውስጥ ካሉ ሰዎች በዚያ ይሆናሉ ብላችሁ፡ ማሰብ ትችላላችሁ... ?

245 መጽሐፍ ቅዱስ፡ "የክፉዎች ሃሳብ እንኳ ይጠፋል" አይልምን? ሐሳቡም ይጠፋል።

246 **እዚህ** አንድ ሰው አለ፡ **እዚህ** ታላቁ ቅዱስ አምላክ፡ እዚያም ነፍሱ እየተቃጠለች መሆኑን እንዴት ያውቃል? ለምን፡ ያ ሰማይ ሊሆን አይችልም። ሃሳቦች፡ ትዝታዎች፡ የተበላሸ ነገር ሁሉ፡ ክፉ ሃሳብ ሁሉ፡ ሁሉም ነገር ይጠፋል፡ በውስጡ ያለው ክፉ ነገር ሁሉ ይጠፋል። ከንጽህና በስተቀር ምንም እንሆንም፡ ከ **ዞዊ**፡ የእግዚአብሔር ሕይወት፣ ለዘላለም፡ ለዘመናት፡ ኖረን፡ ኖረን፡ ኖረን፡ ኖረን፣ ይህ መጨረሻ የለውም፡ ዘላለማዊ መሆን ነው!

247 "ወደ **ዘመናት** ቅጣት ውስጥ ተወሰዱ፡ ጻድቃን ግን ወደ ዘላለም ሕይወት ተወሰዱ።" ተረዳችሁ? **የዘመናት** ቅጣት፡ የዘላለም ሕይወት፡ እንዴት ያለ ልዩነት ነው!

248 አሁን፡ አያችሁ፡ ይሄን... አሁን፡ አውቀዋለሁ፡ ለእናንተ፡ ለውድ ልጆቼ፡ ራ—ራሴን ሁሉን-አዋቂ-አድርጌ ለማሳየት አልሞክርም። ያንን የማደርግ ከሆነ፡...

249 አሁን፡ ሶስት ወይም አራት ተጨማሪ ጥሩ ጥያቄዎች አሉ። ጌታ ቢፈቅድ፡ እሑድ ጠዋት እመልሳቸዋለሁ።

250 አሁን፡ ተመልከቱ። አያችሁ፡ ጥያቄዎች ተነስቷል። እኔም የሸመገለ ሰባኪ ነኝ። በ—በ—በ—በአገልግሎት ሃያ-ስድስት ዓመታት አሳልፌያለሁ። ይህን ማለት ስለቻልኩኝ፡ ለ—ለዚህ በጣም አመስጋኝ ነኝ፡ እኔም... መጀመሪያ ሳይገለጥ በሕይወቴ ውስጥ ምንም ነገር ለማቅረብ ሞክሬ አላውቅም። የጌታ መልአክ በጣም አመሰግናለሁ... ምንም ትምህርት አልነበረኝም፡ ችሎታም

አልነበረኝም። ይህም መልአክ ወረደ፡ ከእግዚአብሔርም ዘንድ የተላከ ረዳቴ ሆነ። ከዘፍጥረት እስከ ራእይ ባለው መጽሐፍ ውስጥ የተገለጸው ነገር ከዚህ ጋር ሙሉ በሙሉ የሚስማማ እንጂ፡ ሌላ ነገር አልነገረኝም... "አንተ—የመለኮትን የፈውስ ስጦታ ትቀበላለህ ሲለኝ" በፍጥነት ጻፍኩኝ። እንደተናገረው መንገድ አድርጌ አስቀምጬዋለሁ።

251 ከሦስት ዓመት ገደማ በኋላ፡ ሥራ አ—አስኪያጄ ትኩረቴን ወደዛ አደርገው፡ እንዲህ አለኝ፡ "ወንድም ብራንሃም፡ ይህን አስተውለሃል? 'ስጦታ' እስኪልህ ድረስ ያ ፍጹም ነው።"

252 አያችሁ፡ በጭራሽ "ስጦታ" አላለም። በ—በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ... እያንዳንዱ ስጦታ "ስጦታ" ነው ነገር ግን መለኰታዊ ፈውስ፡ እሱም "ስጦታ" ነው። "የፈውስ ስጦታዎች" ነው። ሁሉንም ዓይነት የፈውስ ስጦታዎች፡ በተለያዩ መንገዶች ልታገኙ ትችላላችሁ። ግን፡ ሌላ ሁሉም "ስጦታ" ነው፡ "የ" የትንቢት ስጦታ፡ "የ" **የዚህ** ስጦታ። መለኮታዊ ፈውስ ግን በብዙ ቁጥር ነው፡ "ስጦታዎች።" መንፈስ ቅዱስ ፍጹም መሆኑን፡ በፍጹም አላስተዋልሁም ነበር። ኦ፡ ጌታ ይባረክ!

253 ያንን መጽሐፍ ቅዱስ የጻፈው ያው መንፈስ ቅዱስ መሆኑን ተረድታችኋል፡ በመቶዎች በሚቆጠሩ ሰዎች፡ በመቶዎች ለሚቆጠሩ ዓመታት ልዩነት... አንዳቸውም ከሌላው አልተለያዩም። እርስ በርሳቸው ሙሉ ነበሩ፣ አንዱ ስለ ሌላው እንኳን ሰምተው አያውቅም።

254 ጳውሎስም፡ ወደ ዓረብ አገር ወረደ፡ ኢየሩሳሌምንም ለአሥራ አራት ዓመታት አልጎበኛትም ነበር። ነገር ግን በኢየሩሳሌም... ከሄደ በኋላ... ወደ ኢየሩሳሌም ሄዶ ተመልሶ አያውቅም ነበር። ነገር ግን በአረብ አገር ወርዶ፡ መስበክ ጀመረ፡ ጴጥሮስንና ሌሎቹን ለአሥራ አራት ዓመታት እንኳ አላያቸውም። በተሰበሰቡም ጊዜ፡ ያንኑ ነገር ተመሳሳይ ነገር ይሰብኩ ነበር። በኢየሱስ ክርስቶስ ስም የውሃ ጥምቀትና፡ መለኮታዊ ፈውስ፡ የእግዚአብሔርም ኃይል።

ኦህ!

> አንዱ በመሆኔ ደስተኛ ነኝ።
>
> አንዱ ነኝ፡ አንዱ ነኝ፡
> አንዱ በመሆኔ ደስተኛ ነኝ፣ (ሃሌሉያ!)
> አንዱ ነኝ፡ አንዱ ነኝ፡
> አንዱ በመሆኔ ደስተኛ ነኝ።
>
> ሰዎች በሁሉም ሰፍራ፡
> ልባቸው በእሳት ነበልባል፡
> በበዓለ ሃምሳ በወደቀው እሳት፡
> ባነጻቸውና ንጹህ ባደረጋቸው፣
> ኦህ፡ አሁን በልቤ ውስጥ እየነደደ ነው፡
> ኦ፡ ክብር ለስሙ ይሁን!
> አንዱ በመሆኔ ደስተኛ ነኝ።
>
> በላይኛው ክፍል ውስጥ ተሰብሰበው፡

ሁሉም በስሙ ሲጸልዩ፡
በመንፈስ ቅዱስ ተጠመቁ፡
ለአገልግሎትም ኃይል መጣ፣
የዚያን ቀን ያደረገላቸውን፡
እንዲሁ ያደርግላችኋል፡
አንዱ በመሆኔ ደስተኛ ነኝ።

አንዱ ነኝ፡ አንዱ ነኝ፡
አንዱ በመሆኔ ደስተኛ ነኝ። (ሃሌሉያ!)
አንዱ ነኝ፡ አንዱ ነኝ፡
አንዱ በመሆኔ ደስተኛ ነኝ።

255 አዳምጡ፡ ትንሽ መልእክት ይዢያለው ለእናንተ፡

ና፡ ወንድሜ፡ ይህንን በረከት ፈልግ
ልብህን ከኃጢአት ያነጻል፡
የደስታ-ደወል ይጀምርልሃል
የነፍስህን ነበልባል ሁሌ ይጠብቃል፡
ኦህ፡ አሁን በልቤ ውስጥ እየነደደ ነው፡
ኦህ፡ ክብር ለስሙ ይሁን፡
አንዱ በመሆኔ ደስተኛ ነኝ።

256 አንዱ ስለሆናችሁ ደስተኛ አይደላችሁም? ምንድነው ይሄ? የሚገልጠው መንፈስ ነው። የእግዚአብሔር መገለጥ ነው፡ “በዚችም አለት ላይ።” ሊቀ ጳጳስም ቢሆን ግድ የለኝም...

257 የካቶሊክ ቄስ፡ በቅርብ ጊዜ፡ በቤቴ ውስጥ ነበረ። እርሱም፡ “ሚስተር ብራንሃም፡ አንድ ጥያቄ ልጠይቅህ ነው የመጣሁት።”

እኔም፡ “እሺ፡ ወዳጄ” አልኩት።

258 እርሱም፡ “እዚህ ከቢሾፕ የተላከልህ ደብዳቤ፡ ለአንተ ይዣለሁ።”

እኔም፡ “እሺ፡ ወዳጄ” አልኩት።

259 እንዲህም አለ፡ “ስለምትናገራቸው ነገሮች፡ እጅህን አንስተህ እውነትን እንደምትናገር ትምላለህን? ”

260 እኔም፡ “አልምልም” አልኩት። እኔም “መጽሐፍ ቅዱስ፡ ‘በሰማይም በምድርም፡ አትማሉ (የእግሩ መረገጫ ነውና)። የሚትሉት ነገር አዎን እና አይደለም ይሁን።’ ቢሾፑ የምናገረውን መሰማት ከፈለገ፡ ቃሌን ይውሰድ። ካልሆነ፡ እኔ አልምልም” አልኩት።

261 እዚህ ሳክርድ ሀርት ቼርች የሚገኘው ይህ ምስኪን ቄስ፡ እንዲህ አለኝ፡ “ፓውሊን ፍሬዘርን **በዚህ-በዚያ** ቀን አጥምቀሃት ነበርን? ”

262 እኔም “አዎን፡ አጥምቄአታለሁ፡ ወዳጄ፡ በኦሃዮ ወንዝ ውስጥ” አልኩት።

263 “እንዴት ነበር ያጠመቅካት? ” አለኝ፡

264 “በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ከውኃው በታች በማስመጥ አጥምቂያታለው።” አልኩት፡

265 አሰቀመጠው። እንዲህ አለ፡ “ታውቃለህ፡ የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን እንዲህ ታጠምቅ ነበር።”

“መቼ? ” አልኩት፡

እርሱም “በድሮ ዘመን፡” አለኝ።

እኔም፡ “በምን ዘመን? ”

እርሱም፡ “ያኔ፡ በመጀመሪያ” አለኝ።

እኔም፡ “በምን መጀመሪያ? ”

እርሱም “በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ፡” አለኝ።

እኔም፡ “በድሮ-... በ——ደቀ መዝሙር ማለትህ ነውን? ”

እርሱም “አዎን፡” አለኝ።

እንዲህ አልኩት፡ “እነሱ፡ ማለት፡ ካቶሊኮች ነበሩ——ትላለህን... ? ደቀ መዝሙር ካቶሊኮች ነበሩ ትላለህን? ”

እርሱም “አዎን፡ ነበሩ፡” አለኝ።

እኔም አልኩት፡ “የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን የማትለወጥ ናት ብዬ አስብ ነበር? ”

እርሱም “አልተለውጠችም፡” አለኝ።

266 እኔም፡ “ታዲያ ጴጥሮስ ለምን፡ ‘ንስሐ ግቡ፡ በኢየሱስ ክርስቶስ ሰም ተጠመቁ’ ለምን አለ? እሱ... ጳጳስ አልነበረም እንዴ? ”

267 “አዎን።”

268 “ታዲያ ለምን ‘በአባት፡ በልጅ በመንፈስ ቅዱስ’ ሰም ታጠምቃላችሁ? እርሱም በጥልቅ ውሃ ውስጥ አደረገ፡ እናንተም ትረጫላችሁ። አሁን ምን ተፈጠረ? ”’

269 እርሱም “ግን፡ አየህ፡” አለኝ፡ “የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ማድረግ የምትፈልገውን ማንኛውንም ነገር የማድረግ ስልጣን አላት፡” አለኝ። ኧረ።

270 እኔም፡ “ደቀ መዛሙርቱንም ካቶሊኮች ብለሃቸዋል? ”

271 “አዎን፡” አለ።

272 እኔም፡ “ወዳጄ፡ ጆሴፈሰን አይቻለሁ፡ **የፎክስ ቡክ ኦፍ ማርቲይርስ** አይቻለሁ፡ **የፔምበር አርሊ ኤጅ** አንብቤአለሁ፡ **የሂሎፕ ቱ ባቢሎንስ** አንብቤአለሁ፡ በዓለም ውስጥ ካሉ በጣም ጥንታዊ ታሪኮች ውስጥ፡ የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን የተሾመችበት ወይም የተደራጀችበት ሰፍራ አሳየኝ... የመጨረሻው ሐዋርያ ከሞተ ከሰድስት መቶ ዓመታት በኋላ።”

“ኦህ፡” እንዲህ አለኝ፡ “ቤተ ክርስቲያን የምትለውን እናምናለን።”

እኔም፡ “መጽሐፍ ቅዱስ የሚለውን አምናለሁ” አልኩት። አያችሁ?

“ለምን፡” እንዲህ አለ፡ “እግዚአብሔር በቤተክርስቲያኑ ውስጥ ነው።”

273 እኔም፡ “እግዚአብሔር በቃሉ ውስጥ ነው” አልኩት። እኔም፡ “እንግዲህ... ” እርሱም... አልኩት፡ “መጽሐፍ ቅዱስ እግዚአብሔር በቤተ ክርስቲያኑ ውስጥ አለ አይልም፡ ነገር ግን መጽሐፍ ቅዱስ እግዚአብሔርን

በቃሉ እንዳለ ይናገራል። ‘በመጀመሪያ ቃል ነበረ፡ ቃልም በእግዚአብሔር ዘንድ ነበረ፡ ቃልም እግዚአብሔር ነበረ፣ በመካከላችንም አደረ።”’ ትክክል ነው። እንዲህ አልኩት፡ “እግዚአብሔር በቃሉ ውስጥ ነው።”

274 እርሱም ወጣና ተናገረ። እንዲህም አለ፡ “ደህና፡ መከራከር አልቻልንም” እንዲህ አለ፡ “ምክንያቱም አንተ በመጽሐፍ ቅዱስ ታምናለህ፡ እኔ በቤተክርስቲያን አምናለሁ።”

275 እኔም፡ “መጽሐፍ ቅዱስ በአምላክ መንፈስ መሪነት የተጻፈ ቃል እንደሆነ አምናለሁ በእሱም ውስጥ አንድ ተቃርኖ የለም። የእግዚአብሔር ቃል ነው፡ ለሚመጡት ዘመናት ሁሉ ዘላለማዊ ዕቅዶቹ ያሉበት ነው። እንዲህም አለ፡ ‘ሰማይና ምድር ያልፋሉ ቃሌ ግን አያልፍም።’ ትክክል ነው። ቃሉን አምናለሁ።”

276 ወደ ወይዘሮ ፍሬዘር ሄደ። እንዲህም አለ፡ “ወይዘሮ ፍሬዘር፡ ሴት ልጅሽ የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን አባል እንድትሆን እዚህ ወረቀት ላይ ትፈርሚያለሽን? ”

277 እንዲህ አለች፡ “ከእሷ ጋር ወደ መቃብር ብሄድ እመርጣለሁ።”

278 “ታሳፍራለህ፡” አለችው። እንዲህ አላት፡ “ልጅሽ ከዛ ከንቱ ነገር ወጥታ፡ ወደ ካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን መምጣቷ ማመስገን አለብሽ።”

279 እንዲህ አለች፡ “ወደ ቤተ ክርስቲያኔ የምትመጣው ሴት ልጅህ ብትሆንስ፡ ምን ትላለህ? ”

280 “ኦህ፡” እንዲህ አለ፡ “ይህ ይለያል።”

281 እንዲህ አለች፡ “አይ፡ ልዩ አይደለም።” ያቺን ትንሽ ሴት እዚያው ሲተዋት አንድ ቦታ እንደነበር ያውቅ ነበር። የሆነ ቦታ እንደነበረ ያውቃል። እንዲህ አለች፡ “አሁን፡ አሁን አንተ የገባህበት በር ክፍት ነው።”

282 አያችሁ፡ መንገዱ ይህ ነው። መሸነፍ የለባችሁም፡ መሸነፍ አይገባችሁም። እግዚአብሔር ለእናንተ ጋር ከሆነ፡ ማን ይቃወማችኋል? ትክክል! ችግሩ ዛሬ፡ የጀርባ አጥንት ሳይሆን ሰነፍ አጥንት ይዛችኋል! ለእውነትና ለእግዚአብሔር ቁሙ!

283 ከዘመናት በፊት በእነዚያ ሐዋርያት ላይ ያው የወረደው መንፈስ ቅዱስ፡ እግዚአብሔር ራሱን ለገለጠላቸው፡ ዛሬም በቤተክርስቲያኑ ውስጥ አለ። “ከሚምር ከእግዚአብሔር ዘንድ ነው እንጂ፡ ለሚወድ፡ ወይም ለሚሮጥ አይደለም።” እግዚአብሔር ነው፡ በምርጫው፡ ህዝቡን ያመጣል አይናቸውንም ይከፍታል። በፍጹም ልታዩት አትችሉም፡ ታውራችኋል፡ እግዚአብሔርም አይኖቻችሁን ካልከፈተ በስተቀር ማየት አትችሉም። መጽሐፍ ቅዱስ ሲናገር ዕውር ናችሁ፡ ማየትም አትችሉም ይላል። መሞከር አያስፈልግም። በሁሉም ትምህርት፡ ስኮላርሺፕ ልታገኝ ትችላለህ፡ ያለማቋረጥ ዓይንህ ይታወራል።

284 አሁን፡ አንቺ የክርስቶስ ቤተክርስቲያን ሆይ፡ አንቺ “መጽሐፍ ቅዱስ ሲናገር ተናገሪ ዝም ባለበት ቦታ ዝም በይ፡” በአንዳንዶቹስ? በዛ ላይ በኃይል ዝም ብለሻል። በትክክል።

285 አያችሁ፡ በመንፈስ የተገለጠ እውነትን ይጠይቃል። ከዚያም እግዚአብሔር ወርዶ ራሱን ገልጦ እውነት መሆኑን ያረጋግጣል። አሜን! እሱን ትወዱታላችሁ? እኔም እንደዚሁ። አሜን።

286 እሺ፡ እናንተ ሜቶዲስቶች በሙሉ አሁን ከባፕቲስቶች ጋር መጨባበጥ ትፈልጋላችሁ? እናንተ ፕሪስባይቴሪያኖች?

287 "አሁን፡" እንዲህ ትላላችሁ፡ "ወንድም ብራንሃም፡ እነዚህ እንዲህ ስላልሆኑ ባፕቲስቶችንና ፕሪስባይቴሪያኖችን ጉባኤው ታወግዛለህን-... ? "

288 አይ፡ ወዳጄ፡ አላደርግም። እንደ ወንድሞቼ ነው የምቆጥራቸው። በፍፁም! በፍፁም ካልተጠመቃችሁ እንኳ ግድ የለኝም፡ "በሳሮን ጽግረዳ፡ በቆላ አበባና በንጋት ኮከብ፡" ስም ብትጠመቁም እንኳ፡ ልክ እንደ... "አባት፡ ልጅ፡ መንፈስ ቅዱስ ስም" እንደዚያው ያው ነው። ሶስት ማዕረጎች። እሱ የሳሮን ጽግረዳ ነበር። አልነበረም? የቆላ አበባ፡ የንጋት ኮከብ፡ እነዚያ ሁሉ። በእርግጥ እሱ ነበር። እንዲሁም ሌላውም ሁሉ። ነገር ግን ይሄው፡ ትክክለኛው የመጽሐፍ ቅዱስ መንገድ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ነው። መጽሀፍ ቅዱሳዊ መንገድ ከፈለጋችሁ፡ ያ ትክክል ነው። ትክክለኛው መንገድ ያ ነው።

289 አሁን፡ "በአባት፡ በልጅ፡ በመንፈስ ቅዱስ" ስም ከተጠመቃችሁ ትክክል እንደሆነ ከተሰማችሁ፡ አሜን። ለእግዚአብሔር ንጹህ ሕሊና ለእግዚአብሔር መልካም መልስ ከሆነ፡ አሜን። ወደ ፊት ቀጥሉ፡ እያችሁ።

290 ግን እኔ እንደማስበው፡ የእኔን ድርሻ በተመለከተ፡ ብትጠይቁኝ፡ እንዲህ ብትሉኝ፡ "ወንድም ብራንሃም፡ ድጋሚ መጠመቅ አለብኝን? " በበኩሌ፡ "አዎን፡" እላለሁ።

291 በቀደም ምስኪን ሴት፡ ወደዚህ መጥታ "ጌታ ሰባኪ እንድሆን ጠራኝ፡" አለችኝ። ይሄን አልተቀበልኩትም፡ ወደ ጨረቃ መዝለል ትችላለች ቢሉኝ እንደማላምነው—ያህል ይሄን አላምንም። እሷም...

292 እኔም፡ "ደህና፡ ያ በጣም ጥሩ ነው፡ እህቴ" አልኳት። እንዲህ አልኳት፡ "አግብተሻል? "

"አዎን።"

"ሁለት ልጆች አሉሽ አይደል? "

"አዎን።"

እንዲህ አልኳት፡ "ምንድነው... ? ባልሽ ድኗል? "

"አልዳነም።"

እንዲህ አልኳት፡ "እርሱንስ ምን ልታደርጊው ነው? "

"ቤት ጥየው ሊወጣ ነው።"

293 እንዲህ አልኳት፡ "ከመቼውም ጊዜ በላይ ዲያብሎ የከፋ ወጥመዱ ይህ ነው። በመሰረቱ ቆንጆ ሴት ነሽ፡ እዚህ መሰክ ላይ ስትወጪ፡ የዲያብሎስ መደበኛ ማታለያ እና ዒላማ ትሆኛለሽ። ወጣት፡ ባልሽን፡ ከእነዚህም ሁለት ልጆች ጋር፡ ቤት ውስጥ ትተሽ ስትሄጂ፣ እሱ ከሌላ ሴት ጋር መሄድ ይጀምራል፡ እነዚህም ልጆች አንድ ቀን ሌላ አባት ይኖራቸዋል" አልኳት። እንዲህ አልኳት፡ "በመጀመሪያ ደረጃ፡ እግዚአብሔር ሴትን ከጠራ፡ ከቃሉ ጋር ይቃረናል።" እንዲህ አልኳት፡ "አሁን፡ አንቺ ከፈለግሽ ግን፡ ችግር የለውም።" እንዲህ አልኳት፡ "አሁን፡ የመለየት ጸጋ፡ ጌታ ሆይ የመለየት ጸጋ ስጠኝ ብለሻል። ወደ መድረክ ወጥተሽ፡ መሞከር፡ ትፈልጊያለሽን? "

294 እርሷም፡ “አዎ” አለች። ከዚያ በኋላ የሆነውን እናንተ አይታችኋል።

295 አያችሁ፡ ይደንቃል። ከቃሉ መምጣት አለበት። በቃሉ ውስጥ ከሌለ፡ ትክክል አይደለም። ሰሜታችሁ ምንም ቢል ግድ የለኝም፡ ትክክል አይደለም። አሜን! ጥሩ ይመስላል። አሜን!

296 መልካም፡

በሚያምረው ብርሃን፡ በብርሃኑ እንመላለሳለን፡
የምህረት ጠል ጠብታዎች ብሩህ ወደሆኑበት ኑ፣
በቀንም በሌሊትም በዙሪያችን ያበራል፡
ኢየሱስ፡ የዓለም ብርሃን ሆኗል።

እናንተ የብርሃን ቅዱሳን እንዲህ በሉ፡
ኢየሱስ፡ የዓለም ብርሃን ሆኗል፡
ያን ጊዜ የሰማይ ቃጭሎች ድምጽ ያሰማሉ፡
ኢየሱስ፡ የዓለም ብርሃን ሆኗል።

በሚያምረው ብርሃን፡ በብርሃኑ እንመላለሳለን፡
ጤዛ ወደሚወርድበት ቦታ ኑ...
በቀንም በሌሊትም በዙሪያችን ያበራል፡
ኢየሱስ፡ የዓለም ብርሃን...

297 ይህንን እንደገና ሰንዘምር፡ አሁን ሁሉም ሰው ወደ ቀኝ እንዲዞርና፡ በአራቱም አቅታጫዎች፡ ከሁሉም ጋር እንዲጨባበጥ እፈልጋለሁ፦

በሚያምረው ብርሃን፡ በብርሃኑ እንመላለሳለን፡ (አሜን!)
የምህረት ጠል ጠብታዎች ብሩህ ወደሆኑበት ኑ፣
በቀንም በሌሊትም በዙሪያችን ያበራል፡
ኢየሱስ፡ የዓለም ብርሃን...

298 ሜቶዲስቶችን ትወዷቸዋላችሁን? “ኣሜን፡” በሉ። [ጉባኤው፡ “ኣሜን” አለ።—አርታዒ።] ባፕቲሰቶችስ? ፕሪስባይቴሪያን? ካቶሊክ? የ... ኦህ፡ ሁሉንም ትዋደዳላችሁን? “ኣሜን።” በሉ፡ [“ኣሜን።”]

በሚያምረው ብርሃን፡ በብርሃኑ እንመላለሳለን፡

ሰንሄድ፡ እየተጨባበጥን።

ኦህ፡ የምህረት ጠል ጠብታዎች ብሩህ ወደሆኑበት ኑ፣
በቀንም በሌሊትም በዙሪያችን ያበራል፡
ኢየሱስ፡ የዓለም ብርሃን...

299 የማሰነባበቻ መዝሙር ከመዘመራችን በፊት... አሁን፡ እሑድ እንደገና እዚህ ልገኝ እችላለሁ። አሁን፡ ከዚያ በኋላ ከገና በኋላ አልመለሰም። አያችሁ፡ ምክንያቱም ወደ ሚቺጋን፡ ከሚቺጋን እስከ ኮሎራዶ፡ ከኮሎራዶ ወደ አይዳሆ፡ ከአይዳሆ ወደ ካሊፎርኒያ ሄደን፡ እንመለሳለን። ይቻላልና (እንዲትጸልዩልኝ እፈልጋለሁ) በዋተርሎ፡ አዮዋ እገኛለሁ፡ ከጥር ሃያ-አራተኛ ጀምሮ እስከ የካቲት ሁለተኛው ድረስ እዚያ እቆያለሁ። አያችሁ፡ በዚያ ትልቅ መድረክ፡ ጥሪውን ያገኘሁት ከጥቂት ጊዜ በፊት ነው፡ ለመጸለይ ከአሁን ጀምሮ እስከ እሁድ ድረስ አለኝ። አያችሁ፡ ዋተርሉ፡ አዮዋ፡ አሁን ቅርብ ነው።

300 አሁን ግን፡ አስታውሱ፡ የቅዳሜ ጥዋት ዘጠኝ ሰዓት ላይ፡ የወንድሞችን ብሮድካሰት አዳምጡ። ደውለን እናሳውቀዋለን። ይሄ በ WLRP፡ በኔቪል ኳርትት በዘጠኝ ሰአት፡ ቅዳሜ ጥዋት ላይ ያበቃል። እ... እ—እነሱን መመለስ ካልቻልኩ፡ ወንድም ኔቪል ጥያቄዎቹን ይጨርሳል። ትጨርሳለህ፡ ወንድም ኔቪል፡ ለእሁድ ጥዋት? [ወንድም ኔቪል እየሳቀ እንዲህ አለ፡ “ትልቅ ትዕዛዝ!”—አርታዒ።] ደህና፡ ይኸውልህ፡ ችግር ውስጥ ከገባህ፡ አብሬህ እሮጣለሁ። እሱ ይጠብቃል። ደህና።

301 መልካም፡

የኢየሱስ ስም ከአንተ ጋር ይሁን፡
የሀዘንና የዋይታ ልጅ፡
ደስታ እና ምቾት ይሰጣል፡
ኦህ፡ በሄድክበት ቦታ ሁሉ ውሰደው።

ውድ ስም፡ እንዴት ጣፋጭ ነው!
የምድር ተስፋ የሰማይ ደስታ፡
የከበረ ስም፡ (የተከበረ ሰም!) ኦህ እንዴት ጣፋጭ ነው!
(እንዴት ጣፋጭ ነው!)
የምድር ተስፋ የሰማይ ደስታ።

302 አሁን፡ በመጮህ የሚያምን ባፕቲሰት ማወቅ ከፈለጋችሁ፡ ይህ የማምነው አይነት ጩኸት ነው። ያቺ አሮጊት እናት እዚያ ተቀምጣ፡ መንፈስ በእሷ ላይ መጣ። መጮህ ጀመረች፡ መያዝ አልቻለችም፡ ወደ ኋላ ተመልሳ ልጇን አቀፈች። ማየት የምወደው በዚህ መንገድ ነው። ኣሜን። ያ እውነተኛ ጥሩ ነገር ነው፡ የድሮው-ዘመን፡ ከልብ-የመነጨ ሰሜት ነው። ኦህ፡ ማይ፡ ወ—ወደ ክብር ቤት ለመሄድ፡ የተዘጋጀች አረጋዊ፡ የደረሰች፡ የሚትጠባበቅ ቅድስት። መጥሪያውን በመጠባበቅ ላይ፡ እያችሁ፡ አስደሳች ጊዜ ማሳለፍ ብቻ ነው።

ደህና፡ ወንድም ኔቪል አሁን፡ ማድረግ የሚፈልገውን ሁሉ።

57-0925 ጥያቄ እና መልስ በዕብራውያን ክፍል ፤
ብራንሃም ተበርናክል
ጀፈርሰንቪል, ኢንዲያና ዩ.ኤስ.ኤ

AMHARIC

©2024 VGR, ALL RIGHTS RESERVED

VOICE OF GOD RECORDINGS
P.O. BOX 950, JEFFERSONVILLE, INDIANA 47131 U.S.A.
www.branham.org

## የቅጂ መብት ማሳሰብያ

ይህ መጽሐፍ የኢየሱስ ክርሰቶሰን ወንጌል ይሰፋ ዘንድ፣ በቤት ለግል ጠቀሜታም ሆነ ለሌሎች ሰዎች ያለ ክፍያ ለማበርከት፣ በቤት ማተሚያን መጠቀም ይቻላል። ይህ መጽሐፍ ያለ ቮይሰ ኦፍ ጋድ ሪከርዲንግሰ በጽሑፍ የተደገፈ ህጋዊ ፈቃድ መሸጥም ሆነ፣ አብዝቶ ማተም፣ በዌብ ሳይት ላይ ማሰቀመጥ፣ በማከማቻ ዘዴዎች ላይ ማሰቀመጥ፣ ወደ ሌሎች ቋንቋዎች መተርጎምም ሆነ የድጋፍ ማሰባሰቢያ አድርጎ መጠቀም የተከለከለ ነው። ህጋዊ መብቱም ሁሉ የተጠበቀ ነው®።

ለተጨማሪ መረጃ ወይም ተጨማሪ ግብዓቶች ቢፈልጉ፣ እባኮትን ይህ አድራሻ ይጠቀሙ፡

VOICE OF GOD RECORDINGS
P.O. BOX 950, JEFFERSONVILLE, INDIANA 47131 U.S.A.
www.branham.org